# የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የ2007 አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት

**ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ**
**ሓምሌ 2007**
**ዓዲግራት**

ይዘት ገፅ


| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 3 |
| 2 | መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ | 3 |
| | 2.1. ተማሪዎችን የሚመለከት አሃዛዊ መረጃ | 3 |
| | 2.2. የአካዳሚክ ሰራተኞች | 15 |
| | 2.3. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 19 |
| 3 | ለ2007 የተፈቀደልን ባጀትና አጠቃቀሙ | 21 |
| | 3.1. መደበኛ ባጀት | 21 |
| | 3.2. ካፒታል ባጀት | 23 |
| | 3.3. የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም | 24 |
| 4 | የእቅድ አፈፃፀም | 30 |
| | 4.1. የቁልፍ ተግባር አፈፃፀም | 30 |
| | 4.2. የዝግጅት ስልጠናዎች | 34 |
| | 4.3. የትምህርት አሰጣጥ | 36 |
| | 4.4. ምርምር እና ህብረተሰብ አገልግሎት | 37 |
| | 4.5. ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ | 39 |
| | 4.6. የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ግቦችና የዩኒቨርሰቲው አፈፃፀም | 40 |
| | 4.7. የ2007 አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሰንጠረዥ | 42 |
| 5 | ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች | 64 |
| 6 | ማጠቃለያ | 66 |
| | Appendix | 67 |

## የሰንጠረዦች ዝርዝር


| ሰንጠረዥ | ርእስ | ገፅ |
|---|---|---|
| ሰንጠረዥ 1 | በ2007 የተመደቡልን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች በትምህርት ዘርፍና በፆታ | 4 |
| ሰንጠረዥ 2 | የተመደቡት ተማሪዎች በመጡበት ክልልና በፆታ | 4 |
| ሰንጠረዥ 3 | ለ2007 የተመደቡልን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች በመጡበት ክልልና በተመደቡበት ፕሮግራም | 5 |
| ሰንጠረዥ 4 | የተመደቡልን ተማሪዎች ባገኙት የዩኒቨርሲቲ መግብያ ፈተና ውጤት | 6 |
| ሰንጠረዥ 5 | በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች | 7 |
| ሰንጠረዥ 6 | በ2007 በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ በሁለተኛ ሰሚስተር የተመዘገቡ መደበኛ ተማሪዎች (ቅድመ ምረቃ) | 8 |
| ሰንጠረዥ 7 | የ70፤30 ስርጭት (መደበኛ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች) | 10 |
| ሰንጠረዥ 8 | የማታ ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች (2007 ሁለተኛ ሰሚስተር) ቅድመ ምረቃ | 11 |
| ሰንጠረዥ 9 | የክረምት ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች (2006 ክረምት) | 13 |
| ሰንጠረዥ 10 | የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (ሁለተኛ ሰሚስተር) | 15 |
| ሰንጠረዥ 11 | የዩኒቨርሲቲው ጠቅላላ ተማሪዎች ብዛት | 15 |
| ሰንጠረዥ 12 | ስራ ላይ ያሉ የአገር ውስጥ የአካዳሚክ ሰራተኞች በአካዳሚክ መአርግ | 16 |
| ሰንጠረዥ13 | ስራ ላይ ያሉ የአገር ውስጥ መምህራን ብዛት (ሰኔ 2007) | 17 |
| ሰንጠረዥ 14 | የውጭ መምህራን | 19 |
| ሰንጠረዥ 15 | ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 20 |
| ሰንጠረዥ 16 | የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 21 |
| ሰንጠረዥ 17 | የመደበኛና ካፒታል ባጀት አጠቃቀም ማጠቃለያ (በባጀት አርእስት) | 22 |
| ሰንጠረዥ 18 | የመደበኛና ካፒታል ባጀት አጠቃቀም ማጠቃለያ (በፕሮግራም) | 22 |
| ሰንጠረዥ 19 | ለ2007 የተፈቀደ ካፒታል ባጀትና እስከ ሰኔ 30 ድረስ የነበረው አጠቃቀም | 24 |
| ሰንጠረዥ 20 | የሁለተኛ ዙር መሰረተ ልማት ስራዎች አፈፃፀም (ሰኔ 2007) | 28 |
| ሰንጠረዥ 21 | የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት አፈፃፀም (ሰኔ 2007) | 28 |
| ሰንጠረዥ 22 | የአራተኛ ዙር ግንባታ አፈፃፀም (ሰኔ 2007) | 28 |
| ሰንጠረዥ 23 | የተማሪዎች የአንድ ለአምስት እና የልማት ቡድኖች ብዛት | 32 |
| ሰንጠረዥ 24 | የመምህራን የአንድ ለአምስትና የልማት ቡድኖች ብዛት | 34 |
| ሰንጠረዥ 25 | የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የአንድ ለአምስት ቡድኖች ብዛት | 34 |
| ሰንጠረዥ 26 | የነባር ተማሪዎች ስልጠና ተሳታፊዎች (ነሃሴ 2006) | 35 |
| ሰንጠረዥ 27 | የመምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ተሳታፊዎች (መስከረም 2007) | 36 |
| ሰንጠረዥ 28 | የአዲስ ተማሪዎች ስልጠና ተሳታፊዎች (መስከረም 2007) | 36 |
| ሰንጠረዥ 29 | ተቀባይነት ያገኙ የምርምር ፕሮፖዛሎች (በኮሌጅ) | 38 |
| Appendix | Appendix 1 - 7 | 67-80 |

## 1. መግቢያ

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በ2007 አራተኛ ዙር መደበኛ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ የአመቱ ስራውን አጠናቋል። ዩኒቨርሲቲው ስራውን የጀመረው ህዳር 26/2004 ሲሆን፤ ያኔ 960 ተማሪዎችን በአራት ኮሌጆችና በአስራ ሶስት ትምህርት ክፍሎች እንዲመደቡ ተደርገዋል። ከመደበኛው ትምህርት ጎን ለጎን የማታ ተከታታይ ትምህርት በ2004 ሁለተኛ ሰሚስተር የክረምት ተከታታይ ትምህርት ደግሞ በ2005 ክረምት በመጀመር ዩኒቨርሲቲው በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ ተማሪዎችን ማስተናገድ ችሏል። በ2006 ሁለተኛ ሰሚስተር ላይ ዩኒቨርሲቲው የነበሩት ተማሪዎች ብዛት 7912 (6816 በመደበኛው፡ 725 በማታ ተከታታይ፡ እና 371 በክረምት ተከታታይ) ደርሶ የነበረ ሲሆን በ2007 ሁለተኛ ሰሚስተር ደግሞ የተማሪው ቁጥር 13378 (10040 በመደበኛው፡ 1018 በማታ ተከታታይ፡ እና 2320 በክረምት ተከታታይ) ደርሷል።

ዩኒቨርሲቲው በ2007 የትምህርት ዘመን በሁለት የትምህርት መስኮች (አካውንቲንግን እና ፋይናንስ– Master’s Degree in Accounting and Finance ፡ እንዲሁም ቢዝነስ አስተዳደር – Master of Business Administration [MBA]) የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የጀመረ ሲሆን በተጨማሪም ስድስት አዳዲስ የቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞችን (አርኪቴክቸር፡ ፋርማሲ፡ ኢንቫይሮንሜንታል ሳይንስ፡ አርኪዮሎጂ እና ሄሪቴጅ ማኔጅመንት፡ ትግርኛ፡ ትያትሪካል አርት) በመክፈት ተማሪዎች እንዲመደቡላቸው ተደርጓል።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እንደሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ሶስት ዋና ዋና ተልእኮዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ማስተማር፤ ምርምር እና የህብረተሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማከናወን ናቸው። ዩኒቨርሲቲያችን እነዚህን ተልእኮዎች በአጥጋቢ መልኩ ለማሳካት ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ የ2007 ዓመታዊ እቅዱን ካዘጋጀ በኋላ ከዝግጅት ምእራፍ ወደ ትግበራ ምእራፍ ተሸጋግሮ በአመቱ ያከናወናቸው ስራዎች እነሆ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2. መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ

### 2.1 ተማሪዎችን የሚመለከት አሃዛዊ መረጃ

ዩኒቨርሲቲው በ2004 የተመደቡለት መደበኛ ተማረዎች ብዛት 960 የነበረ ሲሆን በ2005 ደግሞ 3141 ተማሪዎች በመደበኛነት እና 117 ኤርትራውያን ስደተኞች በድምሩ 3258 ተማሪዎች በስድስት ኮሌጆች እና በ26 የትምህርት ፕሮግራሞች ተመድበው እንዲማሩ ተደርጓል። በ2006 የተመደቡት ተማሪዎች በመደበኛነት 4289 እና የኤርትራ ስደተኞች 130 በድምሩ 4419 ተማሪዎች ነበሩ።

በየአመቱ እንደምናደርገው ለ2007 የትምህርት ዘመን የመቀበል አቅማችን በ2006 መጨረሻ ላይ ለትምህርት ሚኒስቴር ያሳወቅን ሲሆን በዚሁም መሰረት ዩኒቨርሰቲው የሰባ–ሰላሳ ቀመርን በመንተራስ እና የተደረጉ ዝግጅቶችን እና በቀሪው ወራት የሚጠናቀቁ ስራዎችን (የግንባታ፡ የሰው ሃይል፡ የማቴርያሎች፡ ወዘተ) መሰረት በማድረግ 5000 ተማሪዎችን መቀበል እንደምንችል ባሳወቅነው መሰረት 4704 መደበኛ ተማሪዎች እና 116 ስደተኞች (96 የኤርትራ፡ እና 20 የሶማሊያ) በድምሩ **4820** ተማሪዎች ተመድበውልናል። ከነዚህ ውስጥ ለምዝገባ የቀረቡት ተማሪዎች በ2007 ከተጨመሩ ስድስት አዳዲስ ፕሮግራሞች ጋር በድምሩ በ37 የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲመደቡ ተደርገው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርገዋል።

ዘንድሮ የተመደቡልን መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች (የኤርትራና የሶማሊያ ስደተኞችን ሳይጨምር) በተመደቡበት የትምህርት መስክ እና በመጡበት ክልል እንዲሁም የፆታ ስብጥራቸው በሚከተሉት ሰንጠረዦች በዝርዝር ተመልክተዋል። ከላይ እንደተቀመጠው የተመደቡት ተማሪዎች 4704 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ሴቶች 2498 (53.1%) ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ 2206 (46.9%) ናቸው።

ሰንጠረዥ 1. በ2007 የተመደቡልን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች በትምህርት ዘርፍና በፆታ

| Band | Field of Study | M | F | Total | % | % of Female |
|---|---|---|---|---|---|---|
| I | Engineering Science (1a) | 1018 | 1007 | 2025 | 43.05 | 49.73 |
| | Computer Science (1b) | 51 | 89 | 140 | 2.98 | 63.57 |
| II | Natural and Computational Science (2) | 366 | 101 | 467 | 9.93 | 21.63 |
| III | Medicine (3a) | 41 | 78 | 119 | 2.53 | 65.55 |
| | Public Health Officer (3b) | 21 | 39 | 60 | 1.28 | 65.00 |
| | Other Health Sciences (3c) | 110 | 84 | 194 | 4.12 | 43.30 |
| IV | Agriculture and Env Sc (4b) | 147 | 143 | 290 | 6.16 | 49.31 |
| V | Business and Economics (5) | 241 | 720 | 961 | 20.43 | 74.92 |
| VI | Law (6a) | 13 | 47 | 60 | 1.28 | 78.33 |
| | Other Social Sciences (6b) | 184 | 174 | 358 | 7.61 | 48.60 |
| | Theatrical Arts (6c) | 14 | 16 | 30 | 0.64 | 53.33 |
| | Total | 2206 | 2498 | 4704 | 100 | 53.10 |

ከላይ በሰንጠረዥ 1 እንደተመለከተው ከተመደቡልን ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ማለትም 46% በባንድ አንድ (ኢንጂነሪንግ ሳይንስ እና ኮምፒዩተር ሳይንስ) ተመድበው የተላኩልን ናቸው። ዘንድሮ ከተመደቡልን መደበኛ ተማሪዎች ውስጥ የሴት ተማሪዎች ቁጥር (2498) ከወንድ ተማሪዎች ቁጥር (2206) የበዛ ነው። በሚከተለው ሰንጠረዥ እንደሚታየው ከተመደቡት ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ማለትም 45% የመጡት ከትግራይ ክልል ሲሆን የተቀሩት (55%) ደግሞ ከሌሎች ክልሎች/ከተሞች የተመደቡ ናቸው። ከሌሎች ክልሎች ከተመደቡት ውስጥ 935 (20%) ከአማራ፤ 589 (12.5) ከኦሮሚያ፤ እና 562 (12%) ከአዲስ አበባ ይገኙበታል። አነስተኛ የተማሪ ቁጥር የተመደቡልን ደግሞ ከሃረሪ (5)፤ ከድሬዳዋ (17)፤ እና ከጋምቤላ (18) ነው።

ሰንጠረዥ 2. የተመደቡት ተማሪዎች በመጡበት ክልል እና በፆታ

| ክልል / ከተማ | ወ | ሴ | ድምር | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 911 | 1210 | 2121 | 45.09 |
| ዓፋር | 15 | 8 | 23 | 0.49 |
| አማራ | 496 | 439 | 935 | 19.88 |
| ኦሮሚያ | 274 | 315 | 589 | 12.52 |
| ሶማሌ | 61 | 5 | 66 | 1.40 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 28 | 16 | 44 | 0.94 |
| ደቡብ ህዝቦች | 163 | 157 | 320 | 6.80 |
| ጋምቤላ | 16 | 2 | 18 | 0.38 |
| ሃረሪ | 2 | 3 | 5 | 0.11 |
| አዲስ አበባ | 227 | 335 | 562 | 11.95 |
| ድሬዳዋ | 13 | 4 | 17 | 0.36 |
| ሌሎች አገሮች | 0 | 4 | 4 | 0.09 |
| ድምር | 2206 | 2498 | 4704 | 100 |
| መቶኛ | 46.9 | 53.1 | | |

ሰንጠረዥ 3. ለ2007 የተመደቡልን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች በመጡበት ክልልና በተመደቡበት ፕሮግራም

| ክልል / ከተማ | Eng. Sci | Comp. Sc. | Natural and C Sc | Medic | PHO | OHS | Agric | Bus & Econ | Law | OSC | Thea Art | Total |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ትግራይ | 1275 | 80 | 102 | 9 | 37 | 74 | 173 | 200 | 17 | 153 | 1 | 2121 |
| ዓፋር | 8 | | 3 | | | 1 | 2 | 2 | 1 | 5 | 1 | 23 |
| አማራ | 257 | 39 | 76 | 22 | 15 | 66 | 88 | 274 | 10 | 84 | 4 | 935 |
| ኦሮሚያ | 91 | 9 | 145 | 8 | 3 | 26 | 8 | 243 | 10 | 40 | 6 | 589 |
| ሶማሌ | 3 | 1 | 26 | | | 10 | 1 | 6 | | 12 | 7 | 66 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 10 | 1 | 13 | | | 2 | 4 | 7 | | 7 | | 44 |
| ደቡብ ህዝቦች | 61 | 4 | 43 | 8 | 1 | 3 | 11 | 127 | 7 | 52 | 3 | 320 |
| ጋምቤላ | 3 | | 4 | | | | 1 | 5 | | 4 | 1 | 18 |
| ሃረሪ | 2 | | 2 | 1 | | | | | | | | 5 |
| አዲስ አበባ | 308 | 6 | 46 | 69 | 4 | 10 | 2 | 94 | 15 | 1 | 7 | 562 |
| ድሬዳዋ | 6 | | 6 | 2 | | 1 | | 2 | | | | 17 |
| ሌሎች አገሮች | 1 | | 1 | | | 1 | | 1 | | | | 4 |
| ድምር | 2025 | 140 | 467 | 119 | 60 | 194 | 290 | 961 | 60 | 358 | 30 | 4704 |

የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤታቸውን በተመለከተ ደግሞ ውጤቱ የሚታረመው ከ700 ሲሆን ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የተመደቡት ተማሪዎች በየተመደቡበት የትምህርት ዘርፍ ያገኙት የመግቢያ ፈተና ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል። በሰንጠረዡ እንደሚታየው የመግቢያ ውጤታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ሊቀመጥ የሚችል ነው። ከተመደቡት ተማሪዎች ውስጥ 60.88% የሚሆኑት ውጤታቸው ከ350 በታች (ማለትም ከግማሽ በታች) ነው። አብዛኛዎቹ (ማለትም 48%) የተመደቡልን ተማሪዎች ያገኙት ውጤት ከ300 እስከ 350 ነው። በማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ ከተመደቡልን ተማሪዎች ውስጥ 85% የሚሆኑት ያገኙት የመግቢያ ፈተና ውጤት ከ300 በታች ነው። ከተመደቡልን ተማሪዎች ውስጥ ከ500 በላይ ውጤት ያገኙ ተማሪዎች 0.68% ወይም 32 ተማሪዎች ብቻ ናቸው። እነዚህም ከአንድ ተማሪ በስተቀር በሙሉ የተመደቡት በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ነው። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተመደቡበት የኢንጂነሪንግ ሳይንስ መስክ ላይ ከተመደቡት 2025 ተማሪዎች ውስጥ 1803 ወይም 89% የሚሆኑት ያገኙት ወጤት ከ350 በታች ነው። በአጠቃላይ ሲታይ በ2006 ተመድበውልን ከነበረው ተማሪዎች ውስጥ የዘንድሮው የተማሪዎች ውጤት የተሻለ ቢሆንም አብዛኛዎቹ የተመደቡልን ተማሪዎች ያገኙት የዩኒቨርሰቲ መግቢያ ውጤት አነስተኛ እንደሆነ ማየት ይቻላል። እንደሚገመተው በህክምናና በጤና ዘርፍ የተመደቡት ተማሪዎች ግን የበለጠ ውጤት ያላቸው ናቸው። በዚህ መስክ የተመደቡ ተማሪዎች በሙሉ ከ350 በላይ ያገኙ ሲሆን እንዲያውም በህክምና የተመደቡት ተማሪዎች በሙሉ ከ450 በላይ ያገኙ ናቸው።

የተማሪዎች የመግቢያ ውጤት የተማሪዎችን ችሎታ በተሟላ መልኩ ሊገልፅ ይችላል ተብሎ ባይወሰድም የተማሪዎች ችሎታ ዋና አመላካች መሆኑ ግን ግልፅ ነው። ሆኖም ከባለፈው ልምዳችን እንደታየው አንዳንድ በድጋፍ (Affirmative Action) የገቡ ሴት ተማሪዎች ለውጤትና ለሽልማት በቅተዋል። ስለዚህ አነስተኛ የመግቢያ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የተሻለ ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ የሚታወቅ ነው። በተጨማሪም የተማሪዎች የመግቢያ ውጤት አነስተኛ መሆኑ በዩኒቨርሰቲው በኩል ይሄ ታውቆ ተጨማሪ ጥረት በማድረግ ተማሪዎችን የማብቃት ስራ መሰራት እንዳለበት የሚያመለክት ነው። ባጠቃላይ የመግቢያ ውጤት ብቻ በማየት ተማሪዎቹ በጥቅሉ ብቃታቸው አነስተኛ ነው ለማለት የማያስደፍር ሲሆን ዩኒቨርሲቲ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ጠንክሮ ከተሰራበት (በዩኒቨርሲቲውም በተማሪዎችም) ብቃታቸው ወደተፈለገበት ደረጃ ማድረስ የማይቻልበት ምክንያት ሊኖር እንደማይችል መገንዘበ ያሻል።

ሰንጠረዥ 4. የተመደቡልን ተማሪዎች ባገኙት የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት

| Band | Field of Study | >=500 | [450, 500) | [400,450) | [350, 400) | [300,350) | <300 | Total |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| I | Engineering Science (1a) | 0 | 18 | 204 | 714 | 1089 | 0 | 2025 |
| I | Computer Science (1b) | 1 | 0 | 9 | 43 | 87 | 0 | 140 |
| II | Natural and Computational Science (2) | 0 | 0 | 56 | 158 | 253 | 0 | 467 |
| III | Medicine (3a) | 30 | 89 | 0 | 0 | 0 | 0 | 119 |
| III | Public Health Officer (3b) | 1 | 6 | 51 | 2 | 0 | 0 | 60 |
| III | Other Health Sciences (3c) | 0 | 1 | 19 | 174 | 0 | 0 | 194 |
| IV | Agriculture and Env Sc (4b) | 0 | 0 | 15 | 75 | 200 | 0 | 290 |
| V | Business and Economics (5) | 0 | 0 | 3 | 136 | 510 | 312 | 961 |
| VI | Law (6a) | 0 | 2 | 4 | 16 | 30 | 8 | 60 |
| VI | Other Social Sciences (6b) | 0 | 0 | 1 | 7 | 86 | 264 | 358 |
| VI | Theatrical Arts (6c) | 0 | 0 | 0 | 5 | 21 | 4 | 30 |
| | Total | 32 | 116 | 362 | 1330 | 2276 | 588 | 4704 |
| | **Percent** | **0.68** | **2.47** | **7.70** | **28.27** | **48.38** | **12.50** | **100.00** |

ከላይ በየሰንጠረዡ ከተቀመጠው የአዲስ መደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ 96 ኤርትራውያን እና 20 ሶማሊያውያን ተማሪዎች (በድምሩ 116 ሆኖ ከነዚህ ውስጥ 22 ሴቶች ሲሆኑ 94 ደግሞ ወንዶች ናቸው) የተመደቡልን ሲሆን ከተመደቡት ስደተኛ ተማሪዎች ውስጥ ግን ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩት 77 ብቻ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ 69 ኤርትራውያን (64 ወንድ እና 5 ሴት) ሲሆኑ 8 ደግሞ ሶማልያውያን (7 ወንድ እና 1 ሴት) ናቸው።ስለዚህ ቀደም ብሎ እንደተቀመጠው በ2007 የተመደቡልን ጠቅላላ የተማሪዎች ብዛት 4820 ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የሴት ተማዎች ብዛተ 2520 (ወይም 52.3%) ሴት ተማሪዎች ናቸው።

ኢዲስ ተማሪዎችን ከተቀበልን በኋላ የትምህርት ክፍል መረጣና ምደባ የተደረገ ሲሆን ምደባው ተደርጎ በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩ የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት (የአንደኛ አመት፤ የሁለተኛ አመት፤ የሶስተኛ አመት፤ እና የአራተኛ አመት ተማሪዎች) 10676 የነበረ ሲሆን (ዝርዝሩ በAppendix 1 ተመልክቷል) የድህረ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች ደግሞ 14 ነበር። በድምሩ በ2007 አንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት በመከታተል ላይ የነበሩት መደበኛ ተማሪዎች (ቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ) 10690 ነበር።

በሁለተኛው ሰሚስተር ተመዝገበው ትምህርት የተከታተሉት መደበኛ ተማሪዎች ብዛት 10027 ነው። ከዚህ ቁጥር ውስጥ የወንድ ተማሪዎች ብዛት 5875 (58.6%) ሲሆን የሴት ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 4152 (41.4%) ነው። አንደኛ ሰሚስተር ላይ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከነበሩት 10690 ተማሪዎች ውስጥ በሁለተኛው ሰሚስተር ላይ በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ስለነበሩ እና በሌላ በኩል ደግሞ በዳግመ ቅበላ (readmission) በሁለተኛ ሰሚስተር የገቡ ተማሪዎችም መኖራቸው ታሳቢ በማድረግ 10027 መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በሁለተኛው ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ በተመለከተ በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት በእቅዱ ዘመን መጨረሻ (ማለትም 2007 መጨረኛ) ላይ የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች ቁጥር የጠቅላላ ተማሪዎች 40% ለማድረስ የሚል ሲሆን በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከዚህ ግብ አነስተኛ ብልጫ ያለው መሆኑ መገንዘብ ይቻላል። በ2007 በሁለተኛ ሰሚስተር የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝር በሰንጠረዥ 6 የተቀመጠውን ይመስላል።

በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩን መደበኛ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ቁጥር 545 ሲሆን ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 5፡ በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ የቅድመ ምረቃ መደበኛ ተማሪዎች

| አይነት | አንድኛ አመት | | | ሁለተኛ አመት | | | ሶስተኛ አመት | | | አራተኛ አመት | | | ጠቅላላ ድምር | | | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| ተፈቅዶላቸው ያቋረጡ (Withdrawals) | 37 | 32 | 69 | 18 | 4 | 22 | 7 | 4 | 11 | 0 | 0 | 0 | 62 | 40 | 102 | 0.96 |
| ሳያስፈቅዱ ያቋረጡ (Dropouts) | 132 | 125 | 257 | 19 | 10 | 29 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 151 | 135 | 286 | 2.7 |
| በትምህርት ድክመት (Dismissals) | 54 | 83 | 137 | 10 | 7 | 17 | 2 | 1 | 3 | 0 | 0 | 0 | 66 | 91 | 157 | 1.47 |
| ድምር | 223 | 240 | 463 | 47 | 21 | 68 | 9 | 5 | 14 | | | | 279 | 266 | 545 | 5.13 |

የተማሪዎች የአንደኛ ሰሚስተር ውጤታቸው በተመለከተ በዩኒቨርሰቲው ሰኔት ውይይት ተደርጎበት የሬሜድያል ወይም ማጠናከርያ ድጋፍ ከተደረገ በኋላ በትምህርት ድክመት ትምህርት ያቋረጡት ተማሪዎች ቁጥር በድምሩ 157 ነው። ትምህርት ካቋረጡት ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ (ማለትም 2.7%) በራሳቸው ፈቃድ እና ዩኒቨርሲቲውን ሳያሳውቁ ያቋረጡ (drop outs) ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ (ማለትም 1.47%) በትምህርት ድክመት መቀጠል ያልቻሉት ናቸው። በትምህርት ድክመት ትምህርት ካቋረጡት ውስጥ የሴቶች ቁጥር (58%) እንደሚበዛ ከሰንጠረዡ መመልከት ይቻላል። በአንድ በኩል በዩኒቨርሲቲው ያሉት የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በትምህርት ድክመት ምክንያት ትምህርት መቀጠል ያልቻሉት አብዛኛዎቹ ሴት ተማሪዎች መሆናቸው በተለይ ሴት ተማሪዎችን መሰረት ያደረጉ የድጋፍ ስራዎች በስፋት መሰራት እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው። በራሳቸው ፈቃድ ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ያቋረጡበት ምክንያት የተለያየ ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ሲሆን በተለይም ደግሞ አብዛኛዎቹ ያቋረጡ ተማሪዎች የአንደኛ አመት ተማሪዎች ከመሆኑ አንፃር ከምክንያቶቹ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ትምህርቱን አንችለውም የሚል ስጋት፤ ከቤተሰብ ተለይቶ ለመኖር መቸገር፤ ከህመም ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ እና የኢኮኖሚ ችግር እንደሆኑ ይገመታል። በድምሩ በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት ከጀመሩት ውስጥ 5.13% (ወይም 545 ተማሪዎች) በሁለተኛ ሰሚስተር መቀጠል አልቻሉም። የትምህርት ማቋረጥ መጠንን አስመልክቶ ዩኒቨርሲቲው በ2007 የያዘው እቅድ አምና ከነበረበት የ 7.16% ወደ 5% ማውረድ የነበረ ሲሆን እቅዱ እንደተሳካ ግልፅ ነው። ሆኖም አሁንም ቢሆን በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ቁጥር በርካታ ስለሆነ ማቋረጥን መቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ዩኒቨርሲቲው መጠቀም እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው።

ሰንጠረዥ 6. በ2007 በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ በሁለተኛ ሰሚስተር የተመዘገቡ መደበኛ ተማሪዎች (ቅድመ ምረቃ)

| College | Department | 1st year | | | 2nd year | | | 3rd year | | | 4th year | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| CET | Civil Engineering | 272 | 370 | 642 | 396 | 181 | 577 | 257 | 121 | 378 | 58 | 82 | 140 | 983 | 754 | 1737 |
| | Construction Mgt & Tech. | 106 | 179 | 285 | 110 | 63 | 173 | 76 | 27 | 103 | | | | 292 | 269 | 561 |
| | Computer Science | 34 | 36 | 70 | 56 | 26 | 82 | 19 | 15 | 34 | | | | 109 | 77 | 186 |
| | Information technology | 17 | 49 | 66 | 25 | 22 | 47 | | | | | | | 42 | 71 | 113 |
| | Elect.& Comp.Engineering | 204 | 131 | 335 | 164 | 40 | 204 | 115 | 29 | 144 | 29 | 20 | 49 | 512 | 220 | 732 |
| | Chemical Engineering | 89 | 98 | 187 | 124 | 45 | 169 | 77 | 27 | 104 | 22 | 25 | 47 | 312 | 195 | 507 |
| | Mechanical Engineering | 267 | 85 | 352 | 257 | 25 | 282 | 156 | 23 | 179 | 33 | 10 | 43 | 713 | 143 | 856 |
| | Architecture | 31 | 13 | 44 | | | | | | | | | | 31 | 13 | 44 |
| | **Subtotal** | **1020** | **961** | **1981** | **1132** | **402** | **1534** | **700** | **242** | **942** | **142** | **137** | **279** | **2994** | **1742** | **4736** |
| CNCS | Biology | 77 | 40 | 117 | 18 | 88 | 106 | 39 | 47 | 86 | | | | 134 | 175 | 309 |
| | Chemistry | 42 | 10 | 52 | 11 | 53 | 64 | 26 | 41 | 67 | | | | 79 | 104 | 183 |
| | Mathematics | 27 | 14 | 41 | 13 | 35 | 48 | 30 | 8 | 38 | | | | 70 | 57 | 127 |
| | Statistics | 55 | 4 | 59 | 18 | 25 | 43 | 31 | 6 | 37 | | | | 104 | 35 | 139 |
| | Physics | 46 | 5 | 51 | 17 | 30 | 47 | 26 | 15 | 41 | | | | 89 | 50 | 139 |
| | Geology | 37 | 16 | 53 | 22 | 22 | 44 | 23 | 6 | 29 | | | | 82 | 44 | 126 |
| | Sport Science | 30 | 21 | 51 | 15 | 29 | 44 | 23 | 17 | 40 | | | | 68 | 67 | 135 |
| | **Subtotal** | **314** | **110** | **424** | **114** | **282** | **396** | **198** | **140** | **338** | | | | **626** | **532** | **1158** |
| CMHS | Medicine | 36 | 53 | 89 | 82 | 28 | 110 | 33 | 10 | 43 | | | | 151 | 91 | 242 |
| | Pharmacy | 33 | 8 | 41 | | | 0 | | | 0 | | | | 33 | 8 | 41 |
| | Midwifery | 28 | 32 | 60 | 36 | 18 | 54 | 22 | 4 | 26 | | | | 86 | 54 | 140 |
| | Nursing | 47 | 44 | 91 | 32 | 16 | 48 | 16 | 13 | 29 | | | | 95 | 73 | 168 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Health Officer(P. H.) | 20 | 35 | 55 | 41 | 12 | 53 | 31 | 9 | 40 | | | | 92 | 56 | 148 |
| | Subtotal | 164 | 172 | 336 | 191 | 74 | 265 | 102 | 36 | 138 | | | | 457 | 282 | 739 |
| CAES | Plant Science | 33 | 44 | 77 | 31 | 25 | 56 | 22 | 13 | 35 | | | | 86 | 82 | 168 |
| | Animal.Pr.&Tech. | 34 | 44 | 78 | 47 | 7 | 54 | 28 | 3 | 31 | | | | 109 | 54 | 163 |
| | N.R.Management | 34 | 36 | 70 | 21 | 22 | 43 | 17 | 15 | 32 | | | | 72 | 73 | 145 |
| | Environmental Science | 37 | 27 | 64 | | | | | | | | | | 37 | 27 | 64 |
| | **Subtotal** | **138** | **151** | **289** | **99** | **54** | **153** | **67** | **31** | **98** | | | | **304** | **236** | **540** |
| CBE | Economics | 72 | 88 | 160 | 134 | 9 | 143 | 96 | 12 | 108 | | | | 302 | 109 | 411 |
| | Acct & Fina. | 77 | 229 | 306 | 148 | 83 | 231 | 117 | 57 | 174 | | | | 342 | 369 | 711 |
| | Management | 73 | 184 | 257 | 135 | 74 | 209 | 88 | 63 | 151 | | | | 296 | 321 | 617 |
| | Marketing | 19 | 89 | 108 | 36 | 19 | 55 | | | | | | | 55 | 108 | 163 |
| | **Subtotal** | **241** | **590** | **831** | **453** | **185** | **638** | **301** | **132** | **433** | | | | **995** | **907** | **1902** |
| CSSH | Law | 14 | 38 | 52 | 42 | 8 | 50 | | | | | | | 56 | 46 | 102 |
| | Theatrical Art | 8 | 16 | 24 | | | | | | | | | | 8 | 16 | 24 |
| | English Lan.&Lit. | 11 | 17 | 28 | 9 | 20 | 29 | 23 | 22 | 45 | | | | 43 | 59 | 102 |
| | Geography | 35 | 16 | 51 | 32 | 36 | 68 | 26 | 28 | 54 | | | | 93 | 80 | 173 |
| | Tigrigna | 5 | 24 | 29 | | | 0 | | | 0 | | | | 5 | 24 | 29 |
| | Sociology | 42 | 17 | 59 | 55 | 53 | 108 | | | 0 | | | | 97 | 70 | 167 |
| | Civics & Eth.Educ. | 34 | 21 | 55 | 38 | 27 | 65 | 26 | 19 | 45 | | | | 98 | 67 | 165 |
| | Psychology | 20 | 44 | 64 | 28 | 13 | 41 | 32 | 23 | 55 | | | | 80 | 80 | 160 |
| | Archeology | 19 | 11 | 30 | | | | | | | | | | 19 | 11 | 30 |
| | **Subtotal** | **188** | **204** | **392** | **204** | **157** | **361** | **107** | **92** | **199** | | | | **499** | **453** | **952** |
| **TOTAL** | | **2065** | **2188** | **4253** | **2193** | **1154** | **3347** | **1475** | **673** | **2148** | **142** | **137** | **279** | **5875** | **4152** | **10027** |

ሰንጠረዥ 7. የ70፤30 ስርጭት (መደበኛ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች)

| ኮሌጅ | ወ | ሴ | ድ | መቶኛ | 70-30 ቀመር |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ (ባንድ 1) | 2994 | 1742 | 4736 | 47.23 | |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ (ባንድ 2) | 626 | 532 | 1158 | 11.55 | |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ (ባንድ 3) | 457 | 282 | 739 | 7.37 | |
| ግብርናና አከባቢ ጥናት (ባንድ 4) | 304 | 236 | 540 | 5.39 | **71.54** |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ (ባንድ 5) | 995 | 907 | 1902 | 18.97 | |
| ህብረተሰብ ሳይንስና ስነሰብ (ባንድ 6) | 499 | 453 | 952 | 9.49 | **28.46** |
| ድምር | 5875 | 4152 | 10027 | 100 | |
| መቶኛ | 58.59 | 41.41 | 100 | | |

በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲሟላ የሚፈለገው የተማሪዎች ስብጥር ከተማሪዎቹ 70% በተፈጥሮ ሳይንስ መስኮች (ባንድ 1፣ 2፣ 3 እና 4) እንዲሆኑ ሲሆን የተቀሩት 30% ደግሞ በማህበራዊ ሳይንስ መስኮች (ማለትም ባንድ 5 እና 6) እንዲሆኑ ነው። በየባንዱ ሲታይ ደግሞ በሃገር አቀፍ ደረጃ መኖር የሚገባው ስብጥር በኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ (ባንድ 1) 40%፤ በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ (ባንድ 2) 20%፤ በህክምናና ጤና ሳይንስ (ባንድ 3) 5%፤ በግብርናና አከባቢ ሳይንስ (ባንድ 4) 5%፤ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ (ባንድ 5) 20%፤ እና በሌሎች ህብረተሰብ ሳይንስ (ባንድ 6) 10% ነው። ከላይ በሰንጠረዥ 6 እንደሚታየው በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የመደበኛ ተማሪዎች ስብጥር 71.54% ያህሉ በተፈጥሮ ሳይንስ እና 28.46% ያህሉ ደግሞ በማህበራዊ ሳይንስ በሚገኙ የትምህርት መስኮች መሆኑን ያሳያል። በዚሁም መሰረት አጠቃላይ ስርጭቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚፈለገው ጋር ተመሳሳይ መሆኑ መረዳት ይቻላል። በየባንዱ ያለው ስርጭት ግን በባንድ አንድ (ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ) ያለው ከኮታው በላይ መሆኑ ማየት ይቻላል። ህክምናና ጤና ሳይንስም ከኮታ በላይ ነው። ከኮታ በታች የሆነው ደግሞ የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ወይም ባንድ ሁለት ነው።

ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ የማታ ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች እና የክረምት ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች ያሉት ሲሆን በ2007 አንደኛ ሰሚስተር በቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር በማታ ተከታታይ በሶስት ኮሌጆችና በስምንት ፕሮግራሞች በድምሩ 1188 (675 ወንድ እና 513 ሴት) ተማሪዎች ተመዝግበው ትምህርታቸውን የተከታተሉ መሆናቸው በመንፈቀ አመቱ ሪፖርት ተመልክቶ ነበር። በአመቱ ሁለተኛ ሰሚስተር ደግሞ በማታ ተከታታይ ትምህርት (ቅድመ ምረቃ) ተመዝግበው ትምህርታቸውን የተከታተሉ የተማሪዎች ብዛት ደግሞ በሚከተለው ሰንጠረዥ በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን በድምሩ 923 (ማለትም 524 ወንዶችና 399 ሴቶች) ተማሪዎች ናቸው። ይህም ማለት በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩት የማታ ተከታታይ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ውስጥ 265 የሚሆኑት በተለያየ ምክንያት ትምህርት አቋርጠዋል ማለት ነው።

### ሰንጠረዥ 8፡ የማታ ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች (2007 ሁለተኛ ሰሚስተር) - ቅድመ ምረቃ

| College | Department/Program | 2004 Class | | | 2005 Class | | | 2006 Class | | | 2007 Class | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| CET | Cicvil Engineering | 29 | 26 | 55 | 28 | 2 | 30 | 28 | 2 | 30 | 33 | 2 | 35 | 118 | 32 | 150 |
| | Construction Technology and Mgt (CoTM) | | | | | | | 23 | | 23 | | | | 23 | | 23 |
| | Information Technolgoy | | | | | | | 4 | 13 | 17 | | | | 4 | 13 | 17 |
| | Electrical engineering | 15 | 1 | 16 | | | | | | | | | | 15 | 1 | 16 |
| | **SUB TOTAL** | **44** | **27** | **71** | **28** | **2** | **30** | **55** | **15** | **70** | **33** | **2** | **35** | **160** | **46** | **206** |
| CMHS | Health Officer | | | | | | | 31 | 21 | 52 | 32 | 16 | 48 | 63 | 37 | 100 |
| | Nursing | | | | 15 | 14 | 29 | 17 | 25 | 42 | 27 | 46 | 73 | 59 | 85 | 144 |
| | **SUB TOTAL** | | | | **15** | **14** | **29** | **48** | **46** | **94** | **59** | **62** | **121** | **122** | **122** | **244** |
| CBE | Accounting and Finance | | | | 33 | 19 | 52 | 39 | 32 | 71 | 112 | 123 | 235 | 184 | 174 | 358 |
| | Management | 16 | 15 | 31 | | | | 14 | 13 | 27 | 28 | 29 | 57 | 58 | 57 | 115 |
| | **SUB TOTAL** | **16** | **15** | **31** | **33** | **19** | **52** | **53** | **45** | **98** | **140** | **152** | **292** | **242** | **231** | **473** |
| **TOTAL** | | **60** | **42** | **102** | **76** | **35** | **111** | **156** | **106** | **262** | **232** | **216** | **448** | **524** | **399** | **923** |

በ2006 ክረምት ላይ በክረምት መርሃግብር በመማር ላይ የነበሩት የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ደግሞ በድምሩ 2320 (1757 ወንድ እና 563 ሴት ተማሪዎች) ናቸው (ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል)። በክረምት መርሃግብር በመማር ላይ ከሚገኙት ተማሪዎች ውስጥ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በራሳቸው ወጪውን በመሸፈን የሚማሩ ሲሆን በርካታዎቹ ደግሞ በላካቸው አካል (በመንግስት) ወጪያቸው የሚሸፈንላቸው ናቸው። በ2006 ክረምት ላይ ከተጀመሩት ፕሮግራሞች አንዱ ከትግራይ ክልል የቴክኒክና ሞያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ጋር በመተባበር የተጀመረው **የቴክኖሎጂ ባችለር ዲግሪ (BTech)** ትምህርት ነው። በክልሉ በሚገኙት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኮሌጆች ከባችለር ዲግሪ ደረጃ በታች ኖሯቸው በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን አስፈላጊውን ትምህርት በመስጠት ወደ ዲግሪ ደረጃ እንዲያድጉ ለማድረግ በተደረሰው ስምምነት መሰረት የፌደራል ቴክኒክና ሞያ ኤጀንሲ ሃላፊዎች፤ የኮሌጆቹ መምህራን፤ እና የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ መምህራን በተሳተፉበት መልኩ ካሪከለሞች እንዲዘጋጁ ተደርገው ባለፈው ክረምት የማስተማር ስራው ተጀምሯል። የማስተማር ስራው በአራት ኮሌጆችና በ13 የትምህርት ፕሮግራሞች በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን በነዚህ ፕሮግራሞች በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ደግሞ 1168 ነው። የተዘጋጀው ካሪከለም በዋናነት የቴክኖሎጂ ኤክስፐርቶች ወይም **ቴክኖሎጂስቶች** (Technologists) ለማምረት የተዘጋጀ ስለሆን በአብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች የሚሰጠው ትምህርት የቴክኖሎጂ ባችለር (Bachellor of Technology ወይም BTech) ዲግሪ የሚያስገኝ ይሆናል። ሌላው እና ከትምህርት ሚኒስቴር በመተባበር ባለፈው ክረምት የተጀመረው የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ፕሮግራም (Post Graduate Diploma Program – PGDT) ነው። በዚህ ፕሮግራም ስር በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተፈላጊው የትምህርት ደረጃ (የመጀመርያ ዲግሪ) በማሟላት በሁለተኛ ደረጃ በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን በተማሪነት የሚሳተፉበት ሆኖ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ፕሮግራሙን በመከታተል ላይ ናቸው። የዚህ ፕሮግራም አላማ መምህራኖቹ የማስተማር ክህሎት እንዲያዳብሩ መሰረት ያደረገ ሲሆን ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ (Post Graduate Diploma) የሚያገኙበት ነው።

ሰንጠረዥ 9፡ የክረምት ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች (2006 ክረምት)

| College | Department | Summer I | | | | | | | | | Summer II | | | | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | TEVT /Regional offices Sponsored | | | MoE sponsored | | | Self sponsored | | | Tigray Regional Bureau sponsored | | | Self sponsored | | | Total | | |
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| | Construction technology | 244 | 66 | 310 | | | 0 | 19 | 1 | 20 | | | 0 | | | 0 | 263 | 67 | 330 |
| | IT(PGDT) | | | 0 | 19 | 5 | 24 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 19 | 5 | 24 |
| | IT(TVET) | 136 | 44 | 180 | 0 | 0 | 0 | 28 | 13 | 41 | 77 | 44 | 121 | 33 | 7 | 40 | 274 | 108 | 382 |
| | B.TECH(TVET) | 22 | 10 | 32 | | | 0 | 14 | 1 | 15 | | | 0 | | | 0 | 36 | 11 | 47 |
| | Manufacturing Tech | 96 | 5 | 101 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 96 | 5 | 101 |
| | Wood Sicence | 76 | 11 | 87 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 76 | 11 | 87 |
| | Electrical Engineering | 48 | 6 | 54 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 48 | 6 | 54 |
| | Aouthomotive | 16 | 3 | 19 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 16 | 3 | 19 |
| | Technical Drawing | | | 0 | 99 | 12 | 111 | 12 | 1 | 13 | 57 | 12 | 69 | 11 | 1 | 12 | 179 | 26 | 205 |
| | Surveying | 13 | 6 | 19 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 13 | 6 | 19 |
| CET | **Subtotal** | **651** | **151** | **802** | **118** | **17** | **135** | **73** | **16** | **89** | **134** | **56** | **190** | **44** | **8** | **52** | **1020** | **248** | **1268** |
| | Biology | | | 0 | 67 | 54 | 121 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 67 | 54 | 121 |
| | Chemistry | | | 0 | 80 | 31 | 111 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 80 | 31 | 111 |
| | Mathematics | | | 0 | 43 | 15 | 58 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 43 | 15 | 58 |
| | HPE | | | 0 | 47 | 16 | 63 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 47 | 16 | 63 |
| | Physics | | | 0 | 33 | 8 | 41 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 33 | 8 | 41 |
| CNCS | **Subtotal** | **0** | **0** | **0** | **270** | **124** | **394** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **270** | **124** | **394** |
| | HO | 25 | 2 | 27 | | | 0 | 6 | 0 | 6 | | | 0 | | | 0 | 31 | 2 | 33 |
| | Nursing | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 27 | 21 | 48 | | | 0 | 27 | 21 | 48 |
| CMHS | **Subtotal** | **25** | **2** | **27** | **0** | **0** | **0** | **6** | **0** | **6** | **27** | **21** | **48** | **0** | **0** | **0** | **58** | **23** | **81** |
| | Animal science | 99 | 35 | 134 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 99 | 35 | 134 |
| CAES | Plant science | 75 | 12 | 87 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 75 | 12 | 87 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **Subtotal** | **174** | **47** | **221** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **174** | **47** | **221** |
| | Accounting and finance | 31 | 16 | 47 | | | 0 | 68 | 37 | 105 | | | 0 | | | 0 | 99 | 53 | 152 |
| | Management | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 26 | 7 | 33 | 26 | 7 | 33 |
| | Marketing | 44 | 27 | 71 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 44 | 27 | 71 |
| CBE | **Subtotal** | **75** | **43** | **118** | **0** | **0** | **0** | **68** | **37** | **105** | **0** | **0** | **0** | **26** | **7** | **33** | **169** | **87** | **256** |
| | Civics and ethical education | | | 0 | 28 | 8 | 36 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 28 | 8 | 36 |
| | Geograpy | | | 0 | 17 | 16 | 33 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 17 | 16 | 33 |
| CSSH | English | | | 0 | 21 | 10 | 31 | | | 0 | | | 0 | | | 0 | 21 | 10 | 31 |
| | **Subtotal** | **0** | **0** | **0** | **66** | **34** | **100** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **0** | **66** | **34** | **100** |
| | **Total** | **925** | **243** | **1168** | **454** | **175** | **629** | **147** | **53** | **200** | **161** | **77** | **238** | **70** | **15** | **85** | **1757** | **563** | **2320** |

ሰንጠረዥ 10. የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (ሁለተኛ ሰሚስተር)

| ፕሮግራም | መደበኛ | | | የማታ ኤክስቴንሽን | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| አካውንቲንግና ፋይናንስ (Master of Accounting and Finance) | 3 | 1 | 4 | 17 | 5 | 22 | 20 | 6 | 26 |
| የቢዝነስ አስተዳደር ማስትሬት (MBA) | 9 | | 9 | 70 | 3 | 73 | 79 | 3 | 82 |
| ድምር | 12 | 1 | 13 | 87 | 8 | 95 | 99 | 9 | 108 |

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በ2006 አስፈላጊውን የካሪክለም ዝግጅት በማድረግ በ2007 የትምህርት ዘመን የድህረ ምረቃ ትምህርት በሁለት ፕሮግራሞች ማለትም በአካውንቲንና ፋይናንስ እና በቢዝነስ አስተዳደር ጀምሯል። የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞቹ የተጀመሩት በመደበኛ እና በማታ ተከታታይ መርሃ ግብሮች ሲሆን በ2007 አንደኛ ሰሚስተር በመደበኛው 14 ተማሪዎች እና በማታ ተከታታይ መርሃ ግብሩ ደግሞ 106 ተማሪዎች በድምሩ 116 ተማሪዎች እየተማሩ ነበር። ከላይ በተቀመጠው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በሁለተኛ ሰሚስተር በድህረ ምረቃ ፕሮግራማችን ተመዝግበው ትምህርታቸውን የተከታተሉት ደግሞ በድምሩ 108 (99 ወንዶችና 9 ሴቶች) ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በመደበኛው ፕሮግራም 13 በማታ ተከታታይ ደግሞ 95 ናቸው። በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩት ተማሪዎች ውስጥ 8 የሚሆኑት በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ናቸው።

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ፕሮግራሞች ያሉት የተማሪዎች ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ የቀረበ ሲሆን በድምሩ **14300** ተማሪዎች (8704 ወንድ ወይም 60.87% እና 5596 ሴት ወይም 39.13%) አሉት።

ሰንጠረዥ 11. የዩኒቨርሰቲው ጠቅላላ ተማሪዎች ብዛት

| ፕሮግራም | ቅድመ ምረቃ | | | ድህረ ምረቃ | | | **ድምር** | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | **ወ** | **ሴ** | **ድ** |
| መደበኛ | 5875 | 4152 | 10027 | 12 | 1 | 13 | **5887** | **4153** | **10040** |
| ማታ ተከታታይ | 524 | 399 | 923 | 87 | 8 | 95 | **611** | **407** | **1018** |
| ክረምት ተከታታይ | 1757 | 563 | 2320 | | | | **1757** | **563** | **2320** |
| ድምር | 8156 | 5114 | 13270 | 99 | 9 | 108 | **8255** | **5123** | **13378** |
| መቶኛ | | | 99.19 | | | 0.81 | **61.71** | **38.29** | **100** |

## 2.2 የአካዳሚክ ሰራተኞች

ዩኒቨርሲቲው በድምሩ 661 መምህራን ያሉት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ መምህራን 450፤ በስራ ላይ ያሉት የውጭ መምህራን 43 (በድምሩ **በስራ ላይ ያሉ መምህራን 493**)፤ እና በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት ትምህርት ላይ ያሉት መምህራን ደግሞ 168 ነው። በ2006 ከነበረው የመምህራን ብዛት (ማለትም 413) ዘንድሮ ያለው የመምህራን ቁጥር በ248 ብልጫ አለው። ይህም ማለት በ2007 ውስጥ 248 ተጨማሪ መምህራን በምደባ፤ በዝውውርና በቅጥር (የውጭ መምህራንም ቅጥርም ጭምር) እንዲጨመሩ ተደርገዋል ማለት ነው። በትምህርት ላይ ካሉት መምህራን ውስጥ 129 ያህሉ ለሁለተኛ ዲግሪ በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን 39 ደግሞ የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በመማር ላይ የሚገኙበት አገር በተመለከተ ደግሞ 12 መምህራን በውጭ አገር (1 ኬንያ፤ 8 ህንድ፤ 1 ታይዋን፤ 1 ደቡብ አፍሪካ፤ 1 ኮርያ) በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ አገር ውስጥ በመማር ላይ ይገኛሉ። በአገር ውስጥ በመማር ላይ ከሚገኙት ውስጥ 14 መምህራን በዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በመማር ላይ የሚገኙት ናቸው።

በሚከተለው ሰንጠረዥ እንደሚታየው በዩኒቨርሲቲው በስራ ላይ ያሉት የአገር ውስጥ አካዳሚክ ሰራተኞች ውስጥ 36 (8%) የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ፤ 173 (38.4%) የመጀመርያ ዲግሪ ያላቸው

ደጋፊ መምህራን፤ 235 (52.2%) የሚሆኑት ደግሞ በሌክቸረር መአርግ የሚገኙ መምህራን፤ እና የተቀሩት 6 (1.3%) አሲስታንትና አሶሴት ፕሮፌሰር መአርግ ያላቸው ናቸው፡፡ የፆታ ስብጥር በተመለከተ ደግሞ በስራ ላይ ካሉት የአገር ውስጥ መምህራን 65 (14.4%) ሴት መምህራን ናቸው፡፡

በትምህርት ላይ ያሉት የአገር ውስጥ መምህራንን በመጨመር እና ጠቅላላ የዩኒቨርሲቲው የአገር ውስጥ መምህራን ሲወሰድ ደግሞ በድምሩ ያሉን የአገር ውስጥ የአካዳሚክ ሰራተኞች ቁጥር 618 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ቴክኒካል አሲስታንቶች 37 (6%)፤ በረዳት ምሩቅነትና ደጋፊ ሌክቸረር መአረግ ደረጃ ያሉት 302 (48.9%)፤ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ያሉን መምህራን 274 (44.3%) ሲሆኑ በሶስተኛ ዲግሪ ያሉ መምህራን ደግሞ 3 (0.48%) ናቸው፡፡ ሁሉም የአገር ውስጥ መምህራን (ስራ ላይ ያሉት እና ትምህርት ላይ ያሉትን) በመውሰድ የሚኖረው የፆታ ስብጥር ደግሞ ትምህርት ላይ ያሉ 20 ሴት መምህራን ስላሉ በአጠቃላይ 85 ሴት የአገር ውስጥ መምህራን በዩኒቨርሲቲው ይገኛሉ፡፡ በዚሁም መሰረት የሴት መምህራን ብዛት የጠቅላላው ብዛት 13.8% ነው፡፡

ሰንጠረዥ 12፤ ስራ ላይ ያሉ (የአገር ውስጥ) የአካዳሚክ ሰራተኞች በአካዳሚክ መአርግ

| | TAs | | | BA/BSC | | | MA/MSc/MD | | | A/Aso /Prof | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮሌጅ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ወ | ሴ | ድ |
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 13 | 6 | 19 | 90 | 20 | 110 | 31 | 2 | 33 | 0 | 134 | 28 | 162 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 10 | 0 | 10 | 11 | 1 | 12 | 62 | 4 | 66 | 1 | 84 | 5 | 89 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 2 | 0 | 2 | 17 | 6 | 23 | 32 | 4 | 36 | 0 | 51 | 10 | 61 |
| ግብርናና አከባብያዊ ሳይንስ | 4 | 0 | 4 | 0 | 0 | 0 | 18 | 3 | 21 | 3 | 25 | 3 | 28 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 25 | 3 | 28 | 2 | 27 | 4 | 31 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | 0 | 0 | 0 | 18 | 10 | 28 | 46 | 5 | 51 | 0 | 64 | 15 | 79 |
| **ድምር** | **29** | **7** | **36** | **136** | **37** | **173** | **215** | **21** | **235** | **6** | **385** | **65** | **450** |
| መቶኛ | 6.4 | 1.6 | 8 | 30.2 | 8.2 | 38.4 | 47.8 | 4.7 | 52.2 | 1.3 | 86 | 14.4 | 100 |

ቀደም ብሎ የተቀመጠው የተማሪዎች ብዛትና ከላይ የተመለከተው የመምህራን ብዛት በመጠቀም **የመምህር–ተማሪ ጥምርታ** ወይም Teacher-Student Ratio ማስላት ይቻላል፡፡ በዚሁም መሰረት፤

1. በስራ ላይ ያሉት መምህራን (የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር) ቁጥር 493 ስለሆነ እነዚህን መምህራን እና መደበኛ ተማሪዎችን (የቅድመ ምረቃ 10027 እና የድህረ ምረቃ 13 በድምሩ 10040) በመውሰድ ነገር ግን 36 የቴክኒክ ደጋፊዎችን (Technical Assistants) ሳንጨምር በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያለው የመምህር–ተማሪ ጥምርታ (Teacher-Student Ratio) 21.97 ነው፡፡ በእድገትና ትራንስፎርሜሽኝ እቅድ የተያዘው የመምህር ተማሪ ጥምርታ ግብ 1:20 ሲሆን ዩኒቨርሲቲው አሁን የደረሰበት ግን 1:22 ነው፡፡
2. በስራ ላይ ያሉት መምህራን (የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎችን ጨምሮ) ከወሰድን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያለው የመምህር–ተማሪ ጥምርታ 20.37 ነው፡፡
3. ከቴክኒክ ደጋፊዎች ውጭ ያሉትን መምህራን በሙሉ (ስራ ላይ ያሉ እና ትምህርት ላይ ያሉ) እና መደበኛ ተማሪዎች በመውሰድ የሚኖረው የመምህር–ተማሪ ጥምርታ 16.1 ነው፡፡
4. በተራ ቁጥር 3 በተቀመጠው የመምህራን ቁጥር የቴክኒክ ደጋፊዎችን ስንጨምርበት የሚኖረው የመምህር–ተማሪ ጥምርታ 15.19 ይሆናል፡፡
5. ጠቅላላ የአካዳሚክ ሰራተኞች (በስራ ላይ እና በትምህርት ላይ ያሉት የቴክኒክ ደጋፊዎችን ጨምሮ በመጠቀም – ማለትም 661 የአካዳሚክ ሰራተኞች) በመጠቀም እና ጠቅላላ የተማሪዎችን ቁጥር (መደበኛ፤ ማታ ተከታታይ እና ክረምት ተከታታይ – ቅድመ እና ድህረ ምረቃ– በድምሩ 13378) በመጠቀም ያለው የመምህራን–ተማሪ ጥምርታ ደግሞ 20.23 ነው፡፡

ሰንጠረዥ 13፤ ስራ ላይ ያሉ የአገር ውስጥ መምህራን ብዛት (ሰኔ 2007)

| College | Department | Technical Assistants | | | BA/BSC (Assts.) | | | MA/MSc (Lect.) | | | PhD | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | Total | M | M | F | T |
| Engineering | Electrical Engineering | 4 | 0 | 4 | 11 | 2 | 13 | 9 | 1 | 10 | 0 | 24 | 3 | 27 |
| | Mechanical Engineering | 3 | 0 | 3 | 12 | 3 | 15 | 6 | 0 | 6 | 0 | 21 | 3 | 24 |
| | Chemical Engineering | 0 | 0 | 0 | 9 | 1 | 10 | 3 | 0 | 3 | 0 | 12 | 1 | 13 |
| | Civil Engineering | 5 | 4 | 9 | 37 | 10 | 47 | 6 | 1 | 7 | 0 | 48 | 15 | 63 |
| | Computer Science | 1 | 0 | 1 | 9 | 2 | 11 | 6 | 0 | 6 | 0 | 16 | 2 | 18 |
| | Construction Technology | 0 | 2 | 2 | 8 | 0 | 8 | 1 | 0 | 1 | 0 | 9 | 2 | 11 |
| | Archticture Engineering | 0 | 0 | 0 | 4 | 2 | 6 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 2 | 6 |
| | **Sub Total** | **13** | **6** | **19** | **90** | **20** | **110** | **31** | **2** | **33** | **0** | **134** | **28** | **162** |
| Natural and Computational Sciences | Biology | 2 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 7 | 1 | 8 | 0 | 9 | 1 | 10 |
| | Chemistry | 4 | 0 | 4 | 0 | 0 | 0 | 14 | 0 | 14 | 0 | 18 | 0 | 18 |
| | Mathematics | 0 | 0 | 0 | 2 | 0 | 2 | 26 | 2 | 28 | 0 | 28 | 2 | 30 |
| | Physics | 2 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 7 | 1 | 8 | 1 | 10 | 1 | 11 |
| | Statistics | 1 | 0 | 1 | 6 | 0 | 6 | 3 | 0 | 3 | 0 | 10 | 0 | 10 |
| | Geology | 0 | 0 | 0 | 3 | 1 | 4 | 1 | 0 | 1 | 0 | 4 | 1 | 5 |
| | Sport Science | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 4 | 0 | 4 | 0 | 5 | 0 | 5 |
| | **Sub Total** | **10** | **0** | **10** | **11** | **1** | **12** | **62** | **4** | **66** | **1** | **84** | **5** | **89** |
| Business and Economics | Accounting and Finance | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 7 | 1 | 8 | 0 | 7 | 1 | 8 |
| | Economics | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 8 | 1 | 9 | 1 | 9 | 2 | 11 |
| | Management | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 9 | 1 | 10 | 0 | 9 | 1 | 10 |
| | Marketing | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 0 | 2 | 0 | 2 | 0 | 2 |
| | **Sub Total** | **0** | **1** | **1** | **0** | **0** | **0** | **26** | **3** | **29** | **1** | **27** | **4** | **31** |
| Social Sciences and Humanities | English | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 22 | 2 | 24 | 0 | 22 | 2 | 24 |
| | Tigrgna and Tiatrical art | 0 | 0 | 0 | 4 | 2 | 6 | 2 | 0 | 2 | 0 | 6 | 2 | 8 |
| | Civics | 0 | 0 | 0 | 10 | 2 | 12 | 5 | 0 | 5 | 0 | 15 | 2 | 17 |
| | Psychology | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 2 | 7 | 0 | 7 | 0 | 7 | 2 | 9 |
| | Geography and Environmental Stdies | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 | 1 | 6 | 0 | 5 | 1 | 6 |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Law | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 2 | 3 | 1 | 4 | 0 | 4 | 2 | 6 |
| | arckeology | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 2 | 0 | 2 | 1 | 3 |
| | Sociology | 0 | 0 | 0 | 2 | 3 | 5 | 1 | 0 | 1 | 0 | 3 | 3 | 6 |
| | **Subtotal** | **0** | **0** | **0** | **18** | **10** | **28** | **46** | **5** | **51** | **0** | **64** | **15** | **79** |
| **Agriculture and Environmental Science** | Natural Resource Management (SWC) | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 5 | 2 | 7 | 0 | 6 | 2 | 8 |
| | Animal Science | 2 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 6 | 1 | 7 | 3 | 11 | 1 | 12 |
| | Plant Science | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 7 | 0 | 7 | 0 | 8 | 0 | 8 |
| | **Subtotal** | **4** | **0** | **4** | **0** | **0** | **0** | **18** | **3** | **21** | **3** | **25** | **3** | **28** |
| **Health and Meidical Sciences** | Nursing | 1 | 0 | 1 | 2 | 1 | 3 | 4 | 0 | 4 | 0 | 7 | 1 | 8 |
| | pharmacy | 0 | 0 | 0 | 7 | 0 | 7 | 0 | 0 | 0 | 0 | 7 | 0 | 7 |
| | Midwifery | 0 | 0 | 0 | 3 | 3 | 6 | 1 | 0 | 1 | 0 | 4 | 3 | 7 |
| | Public Health | 0 | 0 | 0 | 0 | 2 | 2 | 7 | 0 | 7 | 0 | 7 | 2 | 9 |
| | Biomedical | 1 | 0 | 1 | 5 | 0 | 5 | 4 | 1 | 5 | 0 | 10 | 1 | 11 |
| | Medicine | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 16 | 3 | 19 | 0 | 16 | 3 | 19 |
| | **Subtotal** | **2** | **0** | **2** | **17** | **6** | **23** | **32** | **4** | **36** | **0** | **51** | **10** | **61** |
| **Overall Total** | | **29** | **7** | **36** | **136** | **37** | **173** | **215** | **21** | **236** | **5** | **385** | **65** | **450** |

ከአገር ውስጥ መምህራን በተጨማሪ 43 የውጭ ሃገር መምህራን በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ 40ዎቹ የህንድ ዜግነት ያላቸው፤ ሁለቱ የፊሊፒንስ መምህራን ሲሆኑ አንዱ ደግሞ የጀርመን ዜጋ ናቸው። ከውጭ ሃገር ያስመጣናቸው መምህራን ያለንን ክፍተት (የመምህራን እጥረት ባለብን የትምህርት መስኮች በዋናነት ኢንጂነሪንግና ህክምና) ለመሸፈን እና ወደ ትምህርት የላክናቸውን መምህራን ለመተካት ድጋፍ የሚሰጡን ናቸው። ከዚሁም በተጨማሪ በተቻለ መጠን በያንዳንዱ የትምህርት ክፍል አንድ ሶስተኛ ዲግሪ ያለው ባለሞያ እንዲኖረን በማድረግ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት ለመጀመር ጠቃሚ ግብአት ይሆናሉ የሚል ታሳቢም ይወሰዳል። በየኮሌጁ ያለው የውጭ ሃገር መምህራን ስርጭት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 14. የውጭ መምህራን

| ኪሌጅ | ሌክቸረር | | | ረ/ተ/ፕሮፌሰር | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ኢንጂነሪንግ | 3 | | 3 | 9 | | 9 | 12 | | 12 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 1 | | 1 | 7 | | 7 | 8 | | 8 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 2 | 2 | 4 | 2 | | 2 | 4 | 2 | 6 |
| ግብርና እና አከባቢያዊ ሳይንስ | | | | | | | | | |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 2 | 1 | 3 | 6 | | 6 | 8 | 1 | 9 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | | 1 | 1 | 7 | | 7 | 7 | 1 | 8 |
| **ድምር** | 8 | 4 | 12 | 31 | | 31 | 39 | 4 | 43 |

### 2.3 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

በ2006 ዩኒቨርሲቲው የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 974 (928 ቋሚ እና 46 የኮንትራት) ሲሆን በ2007 ያሉን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 1179 (ማለትም 1144 ቋሚ –ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት የተላኩ ናቸው– እና 35 የኮንትራት) ደርሷል። በዚህም መሰረት በ2007 ያሉን የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በ2006 ከነበሩን የ205 ብልጫ ያሳያል። በ2004 መጨረሻ ላይ ተዘጋጅቶ የነበረው የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መዋቅር ለሶስት አመታት እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነበር። በዚሁ መዋቅር የተፈቀደው የሰራተኛ ብዛት 1186 የነበረ ቢሆንም ከዚሁም በተጨማሪ በየጊዜው እያስፈቀድን ተጨማሪ የስራ ቦታዎች ተፈቅደውልን ሰራተኞች እንዲቀጠሩ አድርገናል። ዩኒቨርሲቲው ካደረገው መስፋፋት ጋር ተያይዞ በተለይም በምግብ ቤት አከባቢ፤ በተማሪዎች መኝታ ቤት አከባቢ (ፕሮክተሮች)፤ በረጂስትራር፤ በሾፌሮች እና በሌሎች ክፍሎች ተፈቅዶልን በነበረው መዋቅር ያልተካተቱ የስራ መደቦችና ሰራተኞች ስለነበሩ ተጨማሪ የሰራተኞች ቁጥር እንዲፈቀድልን ጠይቀን ተጨማሪ ቅጥሮችን አካሂደናል።

እስከ ሰኔ 2007 ድረስ በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረገዦች የተመለከተውን ይመስላል። ይህ ቁጥር የፅዳት ስራው ወደ ውጭ በመውጣቱ ምክንያት (outsource) በከተማው ትምህርት ጨርሰው ለተደራጁት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋም በጨረታ እንዲሰጥ ስለተደረገ፤ በተጨማሪም የቆሻሻ ማስወገድ ስራም በተመሳሳይ መልኩ ወደ ውጭ ስለወጣ በነዚህ ስራዎች በመስራት ላይ የሚገኙት ሰራተኞች በዩኒቨርሲቲው የሰራተኞች አሃዝ የተካተተ አይደለም።

ሰንጠረዥ 15. ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | ፅህፈት ቤት | ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ፕረዚደንት ፅ/ቤት | | 3 | 3 |
| 2 | እቅድና ተቋማዊ ማሻሻያ ፅ/ቤት | 1 | 2 | 3 |
| 3 | ሕዝብና የውጭ ግንኙነት ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 4 | ውስጥ ኦዲት ፅ/ቤት | 2 | 3 | 5 |
| 5 | ስርአተ ፆታ ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 6 | ህግ አገልግሎት ፅ/ቤት | 2 | 2 | 4 |
| 7 | ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት | 1 | 1 | 2 |
| 8 | አካዳሚክና ምርምር ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 1 | 1 | 2 |
| 9 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ | | 6 | 6 |
| 10 | ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ | | 9 | 9 |
| 11 | ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ | 2 | 9 | 11 |
| 12 | ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ | | 8 | 8 |
| 13 | ግብርና ኮሌጅ | | 5 | 5 |
| 14 | ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | | 5 | 5 |
| 15 | ሬጂስትራር | 5 | 22 | 27 |
| 16 | ቤተመፃህፍትና ዶኩመንቴሽን | 87 | 100 | 187 |
| 17 | ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ማእከል | 4 | 2 | 6 |
| 18 | አስተዳደርና ልማት ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | | 2 | 2 |
| 19 | ሰው ሃብት ልማት ማእከል | 8 | 8 | 16 |
| 20 | ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 14 | 10 | 24 |
| 21 | ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 10 | 10 | 20 |
| 22 | መሰረታዊ አገልግሎት ማእከል | 166 | 25 | 191 |
| 23 | የተማሪዎች ዲን ፅ/ቤት | 3 | 2 | 5 |
| 24 | የተማሪዎች መኝታ ቤትና መዝናኛ አገልግሎት | 37 | 31 | 68 |
| 25 | ተማሪዎች ዲን (ምግብ ቤት ሰራተኞች) | 54 | 453 | 507 |
| 26 | ተማሪዎች ዲን (ክሊኒክ ሰራተኞች) | 9 | 7 | 16 |
| 27 | ዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር | | 1 | 1 |
| 28 | ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት | | 1 | 1 |
| 29 | ጥራት ማረጋገጫ | | 2 | 2 |
| | ድምር | 409 | 732 | 1142 |

ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ እንደሚታየው ዩኒቨርሲቲው ሰኔ 2007 በስራ ላይ የነበሩት ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 1142 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ በጣም አብዛኛዎቹ (ማለትም 507 የሚሆኑት ወይም 44.4%) በምግብ ቤት አከባቢ በመስራት ላይ የሚገኙ ናቸው። ከዚሁም በተጨማሪ ሁለት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ለድህረ ምረቃ አዲስ አበባ ትምህርት ላይ የሚገኙ ስለሆነ ጠቅላላ ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት 1144 ነው። የፆታ ስብጥር በተመለከተ ደግሞ ካሉን ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ውስጥ አብዛኛዎቹ ማለትም 64% ሴት ሰራተኞች ናቸው።

ሰንጠረዥ 16፤ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | አይነት | የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት | 14 | 2 | 16 |
| 2 | ፕሮክተር | 2 | 2 | 4 |
| 3 | ጥበቃ | 11 | | 11 |
| 4 | ጀነሬተር ኦፕሬተር | 1 | | 1 |
| 5 | ሾፌር | 2 | | 2 |
| 6 | ግብርና ኮሌጅ | 1 | | 1 |
| **ድምር** | | 31 | 4 | 35 |

የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ጨምሮ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ እስከ ሰኔ 2007 ድረስ የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች (በትምህርት ላይ ያሉትን ጨምሮ) ቁጥር 1179 ነው፡፡ በፆታ ስብጥር ሲታይ ደግሞ ከጠቅላላው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ውስጥ 62.4% ሴት ሰራተኞች ናቸው፡፡

## 3. ለ2007 የተፈቀደልን ባጀትና አጠቃቀሙ

ዩኒቨርሲቲው ለ2007 የሚያስፈልገውን ባጀት በ2006 ላይ ካቀረበ በኋላ የጠየቀውን ያህል ባይሆንም ለ2007 የሚሆን የመደበኛና የካፒታል ባጀት ተመድቦለት በእቅድ ያስቀመጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ችሏል፡፡ እስከ ሰኔ 30 የነበረው የአመቱ የባጀት አጠቃቀም እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

### 3.1. መደበኛ ባጀት

የ2007 የስራ ዘመን በሚጀመርበት ወቅት በድምሩ ለመደበኛ ባጀት ተፈቅዶልን የነበረው ብር 195485710 የነበረ ቢሆንም የደምወዝ ጭማሪ ማስተካከያ በመደረጉ ምክንያት ለአመቱ ተስተካክሎ የተፈቀደልን የመደበኛ ባጀት ድምር ብር 228038160 ነው፡፡ ተስተካክሎ የተፈቀደልን መደበኛ ባጀት በፕሮግራም ባጀት አደላደል መሰረት ለአራት ፕሮግራሞች ማለትም ለፕሮግራም አንድ ወይም ለአስተዳደር ስራዎች (120884730)፤ ለፕሮግራም ሁለት ወይም አካዳሚክ ነክ ስራዎች (101857230)፤ ለፕሮግራም ሶስት ወይም ለጥናትና ምርምር (4116200)፤ እና ለፕሮግራም አራት ወይም ለማህበረሰብ አገልግሎት (1180000) በድምሩ ብር 228038160 ተመድቦልናል፡፡ ለ2006 ተፈቅዶልን ከነበረ መደበኛ ባጀት (ማለትም 117156060) ጋር ሲነፃፀር የ2007 መደበኛ ባጀት በ110882100 ብር ብልጫ ያለው ነው፡፡ ይህም ማለት የ2007 ባጀት በ2006 ከነበረው በ 94% ብልጫ ያለው ነው፡፡ ከታች በሚገኙት ሰንጠረገች በዝርዝረ እንደተመለከተው እስከ ሰኔ 30/2007 የነበረው የመደበኛ ባጀት አጠቃቀም ከተፈቀደልን አንፃር ሲወዳደር እና በመቶኛ ሲቀመጥ 97.18% ነው፡፡ በሌላ አቀማመጥ ተስተካክሎ ከተፈቀደልን ባጀት ውስጥ ብር 221597226.52 ወጪ አድርገን ብር 6440933.48 ከወጪ ቀሪ ሆኗል፡፡ በርግጥ ከወጪ ቀሪ የሆነውም ቢሆን በቅድመ ክፍያ መልክ እንዲከፈል የተደረገ ነው፡፡ ስለዚህ የአመቱ የባጀት አጠቃቀም አጥጋቢ በሆነ መልኩ ተከናውኗል ማለት ይቻላል፡፡

መደበኛ ባጀቱ የሚመደበው ለደምወዝ፤ ለእቃዎችና አገልግሎት ግዥዎች እና ለሌሎች ተመሳሳይ ወጪዎች ሲሆን ግዥዎችን በተመለከተ በግልፅ ጨረታዎች (ሰባት ግልፅ ጨረታዎች)፤ በውሱን ጨረታዎች፤ በፕሮፎርማ፤ በለቀማ እና በቀጥታ ግዥዎች በመጠቀም የተለያዩ ግዥዎች ተከናውነዋል፡፡ 5000 ያህል አዲስ ተማሪዎችን በ2007 ለመቀበል በያዝነው እቅድ መሰረት ለነዚህ ተማሪዎች የሚሆኑ የተለያዩ ማቴርያሎች ማለትም አልጋ፤ ወንበር፤ ፍራሽ፤ ሎከር፤ ወዘተ እንዲሁም አዲስ ለተቀጠሩና ለነባር ሰራተኞች የሚሆኑ ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ወንበሮች፤ ጠረጴዛዎች፤ እና ሌሎች ማቴርያሎች፤ በተጨማሪም ለማስተማርያ እና ቢሮ አገልግሎት የሚውሉ

ቁሳቁሶች (ወረቀት፤ ፤ ማርከር፤ መፃህፍት ወዘተ)፤ እና ለተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት የሚውሉ የምግብ ግብአቶች እና መሳርያዎች ግዥዎች ተከናውነዋል።

ከተደረጉት በርካታ ግዥዎች ሁለት ነገሮች እንደአብነት መጥቀስ ይቻላል፤ የመፃህፍትና የትራክተር ግዥ። መፃህፍትን በተመለከተ ዘንድሮ በጨረታ እና በለቀማ በርከት ያሉ መፃህፍትን ለመግዛት በመቻላችን በመፃህፍት እጥረት በኩል የነበረው ችግር እንዲቃለል ተደርጓል። በጨረታ የአስር ሚልዮን ያህል በለቀማ ደግሞ የ2.9 ሚልዮን **በድምሩ የአስራ ሶስት ሚልዮን መፃህፍት** ገዝተናል። ሌላው በጥሩ ሊወሳ የሚችለው የትራክተር ግዥ ነው። የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርንና (ምክንያቱም ተሽከርካሪ በራሳችን መግዛት ስለማይፈቀድልን) የግዥና ንብረት አገልግሎት ኤጀንሲን በማስፈቀድ በፕሮፎርማ መልክ ትራክተር እስከነ ሙሉ ደጋፊ መሳርያዎቹ (ማረሻ፤ ተሳቢ፤ የውሃ ቦቴ) በ1.7 ሚልዮን ለመግዛት ችለናል። ሎሌችም በርካታ ግዥዎች ተከናውነዋል። ለዝርዝር እይታ ይረዳ ዘንድ በየባጀት አርእስቱ ያለው የመደበኛ ባጀት አጠቃቀም በየባጀት አርእስቱ በAppendix 3 እንዲቀመጥ ተደርጓል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ደግሞ በአመቱ የነበረው የባጀት አጠቃቀም በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረዦች የቀረበ ሲሆን የመደበኛ እና የካፒታል ባጀት ባጠቃለለ መልኩ የነበረን የባጀት አጠቃቀም 95.78% (አጥጋቢ) መሆኑን ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 17፤ የመደበኛና ካፒታል ባጀት አጠቃቀም ማጠቃለያ (በባጀት አርእስት)

| የባጀት አይነት | የባጀት መደብ | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ ሰኔ 30 ወጪ የተደረገ | አጠቃቀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| መደበኛ ባጀት | 6100 | 86722680.00 | 85364130.21 | 98.43 |
| | 6200 | 103140260.00 | 99356813.66 | 96.33 |
| | 6300 | 36503190.00 | 35223390.68 | 96.49 |
| | 6400 | 1672030.00 | 1652891.97 | 98.86 |
| | **ንኡስ ድምር** | **228038160.00** | **221597226.52** | **97.18** |
| ካፒታል ባጀት | 6100 | 17100000.00 | 17098429.74 | 99.99 |
| | 6200 | 5211700.00 | 4628217.16 | 88.80 |
| | 6300 | 311844220.00 | 295125709.12 | 94.64 |
| | 6400 | 0.00 | 0.00 | |
| | **ንኡስ ድምር** | **334155920.00** | **316852356.02** | **94.82** |
| **ድምር** | | **562194080.00** | **538449582.54** | **95.78** |

ሰንጠረዥ 18፤ የመደበኛና ካፒታል ባጀት አጠቃቀም ማጠቃለያ (በፕሮግራም)

| የባጀት አይነት | ፕሮግራም | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ ሰኔ 30 የተጠቀምንበት | አጠቃቀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| መደበኛ ባጀት | ፕሮግራም አንድ (392-01-01-00): አስተዳደር | 120884730 | 117546337.7 | 97.24 |
| | ፕሮግራም ሁለት (392-02-01-00): አካዳሚ | 101857230 | 99450319.08 | 97.64 |
| | ፕሮግራም ሶስት (392-03-01-00): ምርምር | 4116200 | 3624142.37 | 88.05 |
| | ፕሮግራም አራት (392-04-01-00): ማህበረሰብ አገልግሎት | 1180000 | 976427.37 | 82.75 |
| | **ንኡስ ድምር** | **228038160** | **221597226.5** | **97.18** |
| ካፒታል ባጀት | ፕሮግራም አንድ (392-01-01-010-001) | 202683340.00 | 190600309.33 | 94.04 |
| | ፕሮግራም ሁለት (392-01-01- | 54593250.00 | 54293963.03 | 99.45 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 010-002) | | | |
| | ፕሮግራም ሶስት (392-01-01-010-003) | 21812980.00 | 20494575.62 | 93.96 |
| | ፕሮግራም አራት (392-01-01-010-004) | 40387410.00 | 37267834.28 | 92.28 |
| | ፕሮግራም አምስት (392-01-01-010-005) | 2153300.00 | 2023233.78 | 93.96 |
| | ፕሮግራም ስድስት (392-01-01-010-006) | 12525640.00 | 12172439.98 | 97.18 |
| | **ንኡስ ድምር** | 334155920.00 | 316852356.02 | 94.82 |
| **ድምር** | | 562194080.00 | 538449582.54 | 95.78 |

### 3.2. ካፒታል ባጀት

በካፒታል ባጀት ለሚከናወኑ ተግባራት የተፈቀደልን ገንዘብ ልክ እንደ መደበኛው ሁሉ በፕሮግራም ባጀት መልክ ለስድስት ፕሮግራሞች የተመደበ ነው። በዚሁም መሰረት ለየፕሮግራሙ ተስተካክሎ የተመደበልን ባጀት የሚከተለውን ይመስላል፤ ለፕሮግራም አንድ 202683340.00፤ ለፕሮግራም ሁለት 54593250.00፤ ለፕሮግራም ሶስት 21812980.00፤ ለፕሮግራም አራት 40387410.00፤ ለፕሮግራም አምስት 2153300.00 እና ለፕሮግራም ስድስት 12525640.00 ሆኖ በአጠቃላይ የተፈቀደልን የካፒታል ባጀት 334155920.00 ነው።

በ2006 መጀመርያ ላይ ተፈቅዶልን ከነበረው የብር 283943120 ባጀት ጋር ሲነፃፀር የ2007 ካፒታል ባጀት የ50212800 ወይም የ17.7% ብልጫ ያለው ቢሆንም በ2006 መጨረሻ ላይ ተጨማሪ የካፒታል ባጀት ተፈቅዶልን ስለነበረ እና በአመቱ ተስከካክሎ የተፈቀደልን የካፒታል ባጀት ብር 384300333.07 ስለነበር ተስተካክሎ ከተፈቀደው የ2006 ካፒታል ባጀት ጋር ሲነፃፀር የ2007 ካፒታል ባጀት በ **50144413.07 ብር የቀነሰ** ነው።

የአመቱ የካፒታል ባጀት አጠቃቀማችን በተመለከተ ደግሞ ከላይ ባሉት ሰንጠረዦች እና ከታች ባለው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው 94.82% መሆኑን ያሳያል። በሌላ አገላለፅ ከተመደበልን የካፒታል ባጀት ውስጥ 316.85 ሚልዮን በወጪ መልክ የተጠቀምንበት ሲሆን 17.3 ሚልዮን ደግሞ ከወጪ ቀሪ የሆነው ነው። በወጪነት ያልተከፈለው መጠንም ግን ለግንባታ ስራዎች በቅድመ ክፍያ እንዲከፈል የተደረገ ነው። ከአመቱ የካፒታል ባጀት አጠቃቀም (በየባጀት ርእሱ ያለው ዝርዝር አጠቃቀም በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል) መረዳት እንደሚቻለው በድምሩ አጥጋቢ እንደሆነ ሊቀመጥ ይችላል። ሆኖም አጠቃላይ አጠቃቀሙ አጥጋቢ ቢሆንም ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ግን ቀላል አልነበሩም። ካጋጠሙት ተግዳሮቶች ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

1. በሁለተኛው ግቢ ግንባታ በወቅቱ አለመጀመሩ፤ በ2007 በእቅድ ተይዘው ከነበሩት የግንባታ ስራዎች አንዱ በሁለተኛው ግቢ ግንባታዎችን (33 ብሎኮችን) ማከናወን የሚል ቢሆንም ስራው በወቅቱ ሊጀመር አልቻለም፤ በአመቱ መጨረሻ የግንባታ ስራዎች የተጀመሩ ቢሆንም። የዘገየበት ምክንያትም በአንድ በኩል ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ ያልተጣሩ ጉዳዮች ስለነበሩ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የአማካሪ ድርጅት በጨረታ መለየት ስለነበረበት እና ጨረታው ወጥቶ የመምረጡ ስራ እና የዲዛይን አዳፕቴሽን ስራ የራሱ ጊዜ ስለወሰደ ነው።
2. ለመምህራን መኖርያ ይሆናሉ ተብለው የተገዙት ያላለቁ የኮንደሚንየም ቤቶች ስራ በወቅቱ አለመጀመሩ፤ በ2007 የተያዘው ሌላው የግንባታ እቅድ ለመምህራን መኖርያ ይሆናሉ ተብለው የተገዙት ያልተጠናቀቁ የኮንደሚንየም ቤቶች (በ2006 የተገዙት) የርክክብ ስራ በማከናወን እና የተሻሻሉ የፊኒሺንግ ማቴርያሎችን ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ ማስተካከያ በማድረግ ግንባታ ማከናወን ነበር። በዚሁም መሰረት ርክክቡ ተጠናቆ የሚሻሻሉ ማቴርያሎች መረጣ ተደርጎ፤ የጨረታ ዶኩመንት ተዘጋጅቶ፤ ጨረታ ወጥቶ

አሸናፊዎች ተለይተው በአመቱ መጨረሻ አከባቢ ስራው የተጀመረ ቢሆንም የተጠቀሱት ስራዎች የራሳቸው ጊዜ ስለወሰዱ በተፈለገው ጊዜ ስራው ሊጀመር አልቻለም።

3. የፍሳሽ ማጣርያ (Waster Water Treatment) ስራ ከሚገባው በላይ መጓተቱ፤ የዚህ ስራ መጓተት ዋናው ምክንያት ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ በተነሱት ንትርኮች በቦታው የነበሩ ነዋሪዎች በታሰበው ጊዜ ሊነሱ አለመቻላቸው ነው። ጉዳዩ የዞኑና የወረዳውም አስተዳደር ድጋፍ ታክሎበት ከብዙ ጥረትና ክትትል በኋላ የተፈታ (እና ቆሞ የነበረው የግንባታ ስራ እንዲቀጥል የተደረገ) ቢሆንም ያስከተለው የስራ መጓተት ግን ከፍተኛ ነበር።
4. የዳታ ሰንተር ስራ በታቀደለት ጊዜ አለመጠናቀቅ፤ በዩኒቨርሰቲው የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የላቀ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ የታመነበት የዳታ ሰንተር እና ተያያዥ የኔትወርክ ተከላ በ2006 ጨረታ ወጥቶ አሸናፊው Huawe የተባለው ድርጅት እየሰራው ሲሆን በታሰበለት ጊዜ ሊጠናቀቅ አልቻለም። ባጠቃላይ ስራው በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ቢሆንም በአሸናፊው ድርጅት በኩል እና በዩኒቨርሲቲው በኩል በወቅቱ መቅረብ የነበረባቸው ማቴርያሎች ባለመቅረባቸው ምክንያት መዘግየት ታይቶበታል።

ሰንጠረዥ 19. ለ2007 የተፈቀደ ካፒታል ባጀት እና እስከ ሰኔ 30 ድረስ የነበረው አጠቃቀም

| የሂሳብ መደብ | መግለጫ | ጠቅላላ የተፈቀደ | ጠቅላላ ወጪ የተደረገ | ከወጪ ቀሪ | አጠቃቀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 6115 | ለውጭ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ | 17100000.00 | 17098429.74 | 1570.26 | 99.99 |
| 6231 | ለውሎ አበል | 15000.00 | 14838.40 | 161.60 | 98.92 |
| 6232 | ለትራንስፖርት ክፍያ | 730000.00 | 366955.52 | 363044.48 | 50.27 |
| 6233 | ለመስተንግዶ | 295400.00 | 83722.15 | 211677.85 | 28.34 |
| 6251 | በውል ለሚፈፀሙ የሙያ አገልግሎቶች | 4171300.00 | 4162701.09 | 8598.91 | 99.79 |
| 6313 | ለፕላንት ለማሽነሪና ለመሳርያ መግዣ | 42520700.00 | 42520700.00 | 0.00 | 100.00 |
| 6314 | ለህንፃ ለቁሳቁስ እና ተገጣጣሚዎች መግዣ | 12710100.00 | 12710100.00 | 0.00 | 100.00 |
| 6321 | ለቅድመ ግንባታ ስራዎች | 856700.00 | 844436.49 | 12263.51 | 98.57 |
| 6322 | ለመኖርያ ህንጻዎች ግንባታ | 67665550.00 | 67368763.06 | 296786.94 | 99.56 |
| 6323 | ለመኖርያ ያልሆኑ ህንጻዎች ግንባታ | 79396690.00 | 74544511.42 | 4852178.58 | 93.89 |
| 6324 | ለመሰረተ ልማት ግንባታ | 108694480.00 | 97137198.15 | 11557281.85 | 89.37 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **334155920** | **316852356** | **17303563.98** | 94.82 |

## 3.3. የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም

በአመቱ እቅድ በዝርዝር እንደተመለከተው ዩኒቨርሲቲው በ2007 በርካታ የግንባታ ስራዎችን ለማከናወን አስቀምጦ ነበር። በእቅዱ መሰረት በአንድ በኩል በ2006 ተጀምረው የነበሩት የግንባታ ስራዎች የሚጠናቀቁበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በ2007 አዳዲስ የሚጀመሩ በርካታ ስራዎች እንደሚኖሩ ያመለክታል። ቀደም ብለው ተጀምረው የነበሩ የሶስተኛ ዙር የግንባታ ስራዎች (በAppendix 4 የተመለከቱት ሆነው ከተራ ቁጥር 1 እስከ 17 ያሉት 25 ዋና ብሎኮች፣ 6 የልብስ ማጠብያ ብሎኮች እና ሶስት የስፖርት መጫወቻ ሜዳዎች በ2005 የተጀመሩ ሲሆን ከተራ ቁጥር 18 እስከ 21 ያሉት ሰባት ብሎኮች ደግሞ በ2006 መጨረሻ ላይ የተጀመሩ ናቸው) እንዲሁም የሁለተኛ ዙር የመሰረት ልማት ስራዎች (ሰንጠረዥ 20) እና የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት (ሰንጠረዥ 21) ናቸው።

በ2007 አዲስ ይሰራሉ ተብለው የተያዙት ዋና ዋና የግንባታ ሰራዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፤

- በዋናው ግቢ 23 የህንፃ ብሎኮች መስራት (ሰንጠረዥ 22 ላይ የተመለከቱት)
- በሁለተኛው ግቢ 33 የህንፃ ብሎኮችን መጀመር

- የዋናው ግቢ አጥር ስራዎች ማከናወን
- ለመምህራን መኖርያ ተብለው ከክልሉ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ የተገዙት ያላለቁ የኮንዶሚንየም ቤቶች ርክክበ በመፈፀም የግንባታ ስራዎችን ማከናወን
- አራት ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ቁፈራ ማከናወን
- የማኔጅመንት ህንፃ ዲዛይን በማጠናቀቅ የግንባታ ስራ መጀመር እንዲሁም ከትግራይ ልማት ማህበር ጋር በመተባበር የሚሰራው ሞዴል ትምህርት ቤት እና በከተማው ሆስፒታል ውስጥ አንድ ብሎክ መገንባት ይገኙበታል።

ዩኒቨርሲቲው በአምስት አመታት ውስጥ አስራ አምስት ሺ ተማሪዎችን ሊያስተናግድ ይችላል በሚል እሳቤ ነው የግንባታ ስራዎች እና ሌሎች አጠቃላይ ክንውኖች በመፈፀም ላይ የሚገኙት። የግንባታ ስራዎች ሲባል በሁለት ተከፍለው (ማለትም የህንፃ ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ስራዎች) ነው በመከናወን ላይ ያሉት። የህንፃ ግንባታው በአምስት ዙሮች የሚካሄድ ሆኖ በድምሩ ከ190 በላይ ብሎኮች ይኖሩታል። የመሰረተ ልማት ስራዎች ደግሞ የውሃ፤ የመንገድ፤ የፍሳሽና፤ የኤሌክትሪክ ስራዎችን የሚያጠቃልል ነው። በዚሁም መሰረት የግንባታው ስራ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በ2007 የትምህርት አመት 10690 መደበኛ ተማሪዎችን ለማስተናገድ አስችለውታል።

ቀደም ብለው ተጀምረው የነበሩት የግንባታ ሰራዎች አፈፃፀም በAppendix 4 (የሶስተኛ ዙር ግንባታዎች) እንዲሁም በሰንጠረዦች 20 እና 21 ተመልክተዋል። በዚሁም መሰረት የሶስተኛ ዙር ግንባታ በ21 ኮንትራክሮች አመካኝነት የተሰሩት 32 ዋና ዋና ብሎኮች፤ ስድስት የልብስ ማጠብያዎች (በድምሩ 38 ብሎኮች)፤ እና ሶስት የስፖርት መጫወቻ ሜዳዎች (የቴኒስ፤ የእግር ኳስ፤ እንዲሁም የቮሊናእጅ ኳስ) ግንባታ 99.74 ተጠናቀው ጥቅም ላይ ውለዋል። በገንዘብ ሲገለፅ የሶስተኛው ዙር ግንባታ የኮንትራት ዋጋ (ቫትን ሳይጨምር) 201.3 ሚልዮን (ከቫት ጋር ደግሞ 231.5 ሚልዮን) ሆኖ የተሰራው ስራ ደግሞ 200.8 ሚልዮን (ቫትን ሳይጨምር) ነው። በ2007 ለተቀበልናቸው ከ4500 በላይ ተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበራቸው። በተለይም የሶስተኛ ዙር ሁለተኛው ክፋይ የሆኑትና በጣም ተፈላጊ የነበሩት ተጨማሪ የምግብ አዳራሽ እና አንድ የእንጀራ መጋገርያ ለተማሪዎች ቅበላ በጊዜው መድረሳቸው በጣም አስፈላጊ ነበር።

የሁለተኛ ዙር የመሰረተ ልማት ሰራዎች አፈፃፀም 62% (ሰንጠረዥ 20 ይመልከቱ) የደረሰ ሲሆን 161.8 ሚልዮን ብር ያህል የኮንትራት ዋጋ ያለው የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት አፈፃፀም (30.34%) ግን ከታቀደው በታች ነው። ዋናው ምክንያቱም ለፍሳሽ ማጣርያው ተብሎ በተጨማሪ 20 ሄክታር ያህል እንዲሰጠን ለአከባቢው አስተዳደር ባቀረብነው ጥያቄ መሰረት የተሰጠን ቦታ ከአከባቢው ነዋሪዎች የተወሰደ በመሆኑ ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ እስከ ፍርድ ቤት ድረስ የደረሱ ክርክሮች በመኖራቸው ምክንያት መነሳት የሚገባቸው ነዋሪዎች በጊዜው መነሳት ባለመቻላቸው ነው። በዚሁም ምክንያት የግንባታ ስራው እስከ መቆም ደርሶ የነበረ ሲሆን ችግሩ ከብዙ ጊዜ በኋላ የዞኑና የወረዳው አስተዳደር ድጋፍ ተጨምሮበት የተፈታ (ማለትም ህጋዊ ያልሆኑ ግንባታዎች በማፍረስ) ቢሆንም የግንባታውን ስራ ከማንተት ግን ሊያድነው አልቻለም። ግንባታውን አንቶትና አቁሞት የነበረው ችግር ከተፈታ በኋላ ሰራው በጥሩ ሁኔታ እየቀጠለ ሲሆን 18% ላይ ቆሞ የነበረው አፈፃፀም በአመቱ መጨረሻ ላይ 30.34% ደርሷል።

በ2007 ይሰራሉ ተብለው የታቀዱት አዲስ የግንባታ ስራዎችን በተመለከተ ያለው አፈፃፀም የሚከተለውን ይመስላል፤

1. በዋናው ግቢ ይሰራሉ ተብለው የታቀዱት የአራተኛ ዙር 23 ብሎኮች (20ዎቹ ዋና ብሎኮች ሲሆኑ 3 ደግሞ የልብስ ማጠብያዎች ናቸው) የተጀመሩ ሲሆን አፈፃፀማቸውም በሰንጠረዥ 22 እንደተመለከተው 85.77% ደርሷል። በገንዘብ ሲገለፅ ደግሞ የነዚህ ብሎኮች የኮንትራት መጠን ቫትን ሳይጨምር 107.2 ሚልዮን (ወይም ቫትን ጨምሮ 123.3 ሚልዮን) ሲሆን የተሰራው ስራ ደግሞ 92 ሚልዮን (ቫትን ሳይጨምር) ነው። በነዚህ ብሎኮች ስራ ላይ የሚገኙ 14 ኮንትራክተሮች ናቸው። እነዚህ ብሎኮች ለ2008 የተማሪዎች ቅበላ እንደሚደርሱ ከወዲሁ መገመት አያዳግትም።

2. በሁለተኛው ግቢ ለመስራት የታቀደው 33 ብሎኮች የያዘው የግንባታ ስራ በአመቱ መጨረሻ (ማለትም ሰኔ 2007) የተጀመረ ቢሆንም ግንባታው በታሰበለት ጊዜ ሊጀመር አልቻለም። የመዘግየቱ ሁለት ዋና ምክንያቶች ደግሞ፤ አንደኛ ዩኒቨርሲቲው 60 ሄክታር የያዘ ሁለተኛ ግቢ መጀመርያ ላይ የተመደበለት ቢሆንም በቦታው መገንባት ያለባቸው ግንባታዎች ዲዛይን አልተሰራለትም ነበር። ምንም እንኳ ዩኒቨርሰቲው ከ60 ሄክታሩ በተጨማሪ ከከተማው አስተዳደር ጋር በመመካከር ተጨማሪ 55 ሄክታር የተሰጠው ቢሆንም የግንባታ ስራ እንዲጀመር የተፈለገው ግን መጀመርያ በተሰጠው ቦታ ላይ ነው። ሆኖም በዚህ ቦታ የማስተር ፕላንም ይሁን የዲዛይን ስራ ሳይሰራለት የቆየ ከመሆኑ አንፃር ይሄን ስራ የሚሰራ እና የግንባታውን ስራ የሚያማክር ድርጅት መምረጥ ያስፈልግ ነበር። አማካሪው ድርጅት በጨረታ እንዲመረጥ የተደረገ ቢሆንም የጨረታ ዶኩመንት ለማዘጋጀት እና ጨረታውን ለማከናወን የራሱን ጊዜ ወስዷል። ከዚሁም ጋር ተያይዞ በጨረታው ከተወዳደሩት ውስጥ አንዱ ክስ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማቅረቡ ምክንያት ሂደቱ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን እንዲቆም ተደርጎ ነበር። ጉዳዩ ታይቶ ክሱ ውድቅ የተደረገ ቢሆንም ስራውን በጊዜው ላለመጀመር የራሱን አስተዋፅኦ ማድረጉ ግን አልቀረም። አሸናፊው ድርጅት ከተለየ በኋላ ደግሞ የማስተር ፕላን እና የዲዛይነ አዳፕቴሽን ስራ መሰራት ስለነበረበት እሱም የራሱን ጊዜ ያስፈልገው ነበር። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከካሳ ግመታና ክፍያ የተያያዘ ነው። መጀመርያ ላይ ለዩኒቨርሲቲ ግንባታ ተብሎ በተመደበው 60 ሄክታር ላይ መከፈል የነበረበት ካሳ ክፍያ ከዋናው ግቢ ጋር አንድ ላይ የተሰራ ቢሆንም የተለያዩ ቅሬታዎችና ክሶች ይቀርቡ ስለነበር ያለቀለት ጉዳይ አልነበረም። ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ዩኒቨርሲቲው የተሰጠውን ክልል ማጠር ስለፈለገ የማጠር ስራውን የሚያደናቅፉ የካሳ ጥያቄዎች በስፋት መነሳታቸው አልቀረም። ከጥያቄዎቹ አንዳንዶቹ የተገመተልን ችግር አለበት የሚል ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ጭራሽ አልተገመተልንም (ስለዚህ ተገምቶ ካሳ ይሰጠን፣ ተለዋጭ ቦታም ሊሰጠን ይገባል) የሚሉ ናቸው። ዩኒቨርሲቲውም የአከባቢው አስተዳደርም በከፍተኛ ደረጃ የተሳተፈበት የክትትል ስራዎች በማከናወን የግንባውን መጀመር ሊያደናቅፉ ይችሉ የነበሩት ችግሮች ሊፈቱ ችለዋል። ለምሳሌ ጭራሽ ካሳ አልተገመተልንም የሚለው ጥያቄ ታይቶ ለ16 ነዋሪዎች (ባለይዞታዎች) ካሳ ተገምቶላቸው በዩኒቨርሰቲው አመካኝነት ክፍያ እየተፈፀመላቸው ነው (በርግጥ አንዳንዶቹ የተገመተልን ትክክል ስላልሆነ አንወስድም ያሉም አሉ)። ሁለቱም ከላይ የተነሱት ዋና ዋና ምክንያቶች በዋናነት ተፈተው የግንባታ ስራው በአመቱ መጨረሻ ላይ ስለተጀመረ ለ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል።
3. የዋናው ግቢ አጥር በተመለከተ ደግሞ የዲዛይን ስራ አልቆ የኮንትራክተር መረጣ ተካሂዶ የግንባታው ስራ ተጀምሮ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል። በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት እንደሚጠናቀቅም ይጠበቃል። ለ2008 የተማሪ ቅበላ እንደሚደርስም ይታሰባል። ግቢው እስካሁን አጥር ስላልነበረው አጥሩ ሲጠናቀቅ የደህንነት እና የስርቆት ችግሮችን በእጅጉ ያቃልላል የሚል እምነት አለ።
4. ለመምህራን መኖርያ ይሆናሉ ተብለው የተገዙት ያላለቁ የኮንደሚንየም ቤቶች በተመለከተ ደግሞ የርክክቡ ስራ ተከናውኖ፣ የማቴርያል መረጣ ተደርጎ፣ ኮንራክተሮች በግልፅ ጨረታ እንዲለዩ ተደርጎ በተሻለ ጥራት ለማጠናቀቅ የግንታ ስራው ተጀምሯል። ለክትትል ይመች ዘንድም ከግንባታ ፅ/ቤት በተጨማሪ ዩኒቨርሲቲው ካሉት አስተማሪዎች ውስጥ 5 መምህራን (ሶስት ከሲቪል ምህንድስና፣ አንድ ከኤሌክትሪካል ምህንድስና፣ አንድ ከሜካኒካል ምህንድስና) በመመደብ በክትትል ስራው የሚሳተፉ ይሆናል።
5. አራት ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ግንባታ ማከናወን በአመቱ ከተያዙት የግንባታ እቅዶች ውስጥ ይገኝበታል። ለዩኒቨርሲቲው (ለዋናው ግቢ) የሚሆን ውሃ እየቀረበ ያለው ዩኒቨርሰቲው ቀደም ብሎ ካስቆፈራቸው ሁለት ጉድጓዶች ነው። ወደ መስመር የገባ ባይሆንም ቀደም ብሎ የተቆፈረ ሌላ ሶስተኛ ጉድጓድ አለ፣ የማመንጨት ሃይሉ ግን አነስተኛ (3 ሊትር በሰከንድ) ነው። ጥቅም ላይ ከዋሉት ሁለቱ ውስጥ አንደኛው 4 ሊትር ሁለተኛውና በጣም የተሻለው 10 ሊትር በሰከንድ የማመንጨት አቅም ያላቸው ሲሆን የመጀመርያው በ2004 ብቻውን ስንጠቀምበት የነበረ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደ መስመር የገባው ከ2005 ጀምሮ ነው። በ2004 ጥቅመ መስጠት የጀመረው ጉድጓድ ከ2005 ጀምሮ የማመንጨት አቅሙ በጣም እየደከመ የመጣ ሲሆን በ2005 ጥቅም ላይ የዋለው ደግሞ ከ2006 መጨረሻ ጀምሮ አቅሙ እየደከመ መጥቷል። በዚሁም መሰረት በ2007 የውሃ

አቅርቦች የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ችግር ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ተወስዶበት ስለነበር ከ2006 ክረምት ጀምሮ አራት ተጨማሪ የውሃ ጉድጓድ መቆፈር እንዳለብን እቅድ ተይዞ ለተግባራዊነቱ እንቅስቃሴ ተደርጓል። ከዩኒቨርሲቲው ውጭ እና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ካሉት ባለሞያዎች የተሳተፉበት ጥናት በማካሄድ ውጤት ያመጣሉ ተብለው የተገመቱት አራት ቦታዎች ተመርጠው የቁፋሮ ስራ እንዲጀመር ተደርጓል። ቁፋሮውን ያከናወነው ደግሞ የክልሉ የውሃ ኢንተርፕራይዝ ነው። ከሁሉም የተሻለ ውጤት ይገኝበታል ተብሎ የታሰበው እና ከሌሎቹ ቦታዎች ለዩኒቨርሲቲው ቅርበት ባለው ቦታ (ልዩ ስሙ መገብ በተባለ ቦታ) የሚገኘው የመጀመርያ ቁፋሮ የተደረገ ሲሆን ውጤቱ ግን ከተጠበቀው የወረደ ነው የነበረው። ከዚሁ ጉድጓድ የተገኘው ውሃ አነስተኛ (ማለትም 3.5 ሊትር በሰከንድ) ከመሆኑ በተጨማሪ ውሃው የተገኘው በ18 ሜትር አከባቢ ስለሆነ አስተማማኝነቱ ዝቅተኛ ነው። ወደ ውስጥ በተቆፈረ ቁጥር ተስፋው እየቀነሰ ስለመጣ ሊቆፈር ከታሰበው ርቀት ሳይደርስ እንዲቆም ተደርጓል። ሁለተኛው ቁፋሮ የተደረገው ማይ ፃዕዳ በሚባል አከባቢ (ከዩኒቨርሲቲው ወደ 5 ኪሎሜትር አከባቢ የሚርቅ) ሲሆን የተገኘው ውሃ በጣም ዝቅተኛ (1.5 ሊትር በሰከንድ) ነው። ሶስተኛ ሊቆፈር የታሰበው ከሁለተኛው ቦታ በቅርበት የሚገኝ ስለሆን የተሻለ አይገኝበትም የሚል እሳቤ ስለተወሰደ ቁፋሮው እንዳይካሄድ ተደርጓል። በአራተኝነት ሊቆፈር የታሰበው ግን በአንድ በኩል ለዋናው ግቢ ሳይሆን ለሁለተኛው ግቢ ስለነበርና ቦታው ደግሞ ቀደም ብሎ ለኢንቨስተር የተሰጠ መሆኑ ቆይቶ ስለታወቀ ቁፋሮው ሳይከናወን ቀርቷል። በዚሁም መሰረት የተከናወነው የአዳዲስ ጥልቅ ጉድጓዶች ቁፋሮ በታሰበው መልኩ ውጤታማ ሆኖ ስላልተገኘ እንደጊዚያዊ መፍትሄ ያሉትን የውሃ ጉድጓዶች በተወሰነ መልኩ መጠቀም (በሳምንት ሁለት ቀናት) እና በዩኒቨርሲቲው ግቢ የውሃ ገንዳዎችን (ሮቶዎችን) በማስቀመጥ በየቀኑ በውሃ ቦቴዎች እንዲሞሉ በማድረግ የውሃ ችግሩን በጊዚያዊነት ለማስተዳደር (manage ማድረግ) ተችሏል። እንደዘላቂ መፍትሄ ደግሞ ሌሎች ተጨማሪ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች እንዲቆፈሩ ሆኖ ጨረታ ሲወጣ ግን ምርትን (per product) መሰረት ያደረገ ሆኖ 10 ወይም ከዛ በላይ የማመንጨት አቅም ያላቸው እንዲቆፈሩ በሚል መልኩ የጨረታ ዶኩመንት ተዘጋጅቶ ስራው በ2007 ክረምት ላይ እንደሚጀመር ይጠበቃል።

6. የማኔጅመንት ህንፃ ግንባታ በተመለከተ የተወሰኑ የዝግጅት ሰራዎች የተሰሩ ቢሆንም በስራ መደራረብ ምክንያት በታሰበው መሰረት ሊሰራ ስላልቻለ በ2008 የሚከናወን የሆናል።
7. በከተማው ሆስፒታል ለመስራት የታሰበው አንድ ብሎክ በተመለከተ ከሆስፒታሉ አስተዳደር ጋር ምክክር ተደርጎበት ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ የነበረው ዲዛይን መስተካከል ስለሚያስፈልገው የዲዛይን ማስተካከል ስራ እየተሰራ ይገኛል። ስለሆነም የግንባታው ስራው ሊጀመር አልቻለም።
8. ከትግራይ ልማት ማህበር ጋር በመተባበር በከተማው ሞዴል ሁለተኛ ደረጃ (የኮሙኒቲ) ትምህርት ቤት ለማስራት የተያዘው እቅድም የቦታው ሳይት ፕላን በከተማው አስተዳደር በኩል አልቆ ለዩኒቨርሰቲው ስላልደረሰው በተወሰነ መልኩም ቢሆን (ማለትም የአጥር ስራ) ለመስራት ታስቦ የነበረው ሊሰራ አልቻለም።

ሰንጠረዥ 20. የሁለተኛ ዙር መሰረተ ልማት ስራዎች አፈፃፀም (እስከ ሰኔ 2007)

| No | Name of Contractor | Typology | Contract Amount | Amount with VAT | Executed % | Executed Amount |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | United Construction P.L.C | Infrastructure (phase II) | 45,519,373.15 | 52,347,279.12 | 62.00 | 28,222,011.35 |

ሰንጠረዥ 21. የፍሳሽ ማጣርያ (ትሪትመንት) ፕላንት አፈፃፀም (ሰኔ 2007)

| No | Name of Contractor | Typology | Contract Amount | Executed Amount | Executed % |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | United Construction P.L.C | treatment plant | 161,837,506.09 | 49,094,277.96 | 30.34% |

ሰንጠረዥ 22. የአራተኛ ዙር ግንባታ ስራዎች አፈፃፀም (ሰኔ 2007)

| | Name of Contractor | Typology | Contract Amount | Vat | Contract Amount with Vat | Executed % | Executed Amount |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Akberet G/tsadik G.C | GS-T1-307 | 2,465,211.10 | 369,781.67 | 2,834,992.77 | 100.00 | 2,465,211.10 |
| | | AL-T1-153 | 1,881,425.13 | 282,213.77 | 2,163,638.90 | 100.00 | 1,881,425.13 |
| 2 | Amanuel Gedlu B.C | DN-T1-13 | 4,419,931.37 | 662,989.71 | 5,082,921.08 | 100.00 | 4,419,931.37 |
| 3 | Brothers Engineering B.C | SE-M1-132 | 7,068,501.25 | 1,060,275.19 | 8,128,776.44 | 88.30 | 6,241,486.60 |
| | | LN-T1-* | 456,417.93 | 68,462.69 | 524,880.62 | 33.41 | 152,489.23 |
| 4 | Conic Engineering p.l.c | DO-T1-CYT-253 | 9,671,580.98 | 1,450,737.15 | 11,122,318.13 | 53.45 | 5,169,460.03 |
| | | DO-T1-CYT-256 | 9,671,580.98 | 1,450,737.15 | 11,122,318.13 | 76.42 | 7,391,022.18 |
| 5 | Fantaye Gidey B.C | WS-T1-134 | 2,465,211.10 | 369,781.67 | 2,834,992.77 | 91.97 | 2,267,254.65 |
| | | WS-T1-137 | 2,465,211.10 | 369,781.67 | 2,834,992.77 | 91.97 | 2,267,254.65 |
| | | SL-T1-116 | 1,416,574.37 | 212,486.16 | 1,629,060.53 | 91.90 | 1,301,831.85 |
| 6 | Gizen G.C | SE-M1-131 | 7,068,501.25 | 1,060,275.19 | 8,128,776.44 | 100.00 | 7,068,501.25 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | LN-T1-* | 456,417.93 | 68,462.69 | 524,880.62 | 33.41 | 152,489.23 |
| 7 | kalka Construction B.C | DO-T1/Tv-261 | 6,347,818.08 | 952,172.71 | 7,299,990.79 | 94.47 | 5,996,783.74 |
| 8 | Kibrom Desta B.C | DO-T1-CYT-254 | 9,671,580.98 | 1,450,737.15 | 11,122,318.13 | 100.00 | 9,671,580.98 |
| 9 | Mulugeta Tadesse B.C | SE-M1-130 | 7,068,501.25 | 1,060,275.19 | 8,128,776.44 | 100.00 | 7,068,501.25 |
| | | LN-T1-* | 456,417.93 | 68,462.69 | 524,880.62 | 29.41 | 134,232.51 |
| 10 | Solomon Abraha BC | DO-T1/Tv-257 | 6,529,459.07 | 979,418.86 | 7,508,877.93 | 77.63 | 5,068,819.08 |
| 11 | Teklebrhan Tadesse B.C | DO-T1/Tv-259 | 6,529,459.07 | 979,418.86 | 7,508,877.93 | 81.46 | 5,318,897.36 |
| 12 | Teklu W/Miceal B.C | DO-T1-CYT-255 | 9,671,580.98 | 1,450,737.15 | 11,122,318.13 | 83.12 | 8,039,018.11 |
| 13 | Tsigabu G/Slassie G.C | DO-T1/Tv-260 | 6,529,459.07 | 979,418.86 | 7,508,877.93 | 76.24 | 4,978,059.59 |
| 14 | Zelalem Niguse B.C | MWS-T1- | 2,518,436.69 | 377,765.50 | 2,896,202.19 | 100.00 | 2,518,436.69 |
| | | PP-T1- | 1,583,312.44 | 237,496.87 | 1,820,809.31 | 100.00 | 1,583,312.44 |
| | | FD-T2- | 820,802.41 | 123,120.36 | 943,922.77 | 100.00 | 820,802.41 |
| Total | | | 107,233,392.46 | 16,085,008.87 | 123,318,401.33 | **85.77** | 91,976,801.44 |

*Washing Basin

## 4. የእቅድ አፈፃፀም

ዩኒቨርሲቲው ስራ ከጀመረበት ከ2004 ጀምሮ በቁልፍ ተግባር ዙርያ አመታዊ ዝርዝር እቅድ በማዘጋጀትና በእቅዱ ላይ መግባባት በመድረስ ነው ስራዎቹን በማከናወን ላይ የሚገኘው። በየአመቱ ደግሞ መሪ ቃል (motto) እየተዘጋጀ በዚሁ መሪ ቃል በመሰባሰብ የአመቱን እቅድ በመፈፀም እና የእቅድ አፈፃፀምም በስድስት ወር እና በአመቱ መጨረሻ ጠቅላላው የዩኒቨርሲቲ መምህራን እና ሰራተኞች በሚገኙበት መድረክ እንዲገመገም ይደረጋል። ለምሳሌ ዩኒቨርሲቲው በ2004 የነበረው መሪ ቃል " ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከደረሱበት ደረጃ ተነስተን ወደፊት እንገዝ" የሚል ነበር።

የ2007 ቁልፍ ተግባር **"በአግባቡ የተደራጀ የትምህርት ልማት ሰራዊት በመጠቀም መልካም አስተዳደር፤ ሰላማዊ መማር ማስተማር፤ እና የትምህርት ጥራት የሰፈነበት ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን ማድረግ።"** የሚል ሲሆን በዚሁም የአመቱ ዋናው ተግባር የልማት ሰራዊትን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲውን አላማዎች ለማሳካት ከፍተኛ ጥረትን ማድረግ የሚያመለክት ነው። ቁልፍ ተግባሩን መሰረት በማድረግ ደግሞ በየአመቱ እንደሚደረገው የ2007 መሪ ቃል (motto) ሆኖ የወጣው **"የቡድን ስራ ለሰላማዊ ግቢ"** ወይም 'Team Work for a Tranquil Campus' የሚል ነው። በ2007 የተስተናገደው የመደበኛ ተማሪ ቁጥር ከአስር ሺ በላይ ስለሆነ ይሄንን ያህል ብዛት ያለው የተማሪ ቁጥር በአግባቡ ማስተናገድ የሚቻለው ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች እንደየክፍሉ ሁኔታ የተመደበላቸውን ስራ በደንብ ሲያከናውኑ ከዚሁም አልፎ ደግሞ ሁሉም ክፍሎች እየተባበሩና እየተጋገዙ እንደ አንድ አሃድ ሆነው የዩኒቨርሲቲውን ሶስት ተልእኮዎች ማሳካት ሲችሉ ነው። ይሄንን ማሳካት የሚቻለው ደግሞ የተጠናከረ እና የሚናበብ የቡድን ስራ ሲኖር እንደሆነ የሚያመለክት ነው መሪ ቃሉ። ከዚህም በተጨማሪ 2007 አምስተኛው አገራዊ ምርጫ የሚከናወንበት ስለሆነ ምርጫው ሰላማዊና ዲሚክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለማካሄድ ደጋፊ የሚሆን መሪ ቃል ነው የተመረጠው።

በዚሁም መሰረት የ2006 ስራ አፈፃፀም ሰኔ 28/2006 ጠቅላላ መምህራንና ሰራተኞች ባሳተፈ መልኩ ከተገመገመ በኋላ የ2007 ዝርዝር እቅድ ተዘጋጅቶ እና በዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድ ፀድቆ አስፈላጊው የዝግጅት ስራዎች ከተሰሩ በኋላ የትግበራ ምእራፍ ስራዎችም እንዲከናወኑ ተደርገዋል። ዝርዝር የአፈፃፀም ሁኔታው ነጥብ በነጥብ በሰንጠረዥ መልክ የቀረበ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.1. የቁልፍ ተግባር አፈፃፀም

ከላይ እንደተቀመጠው የአመቱ ቁልፍ ተግባር የትምህርት ልማት ሰራዊትን በመጠቀም የዩኒቨርሲቲውን ተልእኮዎች ማሳካት የሚል ሲሆን በዚሁም መሰረት በ2006 ሁለተኛ ሰሚስተር በጥሩ ሁኔታ የተጀመረው የተማሪዎች የአንድ ለአምስት መረቦች (Cooperative Learning) በ2007 የትምህርት ዘመንም በተጠናከሩ ሁኔታ ቀጥሏል። በ2006 በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው ማንዋል መሰረት በማድረገ ዩኒቨርሲቲው የራሱ የአሰራር ማንዋል ያዘጋጀ ሲሆን በማንዋሉ መሰረት የአንድ ለአምስት አደረጃጀት በጥሩ ሁኔታ ሊፈፀም ችሏል። በዚህም መሰረት በሁሉም ኮሌጆችና ትምህርት ክፍሎች መጠነኛ ልዩነቶች ቢኖሩም አጥጋቢ ሊባል በሚችል ሁኔታ ተከናውኗል።

በድምሩ ሁለተኛው ሰሚስተር ላይ በዩኒቨርሲቲው የነበሩት የተማሪዎች የአንድ ለአምስት መረቦት (Cooperative Learning Teams) 1879 ሲሆኑ የልማት ቡድኖች ደግሞ 197 ናቸው። በAppendix 5 እንደተቀመጠው በአንደኛ ሰሚስተር የነበሩት የአንድ ለአምስት ቡድኖች 1982 እና የልማት ቡድኖች ደግሞ 202 ሲሆን በሁለተኛ ሰሚስተር ቁጥሩ የቀነሰበት ምክንያት የአራተኛ አመት የኢንጂነሪንግ ተማሪዎች ለተግባራዊ ልምምድ (Appreticeship) ስራ ወደተለያዩ ድርጅቶች እንዲሰማሩ ስለተደረገ ነው። ቀደም ብለው በተማሪዎችም በመምህራንም በኩል ይታዩ የነበሩ ተአቅቦዎች (reservations) ስለጉዳዩ አስፈላጊነት በተደጋጋሚ ውይይቶች በመደረጋቸው እና በተለይም ተማሪዎች አከባቢ እርስበርስ በቡድን የመተጋገዙ ጉዳይ ያለውን ጠቃሚነት ከጊዜ

ወደ ጊዜ በተግባር እያዩት ስለመጡ በአስፈላጊነቱ ከፍተኛ የመተማመን ስሜት ፈጥሮላቸዋል። ተማሪዎች በአንድ ለአምስት በሚደራጁበት ጊዜ መጀመርያ ተገቢውን ኦርየንቴሽን ለነባርም ሆነ ለአዲስ ተማሪዎች በመስጠት ያሉዋቸውን ጥያቄዎች ሆኑ ጥርጣሬዎች እንዲያነሱ በማድረግ እና ያሉንን አደረጃጀቶች በመጠቀም ነባር ተማሪዎች ያገኙትን ጠቀሜታ እንዲያብራሩ በማድረግ መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ ነባር ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ባላቸው ውጤት (አዲስ ተማሪዎች ደግሞ ባላቸው የ12ኛ መልቀቅያ ፈተና ውጤት) መሰረት የተሻለ ውጤት ያላቸው እና ደከም ያለ ውጤት ያላቸው እንዲሁም ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ወይም ተሟልተው እስከተገኙ በቋንቋ፤ በሃይማኖት፤ በፆታ ወዘተ በማሰባጠር ወይም በሚያመጣጥን መልኩ እንዲደራጁ በማድረግ ነው የሚተገበረው። ይህም ማለት በየክፍሉ ያሉት ተማሪዎች ሁኔታ መሰረት በማድረግ ከተለያዩ ክልሎች የመጡ እንዲኖሩበትና የፆታና የሃይማኖት ስብጥርም ያካተተ እንዲሆን ይደረጋል ማለት ነው።

ተማሪዎች በዚህ መልኩ ከ5-7 እየሆኑ በአንድ ቡድን ሲደራጁ በየሴክሺኑ ደግሞ የልማት ቡድን ይኖራቸዋል። እያንዳንዱ ቡድንና በቡድኑ ያሉት ተማሪዎች እያንዳንዳቸው በየሰሚስተሩ እቅድ (እያንዳንዱ ተማሪ ለእያንዳንዱ ኮርስ ሊያገኘው የሚያቅደው ውጤት) የሚያዘጋጁ ሲሆን በየሳምንቱ መጨረሻም አጠር ያለና በዩኒቨርሰቲው የተዘጋጀ ቅፅ በመሙላት ሪፖርት ለልማት ቡድናቸውና ለትምህርት ክፍል ሃላፊያቸው ያቀርባሉ። በየደረጃው ያሉ ሃላፊዎችና የየክፍሉ ሜንተሮች (መምህራን) አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ስለሚያደርጉላቸው የተማሪዎች እርስ በርስ መደጋገፉ በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል። ከላይ እንደተጠቀሰው የተማሪ አንድ ለአምስት ቡድኖች (Cooperative Learning Teams) የተዘጋጀላቸውን ፎርማት በመጠቀም እቅድና ግብ (ታርጌት) የሚያዘጋጁ ሲሆን በየሳምንቱ መቼና በስንት ሰአት እንደሚገናኙ ፕሮግራም ይይዛሉ። የሰሩትን ስራ በተመለከተ ደግሞ ሪፖርት ያቀርባሉ። የሚገናኙበት ፕሮግራም እና የሚገናኙበት ቦታ በትምህርት ክፍላቸው የሚታወቅ ሆኖ በነዚህ ቀናት በሜንተርነት የተመደቡ መምህራን ክትትል ያደርጉላቸዋል። ሌሎች የየትምህርት አይነቱ መምህራንም ተማሪዎቹ በቡድን ውይይት ወቅት ለሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች በማስረዳት ይሳተፋሉ። በየፕሮግራሙ መሰረት መምህራን ከስራ ሰአታት ውጭም ጭምር እየተገኙ (ለምሳሌ ምሽት እስከ ሶስት ሰአት ድረስ) ድጋፍ ይሰጣሉ። በዚህ ምክንያት የሚያመሹ መምህራን ማታ ማታ የአውቶቡስ አገልግሎት እንዲዘጋጅላቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረትም የአውቶቡስ አገልግሎት ተዘጋጅቷል። የአንድ ለአምስት ቡድኖች በዩኒቨርሲቲው ቤተመፃህፍት (ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ቦታ) እና በመማርያ ክፍሎችና አደራሾች እየተገናኙ ነው እርስ በርስ የሚደጋገፉት። ላይብረሪው የሃያ አራት ሰአት አገልግሎት ስለሚሰጥ በላይብረሪው ውስጥ የሚገኘው የተማሪዎች አንድ ለአምስት መወያያ አዳራሽም እንዲሁ የሃያ አራት ሰአት አገልግሎት ይሰጣል።

የኔትወርክ ቡድኑ አባላት ተዘዋዋሪ የሆነ ሃላፊነት ይሰጣቸዋል፤ በዚሁም መሰረት አንዱ/ዷ ተማሪ በአንደኛው ቀን ስለአንድ ትምህርት ተዘጋጅታ የምታቀርብ ከሆነ በሚቀጥለው ፕሮግራም ሃላፊነቱ የሌላ ተማሪ ይሆናል። እንዲህ እያለ ስለሚቀጥልና ሁሉም የተለያየ የስራ ድርሻ ስለሚሰጠው አንዱ ተቀባይ አንዱ ደግሞ ሰጪ የሚሆንበት ሁኔታ አይኖርም። ሁሉም እንደየስራ ድርሻው አስተዋፅኦ ስለሚያደርግ ሰጪም ተቀባይም ሆኖ ይሳተፋል፤ ተጠቃሚም ይሆናል። በዚሁም መሰረት ጎበዝ ተማሪዎች ጊዚያችንን አለአግባብ እናባክናለን በሚል ይቀርብ የነበረው ስሞታ የተፈታበት ሁኔታ ነው ያለው። ለነገሩ ጎበዝ ተማሪዎችም ቢሆኑ ሌሎችን በሚያስረዱበት ጊዜ ትምህርቱን የበለጠ ስለሚረዱት እውቀታቸውን ያዳብሩበታል፤ ተጠቃሚ ይሆናሉ። የምንከተለው የነጥብ አሰጣጥ ስርአት ደግሞ ቋሚ መስፈርትን (Criterion Referenced) መሰረት ያደረገ ስለሆነ በተማሪዎች መሃከል አላስፈላጊ የውጤት ውድድርን ስለሚያስቀር እርስ በርስ ለመተጋገዝ የሚከለክላቸው ነገር አይኖርም። የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ አካል ተደርጎ የሚታየው እና ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ክትትል እንዲሳተፉ ለማድረግና በዩኒቨርሲቲው እና በወላጆች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማዳበር የሚጠቅመው በ2006 በአንድ የትምህርት ክፍል (ሳይኮሎጂ) የተጀመረው የወላጆች ቀን (ሳምንት) አከባበርም ዘንድሮ ሰፋ ባለ መልኩ በአራት ኮሌጆች የሚገኙ የአራት ትምህርት ክፍሎች (ሳይኮሎጂ፤ እንስሳት ሳይንስ፤ ማርኬቲንግ፤ ሂልዝ ኦፊሰር) ተማሪዎች ከተለያየ የአገሪቱ ክፍል የመጡ ከ300 በላይ ወላጆች በተገኙበት ሰኔ 06/2007 እንዲከበር ተደርጓል። በአጠቃላይ በአመቱ የተሰራው የልማት ሰራዊት ግንባታ ስራ በጣም ውጤታማ እና ዩኒቨርሲቲው **የትምህርት ልማት ሰራዊት ለመፍጠር** ያስቻለው እንቅስቃሴ ነበር።

ሰንጠረዥ 23. የተማሪዎች የአንድ ለአምስት እና የልማት ቡድኖች ብዛት (ሁለተኛ ሰሚስተር)

| College | Department/Program | First Year | | Second Year | | Third Year | | Fourth Year | | Total | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 to 5 NW | Devt Team | 1 to 5 NW | Devt Team | 1 to 5 NW | Devt Team | 1 to 5 NW | Devt Team | 1 to 5 NW | Devt Team |
| | COMPUTER SCIENCE and IT | 27 | 2 | 32 | 3 | 8 | 1 | | | 67 | 6 |
| | ARCHETECTURE | 8 | 1 | | | | | | | 8 | 1 |
| | Cicvil engineering | 132 | 11 | 132 | 12 | 80 | 8 | | | 344 | 31 |
| | Mechanical engineering | 76 | 8 | 67 | 6 | 29 | 3 | | | 172 | 17 |
| | Chemical engineering | 30 | 3 | 30 | 3 | 20 | 2 | | | 80 | 8 |
| | Constrtuction Tech & Mgt | 50 | 4 | 33 | 3 | 20 | 2 | | | 103 | 9 |
| | Electrical engineering | 72 | 6 | 40 | 4 | 30 | 3 | 10 | 1 | 152 | 14 |
| | **SUB TOTAL** | **395** | **35** | **334** | **31** | **187** | **19** | **10** | **1** | **926** | **86** |
| | MATHEMATICS | 8 | 1 | 10 | 2 | 7 | 1 | | | 25 | 4 |
| | PHYSICS | 8 | 1 | 8 | 1 | 6 | 1 | | | 22 | 3 |
| | CHEMISTRY | 8 | 1 | 13 | 2 | 12 | 2 | | | 33 | 5 |
| | BIOLOGY | 18 | 2 | 16 | 2 | 16 | 2 | | | 50 | 6 |
| | SPORT SCIENCE | 6 | 1 | 8 | 1 | 6 | 1 | | | 20 | 3 |
| | STATISTICS | 12 | 1 | 8 | 1 | 8 | 1 | | | 28 | 3 |
| | GEOLOGY | 8 | 1 | 9 | 1 | 6 | 1 | | | 23 | 3 |
| CNCS | **SUB TOTAL** | **68** | **8** | **72** | **10** | **61** | **9** | **0** | **0** | **201** | **27** |
| | MEDICINE | 16 | 2 | 21 | 2 | 7 | 1 | | | 44 | 5 |
| | HEALTH OFFICER | 11 | 1 | 10 | 1 | 8 | 1 | | | 29 | 3 |
| | NURSING | 18 | 2 | 10 | 1 | 6 | 1 | | | 34 | 4 |
| | MIDWIFERY | 12 | 1 | 11 | 1 | 5 | 1 | | | 28 | 3 |
| | PHARMACY | 8 | 1 | | | | | | | 8 | 1 |
| CMHS | **SUB TOTAL** | **65** | **7** | **52** | **5** | **26** | **4** | **0** | **0** | **143** | **16** |
| CAES | PLANT SCIENCE AND | 16 | 1 | 11 | 1 | 6 | 1 | | | 33 | 3 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | TECHNOLOGY | | | | | | | | | | |
| | Animal Production and Technology | 16 | 1 | 10 | 1 | 5 | 1 | | | 31 | 3 |
| | NATURAL RESOURSE MANAGEMENT | 14 | 1 | 9 | 1 | 6 | 1 | | | 29 | 3 |
| | ENVIRONMENTAL SCIENCE | 14 | 1 | | | | | | | 14 | 1 |
| | **SUB TOTAL** | **60** | **4** | **30** | **3** | **17** | **3** | **0** | **0** | **107** | **10** |
| | ACCONTING AND FINANCE | 50 | 5 | 38 | 5 | 30 | 3 | | | 118 | 13 |
| | MARKETING MANAGEMENT | 20 | 2 | 10 | 1 | | | | | 30 | 3 |
| | MANAGEMENT | 48 | 5 | 36 | 4 | 27 | 3 | | | 111 | 12 |
| | ECONOMICS | 25 | 3 | 24 | 3 | 17 | 2 | | | 66 | 8 |
| CBE | **SUB TOTAL** | **143** | **15** | **108** | **13** | **74** | **8** | **0** | **0** | **325** | **36** |
| | ARCHEOLOGY | 6 | 1 | | | | | | | 6 | 1 |
| | GEOGRAPY | 8 | 1 | 14 | 2 | 8 | 1 | | | 30 | 4 |
| | ENGLISH | 6 | 1 | 6 | 1 | 9 | 1 | | | 21 | 3 |
| | PSYCHOLOGY | 12 | 1 | 8 | 1 | 10 | 1 | | | 30 | 3 |
| | CIVICS AND ETHICAL STUDIES | 10 | 1 | 16 | 2 | 10 | 1 | | | 36 | 4 |
| | SOCIOLOGY | 10 | 1 | 12 | 2 | | | | | 22 | 3 |
| | LAW | 10 | 1 | 12 | 1 | | | | | 22 | 2 |
| | TIGRIGNA | 5 | 1 | | | | | | | 5 | 1 |
| | THEATRICAL ART | 5 | 1 | | | | | | | 5 | 1 |
| CSSH | **SUB TOTAL** | **72** | **9** | **68** | **9** | **37** | **4** | **0** | **0** | **177** | **22** |
| **TOTAL** | | **803** | **78** | **664** | **71** | **402** | **47** | **10** | **1** | **1879** | **197** |

ከተማሪዎች የአንድ ለአምስት መረቦች በተጨማሪ የመምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መረቦችም ተቋቁመው በመስራት ላይ ናቸው። በአጠቃላይ ሲገመገም የተማሪዎች ቡድኖች የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ናቸው። እንደዋና ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው በአንድ በኩል የተሻለ ርብርብ የተደረገው በተማሪወች ቡድኖች በመሆኑ እና ተማሪዎችም ስለተጠቀሙበትና ተጠናክሮ እንዲቀጥል በመፈለጋቸው ነው። በተነፃፃሪ ሲታይ አፈፃፀሙ ከተማሪዎች የደከመ ቢሆንም የመምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቡድኖችም ተደራጅተው እየተሰራበት ነው።የመምህራን መረቦች ብዛት (በሁለተኛ ሰሚስተር የነበሩ) በሚከተለው ሰንጠረዥ ሰፍረዋል።

ሰንጠረዥ 24. የመምህራን የአንድ ለአምስትና የልማት ቡድኖች ብዛት

| ኮሌጅ | የአንድ ለአምስት ቡድኖች | የልማት ቡድኖች |
|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግ እና ቴክኖሎጂ | 24 | 8 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 18 | 7 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 9 | 5 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 5 | 4 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 8 | 4 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ | 18 | 9 |
| **ድምር** | 82 | 37 |

የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችም በአንድ ለአምስት ቡድኖች እንዲደራጁ ተደርገዋል። አፈፃፀማቸው ከላይ እንደተመለከተው ከተማሪዎች ያነሰ ቢሆንም በተለይ ምግብ ቤት፣ ጥበቃ፣ እና ቤተመፃህፍት አከባቢ የተሻለ ሆኖ በሌሎች ክፍሎችም እየተሰራበት ይገኛል። የተደራጁት ቡድኖች ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ ይታያል።

ሰንጠረዥ 25. የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የአንድ ለአምስት ቡድኖች ብዛት

| የስራ ክፍል | የአንድ ለአምስት ቡድኖች |
|---|---|
| ፋይናንስ አስተዳደር | 3 |
| ተማሪዎች ዲን | 115 |
| ግዥና ንብረት አስተዳደር | 4 |
| ሰው ሃብት ልማት ማእከል | 3 |
| መሰረታዊ አገልግሎት | 20 |
| ግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት | 2 |
| ድምር | 147 |

## 4.2. የዝግጅት ስልጠናዎች

የ2007 ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ለተማሪዎች (ነባርና አዲስ)፤ ለመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ሰፋፊ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ለስልጠናው የሚሆኑ ፅሁፎች በአግባቡ ተዘጋጅተውና አሰልጣኞች እና የቡድን ውይይት አስተባባሪዎች (ቱተሮች) ተመድበው የተከናወነ ስልጠና ነበር። ለስልጠናው አካሄድ ይረዳ ዘንድ ዘርዘር ያለ ማንዋል በክልል አመራር በኩል ተዘጋጅቶ በማንዋሉ ላይ ውይይትና መግባባት ከተደረሰበት በኋላ ነው ስልጠናው የተጀመረው። ለስልጠናው የሚሆኑ ግብአቶችና ለሰልጣኞች የሚያስፈልጉ የምግብና የፅህፈት መሳርያዎችም ተዘጋጅተው ነበር። ስልጠናው በአጠቃላይ የተመራው በትምህርት ሚኒስቴር እና በክልል በኩል ሲሆን በዩኒቨርሲቲ በኩል ስልጠናው የተፈፀመው ደግሞ በዩኒቨርሲቲው አመራር ቦርድ አስተባባሪነት ነው። የስልጠናው አካሄድ በሁለት መልክ ሆኖ በአንድ በኩል የተመደቡት አሰልጣኞች የመግቢያ ገለፃ እና የማጠቃለያ ውይይት ያካሄዱ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በየርእሱ ጠለቅ ያሉ የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል። የቡድን ውይይቱን የሚመሩ ደግሞ የቡድን አስተባባሪዎች ነበሩ።

በአጠቃላይ በስልጠናዎቹ በከፍተኛ ተሳትፎ የታጀቡ ሲሆን ከፍተኛ መግባባት የተደረሰባቸው ነበሩ። የተደረጉት ስልጠናዎች ሶስት ሲሆኑ (ለነባር ተማሪዎች፤ ለመምህራንና ሰታተኞች፤ እና ለአዲስ ተማሪዎች) በተደረጉበት ቅደም ተከተል እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል፤

4.2.1. የነባር ተማሪዎች ስልጠና

የነባር ተማሪዎች ስልጠናው ከነሃሴ 15/2006 ጀምሮ ለሁለት ሳምንታት ያህል የተካሄደ ነበር። የስልጠናው ተሳታፉዎች ነዋሪነታቸው በዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ አከባቢ ባሉ ስምንት ወረዳዎች እና ሁለት ከተሞች (ውቕሮ፤ ዓዲግራት) ሆኖ ከሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ነበሩ። ስልጠናውን በዋና አሰልጣኝነት ያካሄዱት ከክልሉ የበላይ አመራር፤ ከቦርድ አባላት፤ ከምስራቃዊ ዞን እና ወረዳ አመራሮች፤ እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲው የተውጣጡ አሰልጣኞች ሲሆኑ በቡድን ውይይት አስተባባሪዎች የተመደቡት ደግሞ በምስራቃዊ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች የተውጣጡ የአመራር አባላት ናቸው። የስልጠናው ሂደት በየእለቱ እየተገመገመ የሚሰራ ስለነበር በቆንጆ ሁኔታ የተከናወነ ስልጠና ነበር። ለስልጠናው የተዘጋጁ ፅሁፎች የሚከተሉት ሲሆኑ ሰልጣኞች በሰባት አዳራሾች እና በበርካታ ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር የተከናወነው።

- የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግልና አገራዊ ህዳሴያችን
- የተሃድሶ መስመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ
- የልማታዊ ስርአት ግንባታ ትግላችንና ፈተናዎቹ
- ህገ መንግስታዊ መርሆዎችና ሰላማዊ የትግል ስልት በትምህርት ተቋማት

በስልጠናው የተሳተፉ ነባር ተማሪዎች ብዛት ከቀን ቀን ትናንሽ ልዩነቶች የነበሩት ሲሆን የተሳታፊዎች ብዛት 5500 ያህል ነበር። ለአብነት ያህል ነሐሴ 21/2006 ከሰአት በኋላ የነበሩት የሰልጣኞች ብዛት በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከተውን ነበር።

ሰንጠረዥ 26. የነባር ተማሪዎች ስልጠና ተሳታፊዎች (ነሃሴ 21/2006 ከሰአት በኋላ)

| ወረዳ/ከተማ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| ዓዲግራት | 597 | 347 | 944 |
| አሕፈሮም | 782 | 379 | 1161 |
| ጉሎምኻዳ | 503 | 186 | 689 |
| ኢሮብ | 103 | 45 | 148 |
| ጋንታ አፈሹም | 346 | 176 | 522 |
| ውቕሮ | 241 | 110 | 351 |
| ክልተ አውላዕሎ | 312 | 119 | 431 |
| ሓውዜን | 358 | 129 | 487 |
| ሳዕሲዕ ፃዕዳ እምባ | 388 | 166 | 554 |
| አፅቢ ወንበርታ | 163 | 47 | 210 |
| **ድምር** | **3793** | **1704** | **5497** |
| መቶኛ | 69 | 31 | 100 |

4.2.2. የመምህራንና ሰራተኞች ስልጠና

ቀጥሎ የተከናወነው የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ሲሆን ስልጠናው ከ መስከረም 10/2007 ጀምሮ ለአስር ቀናት የተካሄደ ነበር። በስልጠናው የተሸፈኑት ፅሁፎች ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ሶስቱ (ማለትም አራተኛውን ሳይጨምር) ነበሩ። የስልጠናው አካሄድ በተማሪዎች ስልጠና እንደተደረገው አይነት በአሰልጣኝ ማብራርያ እና በቡድን ውይይት ተከፋፍሎ የተከናወነ እና በጣም ጥሩ ተሳትፎ የነበረው ነው። ከቦርድ አባላት ከተመደበልን አንድ አሰልጣኝ ውጪ ሌሎቹ በሙሉ (አሰልጣኞችና ቱተሮች) ከዩኒቨርሲቲው የተመደቡ ነበሩ። በመምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ወቅት በተጠቀሱት ርእሶች ከተደረጉ ውይይቶች በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ስራዎች ላይ ግምገማ ስለተደረገ ድርብ ጠቀሜታ ነበረው። በዚህ ስልጠና ላይ በምግብ ቤት አከባቢ ተረኞች ከሆኑት ሰራተኞች ውጭ በሙሉ እንዲሳተፉ የተደረገ ሲሆን የተሳታፊዎች ብዛት ከቀን ወደቀን

የተወሰ ልዩነት የነበረው ቢሆንም በአማካይ አንድ ሺ ያህል ተሳታፊዎች ነበሩ። ለአብነት ያህል በ13/01/2007 የነበሩ ተሳታፊዎች ብዛት የሚከተለውን ይመስላል፤

ሰንጠረዥ 27. የመምህራንና ሰራተኞች ስልጠና ተሳታፊዎች (መስከረም 13/2007)

| ኮሌጅ/የስራ ክፍል | መገኘት የነበረባቸው | የተገኙ |
|---|---|---|
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ | 90 | 70 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ ኮሌጅ | 67 | 60 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፤ ግብርና እና ህክምና ኮሌጆች | 97 | 91 |
| ኢንጂነሪግና ቴክኖሎጂ ኮሌጅ | 170 | 166 |
| ተማሪዎች ዲን | 285 | 275 |
| ላይብረሪ | 124 | 119 |
| ፋይናንስ፤ ግዥና ሰውሃብት ልማት | 76 | 75 |
| የተለያዩ ፅ/ቤቶች (ውስጥ ኦዲት፤ ስርአተ ፆታ፤ እቅድና ተቋማዊ ለውጥ፤ ወዘተ) | 83 | 75 |
| መሰረታዊ አገልግሎት | 91 | 76 |
| ድምር | 1083 | 1007 |
| መቶኛ | 100 | 92.98 |

4.2.3 የአዲስ ተማሪዎች ስልጠና

የ2007 አዲስ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲው ከገቡ በኋላ በተመሳሳይ መልኩ ከላይ በተመለከቱት አራት አርእስቶች ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ስልጠናው በአራት አደራሾች የተደራጀ ሆኖ የተካሄደው ከመስከረም 28/2007 ጀምሮ ለአስር ቀናት ነበር። በዚህ ስልጠና ከአዲስ ተማሪዎች በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሶስተኛ ዙር እንዲሰለጥኑ ታስቦ ግን በጊዜ መጣበብ ባልተካሄደው መሰልጠን የነበረባቸው የዩኒቨርሲቲያችን ተማሪዎችም ተሳትፈውበታል። የስልጠናው አካሄድ በሁለቱ ስልጠናዎች የተካሄደው አይነት ሆኖ አሰልጣኞችም ቱተሮችም ከዩኒቨርሰቲው ሰራተኞች ውስጥ የተመደቡ ነበሩ። በዚህ ስልጠና የነበረው የተማሪዎች ብዛት በአማካይ 4250 ሲሆን ቁጥሩ ከቀን ቀን የተወሰነ ልዩነት ነበረው። ለአብነት ያህል በቅዳሜ 30/01/2007 የነበረው የተሳታፊዎች ቁጥር የሚከተለውን ይመስላል፤

ሰንጠረዥ 28. የአዲስ ተማሪዎች ስልጠና ተሳታፊዎች (መስከረም 30/2007)

| የስልጠና አዳራሽ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| የመመረቅያ አዳራሽ | 722 | 457 | 1179 |
| የምግብ ቤት አዳራሽ I | 398 | 431 | 829 |
| የምግብ ቤት አዳራሽ II | 503 | 401 | 904 |
| አዲሱ ላይብረሪ | 228 | 612 | 840 |
| ነባሩ ላይብረሪ | 221 | 313 | 534 |
| ድምር | 2072 | 2214 | 4286 |
| መቶኛ | 48 | 52 | 100 |

## 4.3. የትምህርት አሰጣጥ

ከቅርብ አመታት ወዲህ በስፋት በዩኒቨርሰቲዎች በኩል እየተተገበረ ያለው የማስተማር እና የነጥብ አሰጣጥ ዘዴ ማለትም የተከታታይ ምዘና ስርአት (Continuous Assessment)፤ ቋሚ መስፈርት መሰረት ያደረገ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት (Criterion Referenced Grading)፤ እንዲሁም ሞዱላር የማስተማር ስርአት (Modularized Curriculum) በዩኒቨርሲተያችን ስራ ላይ እየዋለ ነው። የተከታታይ ምዘናን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው የ60 – 40 አካሄድ ይጠቀማል። ይህም ማለት ከ60 የሚታሰቡ የተለያዩ አጫጭር ፈተናዎችና የቤትና የክፍል ስራዎች እየተሰጡ ቆይተው መጨረሻ ላይ ደግሞ ከ40 የሚታሰብ የመጨረሻ ፈተና (Summative Exam) ይሰጣል። በነዚህ ፈተናዎች የተገኙ ውጤቶች መሰረት በማድረግ ቋሚ መስፈርትን የተከተለ የውጤት አሰጣጥ እንከተላለን። የሞዱላራይዝድ ካሪከለም አተገባበር በተመለከተ ደግሞ በአብዛኛው ትይዩ በሆነው አካሄድ

(Parallel) እየተሰራበት ሲሆን በተወሰኑ ኮርሶች ደግሞ የብሎክ (Block) ኮርስ አሰጣጥ እየተተገበረ ይገኛል። የሞዱላራይዝድ ካሪከለም የላቀ ደረጃ ተደርጎ የሚወሰደው ኢንተግሬትድ (Integrated Modularized Curriculum) ገና ተግባር ላይ ያልዋለ ቢሆንም ስለአተገባበሩ ውይይት እየተደረገበት ይገኛል። በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን በአንዳንድ ትምህርቶች ለመጀመር ከወዲሁ እየታሰበበት ይገኛል።

የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በተለይም የተከታታይ ምዘና አካሄድ በተመለከተ በየጊዜው በመምህራን በኩል ጥያቄዎች የሚነሱ ሲሆን (ለምሳሌ በዝግጅት ስልጠና ወቅት በኢንጂነሪንግ አከባቢ ተከታታይ ምዘና መተግበር አስቸጋሪ አይሆንም ወይ የሚል ጥያቄ ተነስቶ ነበር) ከዚሁም በተጨማሪ በርካታ አዲስ አስተማሪዎች ስለተቀጠሩ በተለይ አዲስ የተቀጠሩ መምህራንን መሰረት ያደረገ የማስተማር ዘዴ ስልጠና (Induction Training) ተሰጥቷል። ስልጠናው የተሰጠው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከመጡ ልምድ ባላቸው በርካታ ባለሞያዎች ነበር። ስልጠናው የተከታታይ ምዘና፤ ቋሚ መስፈርትን መሰረት ያደረገው የነጥብ አሰጣጥ ስርአት፤ እና ሞዱላራይዝድ ካሪከለም መሰረት ያደረገ ሲሆን ባለሞያዎቹ ከፅንሰ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን ከተግባርም ጋር በማያያዝ ጠቃሚ ስልጠና ሰጥተውልናል። የመጀመርያ ቀን መጀመርያ ክፍል (First Day First Class) አተገባበር በተመለከተም በአንደኛ ሰሚስተር እና በሁለተኛ ሰሚስተር በጥሩ ሆኔታ ነው የተተገበረው። በጥሩ ሊተገበር የቻለበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ስለአስፈላጊነቱ ስምምነት ከተደረሰበት በኋላ በየደረጃው አስፈላጊ ክትትል ስለተደረገበት ነው።

### 4.4. ምርምር እና ህብረተሰብ አገልግሎት

በየአመቱ እንደሚደረገው ዘንድሮም በርካታ የምርምር ፕሮፖዛሎች ለውድድር ቀርበዋል። በ2007 የቀረቡት ፕሮፖዛሎች ብዛት 68 የነበረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በተደረገው መረጣ 47 የሚሆኑት ተመርጠው 2.16 ሚልዮን ባጀት ተመድቦላቸዋል ግማሽ የሚሆን ስራው ተገባዷል። የፀደቁ የምርምር ፕሮፖዛሎች ዝርዝርና የተመደበላቸው ባጀት በAppendix 6 ተመልክቷል። የምርምር ፕሮፖዛሎች አመራረጥ የሚደረገው በየኮሌጁ ከየትምህርት ክፍሉ በተቋቋሙት መራጭ ኮሚቴ አባላት ሲሆን ፕሮፖዛሎቹ በፅሁፍ ከቀረቡ በኋላ ግልፅ በሆነ መድረክ እንዲቀርቡ ይደረጋል። በኮሌጅ ደረጃ መረጣው ከተደረገ በኋላ በዲኖችና ዳይሬክተሮች ካውንስል የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል።

በ2006 ተመርጠው ባጀት ተመድቦላቸው የተካሄዱት የምርምር ፕሮፖዛሎች 26 የነበሩ ሲሆን እነዚህም ሰኔ 19 እና 20/2007 በተካሄደው የምርምር ቀን (Research Review Day) ተጠናቀው የተገኘው ውጤት በሙሉ እንዲቀርብ ተደርጓል (የቀረቡት ምርምሮች ዝርዝር Appendix 7 ላይ ይገኛል)። ከነዚህም በተጨማሪ በ2005 የተጀመሩና ወጤታቸው ቀደም ብሎ መቅረብ ከነበረበት ሶስት ምርምሮች ውስጥ ሁለቱ በምርምር ቀኑ እንዲቀርቡ ተደርገዋል። በዩኒቨርሰቲው ባጀት ከሚካሄዱት ጥናቶች በተጨማሪ ከክልሉ የፋይናንስና ፕላን ቢሮ ጋር በመተባበር Savings Behaviour in Tigray በሚል ርእስ የተደረገው የምርምር ስራ ደግሞ የምርምር ስራው ተጠናቆ የመጨረሻው ፅሁፍ ለቢሮው ተልኳል።

ከዚሁም በተጨማሪ በትምህርት አመቱ ሁለት አውደጥናቶች (ኮንፈረንሶች) የተከናወኑ ሰሆን በርካታ የምርምር ፅሁፎች ቀርበዋል። የመጀመርያው "International Workshop on Archeological Findings of Eastern Tigray and its Environs" በሚል ርእስ የተከናወነው አለምአቀፋዊ አውደጥናት ሲሆን የክልሉ ርእሰ መስተዳድር የተከበሩ አቶ አባይ ወልዱ በተገኙበትና ከአዲስ አበባ፤ ከመቀሌ፤ ከካናዳ እና ከዩኒቨርሲቲው የተውጣጡ ምሁራንና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት የተደረገ ነው። ሁለተኛው ደግሞ "ህልዊ ኩነታት ቋንቋ ትግርኛ" ወይም "ትግርኛ ቋንቋ ያለበት ሁኔታ" በሚል ርእስ ተከናወነውና አዲስ በተከፈተው የትግርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አዘጋጅነት ሰኔ 2007 ላይ የተካሄደ አገረ አቀፍ አውደ ጥናት ነው። በዚህ አውደ ጥናት ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል የተውጣጡ ምሁራን እና የሚድያ ሰዎች በርካታ ወረቀቶችን አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል።

ሰንጠረዥ 29፤ ተቀባይነት ያገኙ የምርምር ፕሮፖዛሎች (በኮሌጅ)

| ኮሌጅ | የፀደቁ ፕሮፖዛሎች ብዛት | የተመደበው ባጀት |
|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 9 | 361444.00 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 6 | 264011.42 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 6 | 287313.23 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 8 | 384639.80 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 7 | 325410.00 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብ | 11 | 541804.31 |
| ድምር | 47 | 2164622.76 |

ዩኒቨርሲቲው ለ2007 በእቅድ ከያዘው ውስጥ የምርምር መስኮችን (Research Thematic Areas) ልየታ ይገኝበታል። በዚሁም መሰረት የሚከተሉት የምርምር መስኮች በየደረጃው የተለዩ ሲሆን ወደ ሰኔት ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ የሚፀድቁ ይሆናል፤

- Quality of Education.
- Enhancing Food Security, Improving Farm Earnings livestock production and disease management, Honey, forest & plantation technology. Horticultural crops.
- Diagnosis of major maternal and child health issues, nutrition, HIV & FP interrelation, chronic non communicable disease.
- Environment, ecology and climate change, mitigation and adaptation and Natural Resource Management for Sustainable Development.
- Social Justice, Human rights, Governance and Democracy a means to improve livelihood
- Studies towards Poverty reduction, inequality and Development, budgeting, taxation financial intuitions, MSEs ,Micro – economic & policy issues.
- Engineering and Technology Testing and Adaptation (Water and sanitation, Renewable and sustainable Energy, construction materials and ICT divides), industry.
- Social issues and problems
- crosscutting themes

በየአመቱ እንደሚደረገው ዩኒቨርሲቲው በ2007ም የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በአመቱ የተደረጉት ዋና ዋና የማህበረሰብ አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው።

(1) በክልል ደረጃ በከተማው የሚከበረው የመስቀል በአል በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር የሩጫ ውድድር እና የፓነል ውይይት በማዘጋጀት በጥሩ ሁኔታ ተሳትፏል፡

(2) የከተማው ስፖርት ክበብ (ወልዋሎ ስፖርት ክለብ) ለማጠናከር የገንዘብ እና የስፖርት ማቴርያል ድጋፍ ተሰጥቷል፤ እንዲሁም የክለቡ ተጫዋቾች በዩኒቨርሲቲው ጂምናዝየም የዝግጅት ልምምድ እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸው ተጠቅመውበታል፤

(3) በህግ ትምህርት ክፍላችን አመካኝነት ለ175 ሰልጣኞች የመሬት ዳኝነት (ከጋንታ አፈሹም ወረዳ ለተውጣጡት 60 የመሬት ዳኝነት ስራ የሚሰሩ ዳኞች) እና በሴቶችና ህፃናት ሁኔታ ትኩረት ያደረገ ስልጠና (ከጋንታ አፈሹም እና ከዓዲግራት ከተማ ለተውጣጡ 115 የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች) ከታህሳስ 25 እስከ 26 የሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል።

(4) በአከባቢው ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጠው የበለስ ተክልን የሚያጠቃው ኮችኔል የተባለ በሽታ በተለይ በደቡባዊ የትግራይ አከባቢ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ሲሆን ችግሩ ወደ ምስራቃዊ ትግራይ የመግባት ምልክቶች እየታየ ስለሆነ በሽታው እንዳይስፋፋ ለመከላከል ከክልተ አውላዕሎ ወረዳ ግብርና ፅ/ቤት ጋር በመተባበር የመከላከል ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን፤

(5) በአከባቢያችንና በክልላችን ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ጋር በቴክኖሎጂ ሽግግር፤ በሰው ሃይል ልማት፤ በካይዘን አተገባበር፤ በማሽነሪ መዋዋስ እና በእሴት ሰንሰለት ዙርያ የመደጋገፍ ጅምር ስራዎች ተፈፅመዋል፤

(6) ከትግራይ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር በመተባበር ለቢሮው ሰራተኞች በGIS, AutoCad, SPSS, STATA እና Surveying ስልጠና ተሰጥቷል።

(7) ዘመናዊ የማጓጓዣ አገልግሎት በማይደርስባቸው የምስራቃዊ ዞን ቦታዎች (በተለይም ከዓዲቀለበስ አከባቢ ወደ ገናሕቲ እና ወደ ጉንዳጉንዶ አከባቢ በገመድ ትራንስፖርት (Caple Transport) ለማገናኘት ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ፤ ከዓዲግራት ካቶሊካዊት ቤተክርስያን የልማት ድርጅት፤ ከዞኑ አስተዳደርና ሂልቬታስ ከተባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በመተባበር ጅምር ስራዎች ተሰርተዋል። ጅምር ስራው ውጤት ላይ ሲደርስ ለአከባቢው ህብረተሰብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

(8) ለተለያዩ ማህበራት፤ ድርጅቶችና ፅህፈት ቤቶች የገንዘብና የማቴርያል ድጋፎች ተደርገዋል።

### 4.5. ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ

1. የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ያደርጋል። የሚደረገው ድጋፍ የገንዘብና የቁሳቁስ ሲሆን የገንዘብ ድጋፉ እስካሁን በሰሚስተር አንድ መቶ ብር የነበረ ሲሆን ከ2007 ጀምሮ የገንዘብ ድጋፉ በሰሚስተር 200 እንዲሆነ ተወስኖ እየተተገበረ ይገኛል። የኢኮኖሚ ችግር አለባቸው ተብለው ለዚሁ ስራ ተብሎ እና በስርአተ ፆታ ፅ/ቤት በሚመራ ኮሚቴ አመካኝነት ለሚለዩ ተማሪዎች ከገንዘቡ በተጨማሪ በማቴርያል መልክ የሚሰጣቸወ ሳሙና (የልብስና የገላ)፤ እስክርቢቶ፤ ደብተር ለወንድና ሴት ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪ ለሴት ተማሪዎች ፓንት፤ ቅባትና፤ ሞዴስ ይሰጣሉ። በዚሁም መሰረት በ2007 ከነባር ተማሪዎች ውስጥ ለ143 ሴት ተማሪዎችና ለ118 ወንድ ተማሪዎች በድምሩ ለ261 ተማሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው። ከአዲስ ተማሪዎች ውስጥ ደግሞ 179 ሴት ተማሪዎች እና 67 ወንድ ተማሪዎች በድምሩ 246 ተማሪዎች ተመርጠው ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ድጋፍ ሊደረግልን ይገባል ብለው ያመለከቱት አዲስ ሴት ተማሪዎች በሙሉ የድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተመርጠዋል። በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው ለ322 ሴቶች እና 185 ወንዶች በድምሩ ለ507 ተማሪዎች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። የኢኮኖሚ ድጋፍ ከሚደረግላቸው ውስጥ 63.5% የሚሆኑት ሴት ተማሪዎች ናቸው።

2. ከሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ መሰረት ለ30 ሴት ተማሪዎች በየወሩ 200.00 ብር ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል።

3. ፓዝ ፋይነደር በተባለው ግብረ ሰናይ ድርጅት አመካኝነት ለ30 ሴቶች የማቴርያል ድጋፍ (ሞዴስ፤ ፓንት፤ የገላና የልብስ ሳሙና) እየተደረገ ይገኛል።

4. በስድስቱ ኮሌጆች ለሚገኙ 3000 ያህል አዲስ ሴት ተማሪዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና ለሁለት ቀናት በስርአተ ፆታ ፅ/ቤትና በዩኒቨርሲቲው መምህራን ተሰጥቷል። የማሰልጠኛ ማንዋል በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ የተዘጋጀ ሆኖ ስልጠናው የወሰዱ መምህራን ይሄንን ስልጠና ለተማሪዎቻችን እንዲሰጡዋቸው ተደርጓል። ከዚሁም በተጨማሪ ኦሳ ትግራይ ከተባለ ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር በስነተዋልዶ እና ኤችአይቪ የሚያተኩር ስልጠና ለሁለት

ጊዜያት ያህል የአሰልጣኞች ስልጠና ለተማሪዎች ተሰጥቷል። በመጀመርያ ስልጠና የተሳተፉት 10 ወንዶችና 20 ሴቶች ሲሆኑ በሁለተኛው ዙር ደግሞ ስልጠናው ለ20 ሴቶች ተሰጥቷል።

5. ጥምረት ለህይወት በተባለ ግብረሰናይ ድርጅት አመካኝነት ለ23 ሴት ተማሪዎች በሴት ኮንዶም አጠቃቀም እና በአባለዘር በሽታዎች ዙርያ ስልጠና ተሰጥቷል።

6. የአካዳሚክ ውጤታቸው የበለጠ (በጣም ከፍ ያለ መአርግ) ደረጃ ያላቸው 63 ሴት ተማሪዎች ተለይተው የማበረታቻ ሽልማት (የሰርቲፊኬትና የገንዘብ) በዩኒቨርሲቲው ተደርጎላቸዋል።

7. ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመጡ ሴት የምክር ቤቱ አባላት አሰልጣኝነት ታህሳስ 4 እና 5/2007 ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በሙሉ የሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጥተዋል። ስልጠናው የተሰጠው "የሴቶች ሁለገብ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በተለያዩ ስርአቶች" እና "የሴት ተማሪወች ገፅታና የህይወት ክህሎት" በሚሉ ርእሶች ሲሆን ቀደም ብሎ ተመሳሳይ ስልጠና ለዩኒቨርሲቲው ሴት መምህራን መቐለ (በክልሉ ያሉት ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ሴት መምህራን የተገኙበት) ላይ ተደርጎ ስለነበረ የዩኒቨርሰቲው ሴት መምህራን በዚህ ለተማሪዎች በተሰጠው ስልጠና የቡድን አወያዮች (ቱተሮች) በመሆን ውጤታማ ስራ ሰርተዋል።

8. በትምህርት ክፍል አመዳደብ ለሴት ተማሪዎች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። በዚሁም መሰረት 25% የሚሆኑ ቦታዎች ለሴቶች ብቻ ያለውድድር እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

## 4.6. የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ግቦችና የዩኒቨርሲቲው አፈፃፀም

በ2003 ጀምሮ ላለፉት አምስት አመታት ሲተገበር የቆየው የመጀመርያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (Growth and Transformation Plan – GTP) በ2007 የተጠናቀቀ ሲሆን ለሚቀጥሉት አምስት አመታት የሚያገለግለው የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዝግጅት እየተጠናቀቀ ይገኛል። ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲም የመጀመርያው እቅድ ውጤት መሆኑ እዚህ ላይ ማውሳቱ ተገቢ ነው። በመጀመርያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለከፍተኛ ትምህርት ከተያዘው ታርጌት አኳያ የዩኒቨርሲቲያችን አፈፃፀም ምን እንደሚመስል መቃኘቱ ተገቢ ስለሆነ አጠር ባለ መልኩ እንዲሚከተለው ቀርቧል።

1. የመምህራን ስብጥር፤ በእቅዱ ዩኒቨርሲቲዎች ሊደርሱበት ይገባል ተብሎ የተያዘው የዩኒቨርሰቲ መምህራን ስብጥር 75% የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው እንዲሆኑና 25% ደግሞ የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው እንዲሆኑ ነው። በዚህ መሰረት ሲታይ ዩኒቨርሲቲያችን ይሄንን ታርጌት የደረሰበት አይደለም ብቻ ሳይሆን ከግቡ የራቀ መሆኑ ማየት ይቻላል። በሪፖርቱ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በስራ ላይ ያሉትን የአገር ውስጥ መምህራን (የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎችን ሳንጨምር) ብቻ ከወሰድን ስራ ላይ ካሉት 414 መምህራን ውስጥ 41.8% የሚሆኑት የመጀመርያ ዲግሪ ያላቸው ሲሆኑ 57.5% ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። የሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው ደግሞ 0.7% ናቸው። በርግጥ የውጭ አገር መምህራን ጨምረን ስናይ ቁጥሩ የተሻለ ነው። ያም ሆኖ ስብጥሩ 37.9%፤ 55.8% እና 6.3% ይሆናል እንጂ ከተቀመጠው ታርጌት ጋር ሲነፃር በጣም የራቀ መሆኑ ማየት ይቻላል። ደግነቱ በርከት ያሉ መምህራን ለሶስተኛ ዲግሪ የተላኩ ስለሆነ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን መጨረሻ ወቅት አሁን ካለንበት ሁኔታ ጋር ሲነፃር ወደ ታርጌቱ በጣም በተሻለ መልኩ የቀረበ እንደሚሆን ከወዲሁ መገመቱ አያዳግትም። በተለይም የሁለተኛ ዲግሪ መምህራኖቻችን ብዛት ወደ ተፈለገው ታርጌት የማይደርስበት ምክንያት አይኖርም።

2. የመምህር ተማሪ ጥምርታ (Teacher – Student Ratio): በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ ሊደረስበት የተፈለገው የመምህር ተማሪ ጥምርታ 1፡20 ነው። ጥምርታው የሚሰላበት ዘዴ የተለያየ ቢሆንም በስራ ላይ ያሉት መምህራንን ብቻ በመውሰድ (የቴክኒክ ደጋፊዎችን ሳንጨምር) በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የመምህር ተማሪ ጥምርታ 21.97 ነው። በዚሁ ላይ የቴክኒክ ደጋፊዎችን ጨምረን ስናየው ጥምርታው 20.37 ይሆናል። ስለሆነም ጥምርታውን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው ከታርጌቱ በጣም የተቀራረበ ደረጃ እንዳለው ማየት ይቻላል።

3. የምረቃ ምጣኔ፤ በእቅዱ የተቀመጠው የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የምረቃ ምጣኔ በአማካይ 93% የሚል ሲሆን ለወንዶች 95% ለሴቶች ደግሞ 90% በሚል ነው የተቀመጠው። ይሄንን ታርጌት በተመለከተ የዩኒቨርሲቲው ደረጃ መለካት አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ዩኒቨርሲቲው እስካሁን አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያስመረቀው። ስለዚህ በተዘዋዋሪ መልኩ ውጤቱን ለማየት በየጊዜው ከትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች መጠን ማየት እንችላለን። በዚሁም መሰረት በ2006 የነበረው የማቋረጥ መጠን 7.16 የነበረ ሲሆን በ2007 ወደ 5.13 ሊቀንስ ችሏል። ከዚህ ውስጥ አብዛኛው የሚያቋርጥ ተማሪ በራሱ ውሳኔ ሳያስፈቅድ ለቆ የሚሄድ (Drop out) ነው። ቀጥሎ በትምህርት ድክመት የሚያቋርጥ (Academic Dismissal) ሆኖ የመጨረሻው ደግሞ በአግባቡ አሳውቆ ማቋረጥ (Withdrawal) ነው። በተለይ በሁለተኛውና ሶስተኛው አይነት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ተመልሰው ትምህርታቸውን የመቀጠል እድል ስላላቸው ጊዜ ይወስድ እንደሆነ እንጂ የመመረቅ እድሉ ክፍት ነው። ስለዚህ የምረቃ ምጣኔን በተመለከተ እየተሻለ የመሄድ አዝማምያ መኖሩን ብቻ በማስቀመጥ ሊገለፅ የሚችል ይሆናል። ዩኒቨርሰቲው ተጨማሪ አመታትን ሲያስመርቅ ምጣኔውን በትክክል ማስቀመጥ ይቻላል።

4. የቅድመ ምረቃ ሴቶች ተሳትፎ መጠን፤ በአምስት አመቱ እቅድ የቅድመ ምረቃ ሴቶች ተሳትፎን አስመለክቶ የተቀመጠው ግብ 40% የሚል ነው። በዚህ አንፃር በዩኒቨርሲቲያችን ያለው ሁኔታ እቅዱን ያሳካ (ምናልባትም አልፎ የሄደ) ተብሎ ሊቀመጥ ይችላል። በ2007 ሁለተኛ ሰሚስተር ላይ ያለው የሴቶች ተሳትፎ ምጣኔ 41.4 ነው። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው ይሄንን ግብ ደርሶበታል።

5. የድህረ ምረቃ ሴቶች ተሳትፎ፤ ዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የጀመረው በ2007 በሁለት ፕሮግራሞች ብቻ ስለሆነ አሁን ባለበት ሁኔታ ስለ ድህረ ምረቃ ሴቶች ተሳትፎ ያለው ምጣኔ ማቅረቡ ጠቀሜታው አነስተኛ ነው። ሆኖም በመደበኛም በማታም ያሉንን 108 ተማሪዎች በመውሰድ የሴቶች ተሳትፎ በእቅዱ ከተመጠው የ25% ጋር ሲነፃፀር 8.3% ብቻ ነው።

6. የ70፡30 ቀመር፤ በእቅዱ የተቀመጠው ሌላ ግብ በቅድመ ምረቃ መርሃግብር የተፈጥሮ ሳይንስ (ከባንድ 1 እስከ 4) ተማሪዎች ብዛት 70% እና የማህበራዊ ሳይንስ (ባንድ 5 እና 6) ተማሪዎች ብዛት 30% መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል። በየባንዱ የሚኖረው ስብጥርም እንዲሁ የተቀመጠ ሲሆን ዝርዝሩ በዚህ ሪፖርት ቀደም ብሎ የተመለከተ ሲሆን አጠቃላይ ቀመሩን በተመለከተ በዩኒቨርሰቲያችን ያለው ስብጥር 71.54% በተፈጥሮ ሳይንስ እና 28.46% በማህበራዊ ሳይንስ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው ይሄንን ታርጌት የደረሰበት መሆኑ መገንዘብ ይቻላል።

## 4.7. የ2007 የስራ ዘመን አመታዊ የስራ የአፈፃፀም ሰንጠረዥ

| ግቦች | ሊሰሩ የታቀዱ ዝርዝር ስራዎች | አመታዊ የአፈፃፀም ማብራርያ እና በመቶኛ ሲገለፅ | እቅዱን በመፈፀም ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ሁኔታዎች | የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. የዝግጅት ምእራፍ ስራዎችን በተገቢው በመከወን በድምሩ አስራ አንድ ሺ ያህል መደበኛ ተማሪዎችን (5000 አዲስና 6000 ነባር) ማስተናገድ የሚችል አቅም በመፍጠር የአመቱን ስራ መጀመር | 1.1 የዩኒቨርሲቲው የ2007 እቅድ አሳታፊ በሆነ መልኩ ማዘጋጀት፤ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የየክፍላቸውን እቅድ ያዘጋጃሉ፤ በእቅዶቹ ላይ መግባባት በመፍጠር ወደ ዝርዝር አፈፃፀም መግባት | የ2006 አፈፃፀም ግምገማ ሰኔ 28/2006 በሚደረግበት ጊዜ የ2007 መነሻ እቅድ አብሮ እንዲቀርብ ተደርገኳል። በ2006 ክረምት ላይ ደግሞ የ2007 ዝርዝር እቅድ ተዘጋጅቶ በቦርድ ውይይት ተደርጎበት ፀድቋል። በእቅዱ ላይም ጠቅላላ የዩኒቨርሲቲው መምህራን እና ሰራተኞች የተሳተፉበት መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይትና መግባባት ተደርጎበታል። የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች ደግሞ ከዩኒቨርሲቲው እቅድ የሚሄድ የየራሳቸውን እቅድ አዘጋጅተዋል። የዝግጅት ምእራፉንና የትግበራ ምእራፉን በተገቢው ሁኔታ በማከናወን የማጠቃለያ ምእራፉም በተመሳሳይ አኳሃን እንዲፈፀም ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.2. የዝግጅት ስልጠናዎችን ማከናወን (የመምህራን፤ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና የተማሪዎች የመንግስት ፖሊሲዎች፤ ስትራቴጂዎችና አቅጣጫዎች እና ሰላማዊ መማር ማስተማርን በተመለከተ ሰፋፊ ስልጠናዎች ማዘጋጀትና ማስፈፀም)፤ ለመምህራን የሚሰጥ የዝግጅት ስልጠና (Induction Training); የህይወት ክህሎት ስልጠና ለሴት ተማሪዎች መስጠት | ሰፋፊ የዝግጅት ስልጠናዎች ተከናውነዋል። ስልጠናዎቹ በሶስት ተከፍለው ነበር የተከናወኑት። ከነሃሴ 15 እስከ 30 በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሚማሩ እና ነዋሪነታቸው በዩኒቨርሲቲው አከባቢ በሚገኙ ወረዳዎች ነዋሪ የሆኑ 5500 ያህል ነባር ተማሪዎች የተሳተፉበት እና በአራት ርእሶች ዙርያ (ማለትም የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግልና አገራዊ ህዳሴያችን፤ የተሃድሶ መስመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ፤ የልማታዊ ስርአት ግንባታ ትግላችንና ፈተናዎቹ፤ ህገ መንግስታዊ መርሆዎችና ሰላማዊ የትግል ስልት በትምህርት ተቋማት) ስልጠና ተሰጥቷል። ሁለተኛው ስልጠና ደግሞ መስከረም 10/2007 የተጀመረው እና ለአስር ቀናት የዘለቀው ስልጠና ለዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች የተሰጠ ነው። ይህ ስልጠና በሶስት ርእሶች (አራተኛው ርእስ ሳይጨምር) የተከናወነ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው አሰራርና አፈፃፀም በተመለከተም ግምገማዊ ውይይት ተካሂዶበታል። በዚህ ስልጠና | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የተሳተፊው ሰራተኛ በአማካይ 1000 ነበር። ሶስተኛው ስልጠና ደግሞ ለአዲስ ተማሪዎች የተሰጠ ሲሆን ስልጠናው የተደረገው ከመስከረም 28/2007 ጀምሮ ለአስር ቀናት የተካሄደ ነበር። በዚህ ስልጠና 4250 ተማሪዎች ተሳትፈውበታል። ከነዚህ ስልጠናዎች በተጨማሪ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ባለሞያዎች በተገኙበት በማስተማር ዘዴዎች (ተከታታይ ምዘና፤ ቋሚ መስፈርት ያደረገ የነጥብ አሰጣጥ፤ ሞዱላራይዝድ ካሪኩለም) የመግቢያ ስልጠና (Induction Training) ተሰጥቷል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.3. ተማሪዎች እርስ በርስ የሚደጋገፉባቸው የአንድ ለአምስት መረቦች (Cooperative Learning Teams) እና የልማት ቡድኖች እንዲደራጁ ማድረግ፤ ቤተመፃህፍቶች ተማረዎች በቡድን እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል አሰራር አጠናክሮ መቀጠል፤ የተማሪዎች የክፍል ተወካዮችን ማስመረጥ | በአመቱ አንደኛ ሰሚስተር ላይ 1982 በሁለተኛው ሰሚስተር ደግሞ 1879 የተማሪዎች የአንድ ለአምስት ቡድኖች (Cooperative Learning Teams) ተመስርተው ተማሪዎቹ በነዚህ ቡድኖች አመካኝነት እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ ተደርጓል። እነዚህ ቡድኖች ደግሞ በአንደኛው ሰሚስተር በ202 በሁለተኛው ሰሚስተር በ197 የልማት ቡድኖች (አንድ ክፍል አንድ የልማት ቡድን ነው) የተደራጁ ሲሆን ለያንዳንዱ የልማት ቡድን ደግሞ አንድ ደጋፊ መምህር (mentor) ተመድቦላቸዋል። የተማሪዎቹ የአንድ ለአምስት ቡድኖች እቅድ በማውጣትና በየሳምንቱ የሚገናኙበትን ፕሮግራም በማውጣት በዩኒቨርሲቲው ቤተመፃህፍት እና የመማርያ ክፍሎች በየጊዜው እየተገናኙ አብረው ይሰራሉ። ከዚሁም በተጨማሪ ተማሪዎች ሁለት ሁለት የክፍል ተወካዮች (ቢያንስ አንድዋ ሴት መሆን አለባት) እንዲመርጡ ተደርጎ በነዚህ ተወካዮች አመካኝነት ከትምህርት ክፍሉ ሃላፊ እንዲሁም በትምህርት ክፍል ካውንስል እና በኮሌጅ ካውንስል እንዲሳተፉ ይደረጋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.4. አምስት ሺ ያህል አዲስ መደበኛ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችለን ሰብአዊና | በ2007 አዲስ እንቀበላቸዋለን ብለን በእቅድ የያዝነው 5000 ያህል ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህን ለመቀበል የሚያስችሉ የመማርያ እና የመኝታ | በተለይ ተጨማሪ የስራ መደቦች እንዲፈቀዱልን | ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ውይይት በማካሄድ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ማቴርያላዊ ዝግጅቶችን ማድረግ። የመምህራን ቅጥርና ዝውውር ማከናወን፤ የ480 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ተጨማሪ ቅጥር ማካሄድ (የቅጥር መደብ ያልፀደቀላቸው 331 ቦታዎች ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴርን በማስፈቀድ ቅጥሮች እንዲካሄዱ ማድረግ)፤ ግንባታዎች በወቅቱ መጠናቀቃቸው መከታተል፤ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ግዥዎችና አቅርቦቶች (አልጋ፤ ፍራሽ፤ ጠረጴዛ፤ ወንበር፤ ወዘተ) መሟላታቸውን ማረጋገጥ | ክፍሎች፤ አልጋ፤ ወንበር፤ ፍራሽ፤ ወዘተ እንዲሁም ተፈላጊ መምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች መቀጠር ነበረባቸው። በዚህም መሰረት በቂ የመማርያና የመኖርያ ክፍሎች ለተማሪዎች ቅበላ ደርሰውልናል። የአልጋና ወንበር ፍራሽና ሌሎች አቅርቦቶችም እንዲሁ በ2006 መጨረሻ ላይ ጨረታ አውጥተን ስለነበር ደርሰውልናል። የመምህራን አቅርቦት በተመለከተም በቅጥር (ከአገር ውስጥም ከውጭም)፤ በዝውውር እና በምደባ (ከትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡልን) በድምሩ 231 ተጨማሪ መምህራን ተገኝተዋል። የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በተመለከተ ወደ 331 የሚሆኑ የስራ መደቦችን ከሲቪል ሰርቪስ በማስፈቀድ እና ቀደም ብሎ በተፈቀደው መዋቅር ያልቀጠርናቸው ሰራተኞችን ጨምሮ 480 ሰራተኞች ለመቅጠር እቅድ የተያዘ ቢሆንም በ2007 ያሉት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በ2006 ከነበረው ያሳየው ጭማሪ 205 ብቻ ነው። የተጨመሩ ሰራተኞች ከታቀደው ያነሰበት አንደኛው ምክንያት ተጨማሪ የስራ መደቦችን የማስፈቀዱ ስራ ጊዜ በመውሰዱ ነው። ጥያቄው ቀደም ብሎ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የቀረበ ቢሆንም ቢፒአር ሳታዘጋጁ አይፈቀድም የሚል መልስ ስለተሰጠን እንደገና ጥያቄያችንን እስከነዝርዝር ምክንያቱ ማቅረብ ነበረብን፤ ካቀረብን በኋላ ግን ተፈቅዶልናል። (አፈፃፀም 90%) | በወቅቱ ጥያቄ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አቅርበን የነበረ ቢሆንም ቢፒአር ሳይሰራ ሊፈቀድ አይችለም የሚል መልስ ስለተሰጠን ተጨማሪ ቦታዎች የማስፈቀዱ ጉዳይ በወራት ዘግይቶብናል። | አዳዲስ ለምንጠይቃቸው የስራ መደቦች ዘርዘር ያለ ማክንያት (justification) በማቅረብ እንደገና እንድንጠይቅ በተሰጠን አቅጣጫ መሰረት በዚሁ መሰረት አቅርበን ተጨማሪ የስራ መደቦች ተፈቅደውልናል። |
| | 1.5. የግቢ ማስዋብ ስራዎችን ማከናወን [የክረምት ተከላ ማካሄድ፤ በተማሪዎች ካፌቴርያ ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ የማሳመር (landscaping) ስራ መስራት፤ የጣራ ውሃ ለመጠቀም የሚያስችሉ ስትራክቸሮች (roofwater harvesting structures) መስራት፤ | የክረምት ተከላ ፕሮግራም ተይዞለት ተከናውኗል፤ የጣራ ውሃ ለማጠራቀም የሚያስችል ስራ በአንድ ቦታ ላይ የተጀመረ ቢሆንም ገና አልተጠናቀቀም፤ Green Ethiopia ከሚባል ገባሬ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር የችግኝ ማፍያ ጣብያ ለመስራት ተችሏል። በተማሪዎች ካፌቴርያ ፊት ለፊት ያለው ቦታ የማስዋብ ስራም የራሱ ዲዛይን ተይዞለት በ2008 የሚሰራ ይሆናል። (65%) | የጣራ ውሃን ለማጠራቀም የሚያገለግል ጉድጓድ ስራ በቀዳሚው ቤተመፃህፍት አከባቢ የተጀመረ ቢሆንም ቦታው አለታማ ስለሆነ | የጣራ ውሃ የማጠራቀሙ ስራ የራሱ የሆነ ዲዛይን ተሰርቶለት በውድድር መልክ እንዲሰራ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ለሚቀጥለው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በሁለተኛው ግቢ የችግኝ ማፍያ ጣብያ ማደራጀት] | | በእጅ መስራት አልተቻለም። | አመት ተሸጋግሯል። |
| | 1.6. የክረምት ተማሪዎችን መቀበልና ማስተናገድ [2006 ክረምት ላይ 2500 ያህል ተማሪዎችን ማስተናገድ፤ ከነዚህ ተማሪዎች አብዛኛዎቹ አዲስ በምንጀምረውና ከክልሉ የቴክኒክና ሞያ ኮሌጆች የተውጣጡና በቴክኖሎጂ የመጀመርያ ዲግሪ የሚማሩ ተማሪዎች ይሆናሉ፤ ከትምህርት ሚኒስቴር ለድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ወይም PDGT የሚላኩልን ተማሪዎች ሲሆን ይሄም ዘንድሮ የሚጀመር አዲስ ፕሮግራም ነው። ቀደም ብለው የተጀመሩት የክረምት ትምህርት ፕሮግራሞችም የሚቀጥሉ ይሆናል። ከዚህም ሌላ በክልሉ ምስራቃዊ ዞን እና በዓፋር ክልል አጎራባች ወረዳዎች ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ ጎበዝ ተማሪዎች በሂሳብና ሳይንስ ትምህርቶች መሰረት ያደረገው የክረምት አውትሪች ፕሮግራም የሚካሄድ ይሆናል ] | በእቅዱ መሰረት በርካታ የክረምት ተማሪዎችን በተለያዩ ፕሮግራሞች ተቀብለን አስተምረናል። በዚሁም መሰረት ከክልሉ የቴክኒክና ሞያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ባችለር ዲግሪ (Btech) ፕሮግራም በ13 የትምህርት መስኮች 1168 ተማሪዎችን ተቀብለን አስተምረናል። ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ደግሞ የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ፕሮግራም (PGDT) ተማሪዎችን ተቀብለን አስተናግደናል። ከዚሁም በተጨማሪ ቀደም ብለው በትምህርት ሚኒስቴር ስፖንሰርነት፤ በክልሉ ጤና ቢሮ ስፖንሰርነት፤ እና በራሳቸው ወጪ የሚሸፍኑ ተማሪዎችም በክረምት ፕሮግራማችን በድምሩ 2320 ተማሪዎችን በማስተማር ላይ እንገኛለን። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.7. የአመቱን የአካዳሚክ መርሃ ግብር ማውጣትና ማስፀደቅ | የአመቱ የትምህርት መርሃ ግብር በዩኒቨርሲው ረጂስትራር አዘጋጅነት ቀርቦ በሰኔት ውይይት ተደርጎበት እንዲሻሻል ተደርጎ ፀድቋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.8. አዲስ ለተመደቡ ተማሪዎች ኦርየንቴሽን መስጠት፤ የዩኒቨርሲቲው የዲሲፕሊን | ለአዲስ ተማሪዎች ሰፋ ያለ ኦርየንቴሽን ተሰጥቷል፤ የትምህርት ክፍል መረጣም ተከናውኗል። (አፈፃፀም 100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መመርያ ማሰራጨት፤ የትምህርት ክፍል መረጣ ማድረግ | | | |
| | 1.9. የዩኒቨርሰቲው የመጀመርያ የምረቃ ፕሮግራም በደመቀ አኳሃን ሃምሌ 2006 ላይ ማከናወን | የዩኒቨርሲቲው የመጀመርያው ምረቃ ፕሮግራም ሃምሌ 12/2006 በጣም በደመቀ እና ታሪካዊነቱን ሊያንፀባርቅ በሚችል መልኩ ተከናውኗል። (100%) | | |
| | 1.10. የተጠናከረ የማባዣ ክፍል በማደራጀት ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙትን መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች ማዘጋጀትና ማቅረብ፡ መፃህፍትን በሶፍት ኮፒ ማሰባሰብ | ዩኒቨርሲቲው የተጠናከረ የማባዣ ክፍል ስላለው አስፈላጊ የሆኑ መፃህፍትና ማቴርያሎች በዚሁ ክፍል አመካኝነት እየተባዙ ቤተመፃህፍት ውስጥ እንዲቀመጡ ይደረጋል። ሆኖም ትምህርት ሊጀመር አከባቢ የወረቀት አቅርቦት እጥረት አጋጥሞ ስለነበር የማባዛቱ ስራ በሚፈለገው መልኩ ሊሄድ አልቻለም ነበር። በሶፍት ኮፒ የሚገኙ መፃህፍት ደግሞ ባለው ዲጂታል ላይብረሪ እንዲቀመጡ ተደርገዋል። (አፈፃፀም 90%) | ስራው በአንድ ማእከል (ማለትም በቤተ መፃህፍት) የሚከናወን ስለሆነ ቅልጥፍናውን የበለጠ ለማድረግ ወደየኮሌጆች መውረድ ይኖርበታል | የማባዛት ስራው ከ2008 ጀምሮ በየኮሌጁ እንዲሆን የሚያስችል መዋቅር በማዘጋጀትና ሰራተኛ በመቅጠር የሚሰራ ይሆናል |
| ግብ 2. የግንባታ ስራዎች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸው መከታተል፣ ያለቁትን ጥቅም ላይ ማዋል፣ አዳዲስ ግንባታዎችን ማከናወን | 2.1 ከሶስተኛ ዙር ግንባታዎች ያልተጠናቀቁትን ማጠናቀቅ፤ በአራተኛ እና አምስተኛ ዙር መሰራት ካለባቸው ደግሞ በድምሩ 56 ብሎኮችን (እና የመሰረተ ልማት ስራዎች) ግንባታ መጀመርና መከታተል | ከሶስተኛ ዙር ግንባታ ውስጥ ቆየት ብለው (ማለትም 2006 ማለቂያ አከባቢ) የተጀመሩት 7 ህንፃዎች አፈፃፀማቸው 96.05% ደርሷል። በተለይም ለተማሪዎች ቅበላ አስፈላጊ የነበሩት የምግብ ቤት አዳራሽ (Dining Hall) እና የእንጀራ መጋገርያ በወቅቱ ደርሰውልናል። የአራተኛ እና የአምስተና ዙር ግንባታዎችን በተመለከተ በዋናው ግቢ 23 ብሎኮች ተጀምረው ወደ መጠናቀቅ ደረጃ ላይ ስለደረሱ (እስከ ሰኔ ያለው አፈፃፀም 85.77% ደርሷል) ለ2008 የተማሪዎች ቅበላ በወቅቱ ዝግጁ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። በሁለተኛው ግቢ የሚሰሩት የአምስተኛ ዙር 33 ብሎኮች ደግሞ ዘግይቶም ቢሆን (ማለትም ሰኔ ላይ) ስለተጀመሩ ለ2008 ሁለተኛ ሰሚስተር እንደሚደርሱ ይጠበቃል። የሁለተኛው ዙር መሰረተ ልማት ስራዎች አፈፃፀም 62% ነው። የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት አፈፃፀም ግን ከሚጠበቀው በታች ነው (30.34%)። (አፈፃፀም 85%) | የፍሳሽ ማጣርያ ግንባታ በተመለከተ ዘግይቶ የተፈታ ቢሆንም ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ በተነሳው ክርክር ከቦታው ማንሳት ይገባቸው የነበሩ ህጋዊ ያልሆኑ ግንባታዎች በወቅቱ ባለማንሳታቸው የግንባታውን ሂደት ጎድቶታል። በሁለተኛው ግቢ ስለሚደረገው ግንባታ ደግሞ ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ ገና ያልተፈቱ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን በተጨማሪም አማካሪ ድርጅት አቀጣጠር እና ዲዛይን አዳፕቴሽን የራሱን ጊዜ ወስዷል። | ከሚመለከታቸው የዞን እና የወረዳ አስተዳደር አካላት ጋር በመተባበር ከካሳ ክፍያ በዋናው ግቢ ለተነሱት ችግሮች መፍትሄ ተበጅቶላቸው የፍሳሽ ማጣርያ ስራው በሙሉ ሃይል እንዲጀመር ተደርጓል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2.2. በሁለተኛው ግቢ የግንባታ ስራዎችን መጀመር (33 ብሎኮችና የመሰረት ልማት ስራዎች) | በ2.1 እንደተቀመጠው በሁለተኛው ግቢ ይጀመራሉ ተብለው የታሰቡት 33 ብሎኮች በአመቱ መጨረሻ አከባቢ የተጀመሩ ቢሆንም የመሰረት ልማት ስራዎች ግን ገና አልተጀመሩም። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 2.3. ለሁለተኛው ግቢ የሚሆን አማካሪ በጨረታ መለየትና መቅጠር | ለሁለተኛው ግቢ የሚሆን አማካሪ ጨረታ ወጥቶ የጨረታ ትንተና (የቴክኒክና የፋይናንስ) ተደርጎ አሸናፊ ድርጅት ተለይቶ ሰራው እየተከናወነ ይገኛል። (100%) | | |
| | 2.4 የዋናው ግቢ አጥር ስራ ማከናወን፣ በዋናው ግቢ ምእራብ በኩል የሚገኘው መንገድ የኮብልስቶን ስራ ማከናወን | የዋናው ግቢ አጥር በአማካሪው ዲዛይን ተሰርቶ፤ ሶስት ኮንትራክተሮች ተመርጠው የአጥር ስራው እየተከናወነ ይገኛል። የክትትል ስራው በዋናው ግቢ አማካሪ ድርጅት ተቆጣጣነት የሚከናወን ሲሆን ለኮንትራክተሮች ከመሰጠቱ በፊት በቁርጥ ዋጋ አሰራር መሰረት መፅደቅ ስለነበረበት ተሰርቶ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር እና ወደ ቤቶችና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተልኮ የመዘግየት እክል የነበረው ቢሆንም ፀድቆ የግንባታ ስራው እየተከናወነ ነው። ከ2008 ተማሪዎች ቅበላ በፊት ይጠናቀቃል የሚል ግምት አለን። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 2.5. ተጨማሪ አራት የውሃ ጉድጓዶች ቁፋሮ ማከናወንና የተወሰኑትን ወደ ዩኒቨርሲቲው መስመር መዘርጋት | አራት ጥልቅ የውሃ ጎድጓዶች በባለሞያዎች ተጠንተውና ተለይተው የቀረቡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ላይ ብቻ ነው የቁፋሮ ስራ በክልሉ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን አመካኝነት የተከናወነው። የበለጠ ግምት ተሰጥቶበት የነበረው መገብ በሚባለው ለዩኒቨርሲቲው ቅርብ በሆነ አከባቢ የተቆፈረው ጉድጓድ ውጤቱ የተወሰነ ውሃ (3.5 ሊትር በሰከንድ) የተገኘበት ቢሆንም እንደተጠበቀው ግን ሊሆን አልቻለም። ሁለተኛው ጉድጓድ ማይ ፃዕዳ በሚባል ከዩኒቨርሲቲው ራቅ ብሎ በሚገኝ መንደር የተደረገው ቁፋሮም ከመጀመርያው ያነሰ ውጤት (ማለትም 1.5 ሊትር በሰከንድ) የተገኘበት ነው። ሶስተኛው ጉድጓድ ሊቆፈር ታስቦ የነበረው ከሁለተኛው ቦታ አጠገብ ሲሆን የሁለተኛው ውጤት ጥሩ ሳይሆን ሲቀር ሶስተኛውም እንዲቀር ተደርጓል። አራተኛ ጉድጓድ | ጥልቅ ጉድጓዶችን በመቆፈር ዘላቂ መፍትሄ የማፈላለግ ስራው ስላልተሳካ ጊዚያዊ መፍትሄ መፈለግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። | በግቢው ውስጥ የውሃ ገንዳዎችን (ሮቶውችን) በብዛት በማስቀመጥ በውሃ ቦቴ እንዲሞሉ በማድረግ ችግሩን ለማቃለል ተችሏል ። በሳምንት ሁለት ጊዜ ደግሞ ቀደም ብሎ ስንጠቀም ከነበሩት ጉድጓዶች በፓምባ እንዲቀርብም ተደርጓል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እንዲቆፈር የታሰበው ለዋናው ግቢ ሳይሆን ለሁለተኛው ግቢ ቅርብ በሆነ ቦታ ኒሕቢ በሚባል መንደር ተመርጦ የነበረ ቢሆንም ቦታው ቀደም ብሎ ለኢንቨስተር ተሰጥቶ የነበረ መሆኑ ሲታወቅ ቁፋሮው ሊቀጥል አልቻለም። በድምሩ ሲታይ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። በዚሁም ምክንያት ለ2008 ምርትን መሰረት ያደረገ (per product) የጉድጓድ ቁፋሮ ስራ እንዲሰራ የጨረታ ዶኩመንት ተዘጋጅቷል። ለውሃው ችግር ደግሞ ጊዚያዊ መፍትሄ በማበጀት በቦቴ እንዲቀርብ ተደርጓል። ( አፈፃፀም 65%) | | |
| | 2.6 የማኔጅመንት ህንፃ የዲዛይን ስራ በማጠናቀቅ የግንባታ ስራ መጀመር | ይህ እቅድ በዋናነት በሶስተኛውና በአራተኛው ሩብ አመት እንዲሰራ ተይዞ የነበረ ሲሆን የግንባታ ፅ/ቤታችን በሌሎች ሰራዎች ስለተጠመደ ጅምር ስራዎች የተከናወኑ ቢሆንም የዲዛይን ስራው ሊከናወን አልቻለም። ሰራው በ2008 የሚከናወን ይሆናል። (አፈፃፀም 30%) | | |
| | 2.7 በተማሪዎች ምግብ ቤት አዳራሽ ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ ለማስዋብ የላንድስኬፒንግ ዲዛይን እና ግንባታ ስራዎችን ማከናወን | የዩኒቨርሲቲው ግቢ በተክሎች የማስዋብ ስራ በተለያዩ ቦታዎች እንዲከናወን ተደርጓል፤ ከአመት አመትም የግቢው ውበት እየተሻለ መጥቷል። በተጠቀሰው ቦታ የተያዘው እቅድ የራሱ የሆነ የዲዛይን ስራ የሚያስፈልገው ስለሆነ በ2008 እንዲሰራ ይደረጋል። (አፈፃፀም 40%) | | |
| | 2.8 የተሰራው የስብሰባ አዳራሽ (ኦዲተርየም) ለስብሰባ ምቹ በሆኑ ወንበሮችና ሌሎች ማቴርያሎች ማሟላት | የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራውን በተመለከተ የስፔሲፊኪኬሽን ዝግጅት ተጠናቆ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጓል። አሸናፊውን ለመለየት የቴክኒክና የፋይናንስ መረጣ እየተደረገ ነው። (አፈፃፀም 45%) | | |
| | 2.9. ተጀምረው ያላለቁ ሆነው ዩኒቨርሲቲው የገዛቸው የኮንደሚንየም ቤቶች አስፈላጊው የርክክብ ስራዎችን በማጠናቀቅ ለመምህራን መኖርያ ጥቅም ይውሉ ዘንድ አስፈላጊው ጨረታ በማውጣት የግንባታ ስራዎችን ማከናወን | የነዚህ ያላለቁት የኮንደሚንየም ቤቶች ርክክብ ተከናውኗል። እያንዳንዱ ብሎክ ምን ስራ እንደሚጎድለው ተለይቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል። በምን አይነት ማቴረያሎች የፊኒሺንግ ስራዎች መከናወን እንዳለባቸው ተለይቷል። የጨረታ ዶኮመንት ተዘጋጅቶ ጨረታ ተካሂዶ ያሸነፉት ኮንትራክቶች ስራውን ጀምረውታል፤ በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል። (አፈፃፀም 90%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2.10. በራስ ሃይል (own force) እንዲሰሩ የታቀዱትን የወፍጮ ቤት፤ የተማሪዎች ቴሌቪዥን ማሳያ አዳራሽ፤ የወተትና የከብት ማድለብያ ህንፃዎች፤ የዶሮ ማርቢያ፤ እና የጣራ ውሃ ማሰባሰብያ ስራዎችን መስራት | በራስ ሃይል እንዲሰራ የታቀደው የወፍጮ ቤት ስራ የተጠናቀቀ ሲሆን የወፍጮ ተከላም ተከናውኗል። የወፍጮ ስራውን ወደውጭ ለማውጣት ጨረታ ወጥቶ የቀረበው ዋጋ የተጋነነ ስለሆነ ሁለተኛ ጨረታ የሚወጣ ይሆናል። የቴሌቭዥን ማሳያው ሌላ አማራጭ ስለተገኘበት እንዲቀር የተደረገ ሲሆን ሌሎች ስራዎች ደግሞ የመዘግየት ችግር (አስፈላጊ ማቴርያሎች በወቅቱ ተገዝተው ስላልቀረቡ) ያለባቸው ቢሆንም እየተሰሩ ነው። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 2.11. ከተለያዩ የውሃ ጉድጓዶች ወደ ዋናው ሪዘርቫየር የሚመጣውን ውሃ በጊዜያዊነት ማጠራቀም የሚችል ሪዘርቫየር (ኮሌክሽን ቻምበር) ከግቢው ውጭ መስራት | የማጠራቀምያ ጊዜያዊ ሪዘርቫየር (ኮሌክሽን ቻምበር) እንዲሰሩልን ለክልሉ የውሃ ኢንተርፕራይዝ ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ግንባታው ግን ገና አልተጀመረም። (አፈፃፀም 50%) | | |
| | 2.12. ከከተማው አስተዳደር እንዲሁም ከትግራይ ልማት ማህበር እና ከከተማው ሆስፒታል ጋር በመተባበር የማህበረሰብ ትምህርት ቤት እና በሆስፒታሉ ውስጥ የህክምና ተማሪዎቻችን የሚጠቀሙበትና ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚውል በሎክ መስራት | የማህበረሰብ ትምህርት ቤት በተመለከተ ቦታውን በአጥር በማጠር የጨረታ ስራዎች ለማከናወን ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በከተማው አስተዳደር በኩል የቦታው ፕላን ስላልቀረበልን ስራው ሊከናወን አልቻለም። በከተማው ሆስፒታል አንድ ብሎክ ለመስራት ታቅዶ የነበረ ሲሆን ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ የነበረው ዲዛይን ማስተካከያ ያስፈልገው ስለነበር ዲዛይኑን የማስተካከል ስራ እየሰራን እንገኛለን። (30%) | | |
| | 2.13 በሁለተኛው ግቢ ለሚሰራው ስፒሻላይዝድ ሆስፒታል የዲዛይን ስራ አወዳድሮ ማሰራት | የማስተር ፕላን ስራው በጨረታ ባሸነፈው ድርጅት የተሰራ ቢሆንም ዝርዝር የሆስፒታል ዲዛይን የማሰራቱ ጉዳይ ግን በደንብ መጠናት ስላለበት በ2008 እንዲሰራ በእቅድ የሚያዝ ይሆናል። (አፈፃፀም 45%) | | |
| **ግብ 3. ተቋማዊ መልካም አስተዳደርን ማስፈንና ማስጠበቅ** | 3.1 የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በስፋት የሚያሳትፍ አሰራር መከተል፤ የጋራ መግባባት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ | ዩኒቨርሲቲው በየደረጃው ማህበረሰቡ (መምህር፤ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ፤ እና ተማሪ) በሰፊው የሚሳተፍበት ስርአት ተዘጋጅቶ በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም ተደርጓል። የተለያዩ መድረኮች ተዘጋጅተው ማህበረሰቡ ከእቅድ ዝግጅት እስከ አፈፃፀም ግምገማ በስፋት ይሳተፋል። (አፈፃፀም 95%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.2. የተጀመሩት የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በማድረግ ውጤታማነታቸውን ወደ መለካት መሸጋገር፤ በ2006 በተዘጋጀው ማንዋል መሰረት የመምህራን እና በአስተዳደር ሰራተኞች የአንድ ለአምስት አደረጃጀት መፍጠርና ማጠናከር፤ የልማት ቡድኖች መፍጠርና ማጠናከር | በአንደኛ ሰሚስተር 1982 የተማሪ የአንድ ለአምስት እና 202 የልማት ቡድኖች እንዲሁም በሁለተኛ ሰሚስተር 1879 የአንድ ለአምስት ቡድኖችና 179 የልማት ቡድኖች ተመስርተው የሚጠበቅባቸውን ተግባራት አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ አከናውነዋል። በመምህራን አከባቢም 82 የአንድ ለአምስት እና 37 የልማት ቡድኖች አሉ። አፈፃፀማቸው በተመለከተ የተማሪዎች የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው ሲሆን የመምህራን እና ሰራተኞች ግን ወደ ሚፈለገው ደረጃ የደረሱ አይደለም። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 3.3. ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲሰፍን የተማሪዎች አቅርቦቶች (ምግብ፣ መኖርያ፣ ውሃና ፍሳሽ፣ መዝናኛ፣ ወዘተ) በጊዜው እንዲሟሉ ማድረግ። ችግሮች ሲያጋጥሙ አፋጣኝ ምላሾች መስጠት። ተማሪዎችን በሰፊው የሚያሳትፍ አሰራር መከተል። በአካደሚው ዘርፉ በተማሪና በመምህር ዲሞክራያዊ ግንኙነት እንዲሰፍን ማድረግ፤ ትምህርት በወቅቱ መጀመር (First Day First Class)። የጥበቃና የፀጥታ ስርአት ማጠናከር፤ በተማሪወች መሃከል የእርስ በርስ መግባባት እንዲጎለብት የሰላም ፎረም ማጠናከር። ለ2007 አገራዊ ምርጫ አስገላጊው ዝግጅትና ድጋፍ ማድረግ | የምግብ፤ የውሃ እና የመዝናኛ አቅርቦቶች በተመለከተ ከፍተኛ ክትትል ይደረግባቸዋል። በውሃ በኩል የነበረው ችግር ከፍተኛ ቢሆንም በየቦታው ትላልቅ ሮቶዎችን በማዘጋጀት እና በቦቴ እንዲሞሉ በማድረግ በመስመር የሚመጣውን ውሃ ደግሞ በሳምንት ሁለት ቀን (ሮብ እና እሁድ) እንዲዳረስ በማድረግ የውሃ ችግሩን የፈታነው ባይሆንም ለማስተዳደር (manage ለማድረግ) ችለናል። የመጀመርያ ቀን የመጀመርያ ክፍል በተመለከተ ደግሞ በአንደኛም በሁለተኛም ሰሚስተር በጥሩ ሆኔታ ተከናውኗል። በመምህር እና በተማሪ ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ዲሚክራሲያዊ እንዲሆን ለማድረግ ተደጋጋሚ ጥረቶች ስለሚደረጉ ውጤቱም በአጠቃላይ በጣም ጥሩ ሊባል የሚችል ነው። የ2007 ምርጫን በተመለከተ ደግሞ ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ በጥሩ ሁኔታ ሊከናወን ችሏል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 3.4. ከኪራይ ሰብሳቢነት የፀዳ እና በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ አመራርና ማህበረሰብ እንዲኖር አስፈላጊው ጥረት ማድረግ፤ የዩኒቨርሲቲ የስነምግባር መመርያ እንዲኖር ማድረግ፤ ለችግር ተጋላጭ የሆኑትን በማጥናትና | በፌደራል ኦዲተሮችና በውስጥ ኦዲተሮች የሚቀርቡ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ ማስተካከያዎች ይወሰዳሉ። በተደረጉት የዝግጅት ስልጠናዎች አፅንኦት ከተሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የመልካም አስተዳደር እና ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የፀዳ ማህበረሰብ የመኖር ጉዳይ ነው። በስልጠና ብቻ ሳይሆን | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በመለየት የክትትል ስራዎችን መስራት፤ ጥርጣሬዎች ሲያጋጥሙ የማጣራት ስራዎች ማካሄድ፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት፤ ቅሬታዎችን በአግባቡ ማስተናገድ፤ በዋና ኦዲተር እና በውስጥ ኦዲት የሚለዩ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድ | በአሰራርም ዩኒቨርሲቲው ግልፅነት መሰረት ያደረገ አሰራር ይከተላል። ቅሬታዎች እና ችግሮች በግልፅ እንዲቀርቡ በማድረግ ውይይት ይደረግባቸዋል። ቅሬታዎች ወደ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቀርበው እንዲታዩ ይደረጋል። የስነ ምግባር መመርያ በተመለከተ ጅማ ላይ በተካሄደው ሁለተኛው የዩኒቨርሲቲዎች የስነምግባር ማኅልበቻ ንቅናቄ በጋራ ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሰራ እቅድ የተያዘለት ቢሆንም አልተፈፀመም። ዩኒቨርሰቲው የራሱ የሆነ የስነምግባር መመርያ ያዘጋጀ ቢሆንም ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የጋራ መመርያ ይዘጋጃል በሚል እንዲፀድቅ አልተደረገም። ከተለያዩ ቦታዎች የመጡለትን ጥቆማ መሰረት በማድረግ የዩኒቨርሲቲው ስነ–ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት አስፈላጊውን ማጣራት ያደረገ ሲሆን ወደ ዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲመራ የተደረገ ጉዳይም (ለቀን ሰራተኞች አላግባብ ስለተፈፀመ ክፍያ) አለ። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 3.5. የእቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በየጊዜው ማድረግ። በዚሁም መሰረት የስድስት ወር እና አመታዊ አጠቃላይ ግምገማ ይከናወናል፤ ሰኔት በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ የዲኖችና ዳይሬክተሮች ካውንስል በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ በአስተዳደር ምክትል ፕረዚደንት ፅ/ቤት ስር የሚገኙ ዳይሬክተሮች በየሁለት ሳምንት ይሰበሰባሉ፤ የየሩብ አመቱ ሪፖርቶች ይዘጋጃሉ ለሚመለከተወ ክፍል ይላካሉ። | የ2007 የመጀመርያው ሩብ አመት የእቅድ አፈፃፀም የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች በተገኙበት ውይይት ተደርጎበታል። የዩኒቨርሲቲው ሰኔት፤ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ካውንስል፤ የዲኖችና ዳይሬክተሮች ካውንስል (በአካዳሚክና ምርምር ምክትል ፕረዚደንት ስር የሚገኙት)፤ የዳይሬክተሮች ካውንስል (በአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕረዚደንት ስረ የሚገኙት) በእቅዱ በተቀመጠው መሰረት ጥብቅ የክትትል ስራዎች ይደረጋሉ። አስፈላጊ ውሳኔዎችም ይደረጋሉ። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 3.6. የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን እና የልምድ ልውውጦችን ማከናወን | ለአዲስ መምህራን የኢንዳክሽን ስልጠና ተሰጥቷል። በድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በኩል ደግሞ በተለይ ለውስጥ ኦዲት ክፍል ሰራተኞች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ለመላው መምህራን ደግሞ ስለ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ፕሮፖዛል አቀራረብ ስልጠና ተሰጥቷል። በርካታ የልምድ ልውውጦችም ተደርገዋል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 3.7. የዩኒቨርሲቲ ስትራቴጂክ ፕላን መሰረት በማድረግ የካስኬዲንግ ስራዎችን መስራት | የካስኬዲንግ ስራዎች ለመስራት ታቅዶ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የተጀመሩ ቢሆንም (ስልጠና በመስጠት)፤ የመጀመርያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተጠናቆ ሁለተኛው የሚዘጋጅበት ወቅት ስለሆን የተዘጋጀው የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂክ እቅድ በሁለተኛው ትራንስፎርሜሽነ እቅድ እንዲቃኝና እንዲዳብር (upgrade) አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ከካስኬዲንግ ስራው ይልቅ የማዳበሩ ስራ ቅድሚያ ተሰጥቶት ይሄንን የሚሰራ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲያዳብረው ተደርጓል። (75%) | | |
| | 3.8. የካይዘን ስራዎችን ማጠናከርና መተግበር | በ2006 የተጀመሩት እና በተመረጡት ቦታዎች (ዎርክሾፖች፤ ምግብ ቤት፤ እቃ መጋዘን፤ ላቦራቶሪዎች) የካይዘን ስራዎች ዘንድሮም በጥሩ ሁኔታ እየቀጠሉ ነው። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 3.9. ለተማሪዎች ካውንስል፤ ለተማሪ ክበቦች፤ ለመምህራን ማህበር፤ ለቁጠባና ብድር ማህበር፤ እና ለሌሎች አደረጃጀቶች ድጋፍ ማድረግ | በእቅዱ ለተጠቀሱት አካላት በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ከተማሪዎች ካውንስል ተደጋጋሚ ውይይቶች ይደረጋሉ። እንደምሳሌ የሚጠቀሰው በዩኒቨርሲቲው ለተደራጀ የቁጠባና ብድር ተቋም ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችን ልምድ እንዲቀስም ድጋፍ ተደርጎለታል። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 3.10. ህጉን የተከተለና የተቀላጠፈ የግዥና ፋይናንስ ስርአት እንዲኖር ማድረግ፤ ዋና ዋና የግዥ ስራዎችን በታቀደ መልኩ እንዲከናወኑ ማድረግ፤ የንብረት አያያዝና ሪፖርቲንግ ስርአት ማሻሻልና ማጠናከር | የግዥ እና የፋይናንስ ስርአታችን ህጉን በተከተለ መልኩ የሚከናወን ነው። መስተካከል የሚያስፈልጋቸው ነገሮች በፌደራልና ውስጥ ኦዲተሮች፤ በግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚቀርቡበት ጊዜ ተገቢው ውይይቶች ይካሄዱባቸዋል (የመውጫ ኮንፈረንሶች)። የግዥ ስራው እቅድም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል። (አፈፃፀም 85%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.11. የወፍጮ ስራን በግቢው ውስጥ ማከናወን | የወፍጮ ቤቱ የተጠናቀቀ ሲሆን የተከላው ስራም ተሰርቷል። ተወፍጮ ስራው በከፊልም ቢሆን በግቢው ውስጥ ለማከናወን የተያዘው እቅድ ግን ወደ ውጭ በማውጣት ለማሰራት ታቅዶ የነበረው ሊከናወን አልቻለም (65%) | | |
| | 3.12. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ስራን ወደ ውጭ እንዲወጣ ተደርጎ (outsourcing) በየጊዜው እንዲወገድ ማድረግ | የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ ስራ በእቅዱ መሰረት በውድድር ወደ ውጭ እንዲወጣ ተደርጎ ስራው በመከናወን ላይ ይገኛል። (100%) | | |
| | 3.13. ለተማሪዎች የሚቀርብ ዳቦ ዩኒቨርሲቲው በገዛቸው የዳቦ መጋገርያ ማሽኖች በከፊልም ቢሆን እንዲቀርብ ማድረግ። ሰራተኞቹን በተመለከተ ወደ ውጭ ወጥቶ (outsource ተደርጎ) እንዲሰራ ይደረጋል | ስራውን ለመጀመር የሚያስፈልጉ ማቴርያሎች ለመግዛት ጨረታ ወጥቶ በአቅራቢዎች ዘንድ ባለመቅረቡ ምክንያት እና ስራውን ወደውጭ ለማውጣት ጨረታ ወጥቶ የተጋነነ ዋጋ መበቅረቡ ስራው ሊከናወን አልቻለም። (አፈፃፀም 40%) | | |
| | 3.14. አዲስ አበባ የሊያይዘን ፅ/ቤት መክፈት | የጉዳይ ፈፃሚ (liaison) ፅ/ቤት ለመክፈት የሚያስችለን ግቢ ለመከራየት ኮሜቴ ተቋቁሞ የኪራዩ ስራ ተጠናቋል። አስፈላጊ ሰራተኞች የመቅጠር ስራ ግን ገና የሚቀር ነው። በቅርቡ የሚሰራ ይሆናል። (አፈፃፀም 65%) | | |
| | 3.15. አዲስ እና የተሻሻለ የስራ መዋቅረ በማዘጋጀት የዩኒቨርሲቲው ቦርድ እንዲያፀድቀው ተደርጎ ወደ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማስፀደቅ በ2008 እንዲተገበር ማድረግ | አዲስ መዋቅር የሚያዘጋጅ ኮሚቴ ተቋቁሞ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችን በመጎብኘትና ከሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው አካላት ጋር በመወያየት ድራፍት መዋቅሩን ያዘጋጀ ሲሆን የማፅደቅ ስራ ግን አልተጠናቀቀም። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 3.16. በመኪና እጥረት ምክንያት የሚያጋጥመውን የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር ለመቀነስ የሰርቪስ መኪኖችን መከራየት፤ የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ እንዲቋቋም በማድረግ ከሚገዛቸው መኪኖች ዩኒቨRሲቲው እንዲከራይ ማድረግ (ከተቻለ በ2007 አልያም በ2008) | ተጨማሪ ሶስት አውቶቡሶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ተገዝተው የተላኩልን ሲሆን ከነዚህም በተጨማሪ ሁለት አውቶቡሶችን በኪራይ መልክ እየተጠቀምን እንገኛለን። የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም ይቻል ዘንድም አስፈላጊውን ዶኩመንቶች እንዲያዘጋጅ አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሰራ ይገኛል። (አፈፃፀም 85%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.17. በቀልጣፋ ለውጥ አምጪ መሳርያ (quick wins) መሰራት ያለባቸውን በመለየት እንዲከናወኑ ማድረግ | በየደረጃው ያሉት የስራ ክፍሎች ቢሮዎችና በየደረጃው የሚገኙ ሃላፊዎች ስሞች የሚያመለክቱ ፅሁፎች ለመስራት ታስቦ ግዥዎች ጨረታ ወጥቶ በአመቱ መጨረሻ እንዲቀርቡ ተደርጓል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| ግብ 4. የመምህራን ልማት ማጠናከር | 4.1 መምህራንን ለሁለተኛ እና ለሶሥተኛ ዲግሪ ትምህርት መላክ | ዘንድሮ በርካታ መምህራን ወደ ትምህርት የተላኩ ሲሆን በድምሩ 168 የዩኒቨርሲቲው መምህራን በትምህርት ላይ ነው ያሉት። ከነዚህ ውስጥ 39 የሶስትኛ ዲግሪ በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን 129 ደግሞ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በትምህርት ላይ ከሚገኙ መምህራን ውስጥ 13 የሚሆኑት ዩኒቨርሲቲው በጀመረው የድህረ ምረቃ ፕሮግራም በመማር ላይ የሚገኙ ናቸው። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 4.2 በትምህርት የሚገኙ መምህራን የትምህርት ሁኔታቸዎ መከታተል | በየኮሌጁ ክትትል ይደረግላቸዋል። ክትትሉ ም የሚቀጥል ይሆናል። ትምህርት አጠናቀው ሪፖርት ባላደረጉ ላይ የህግ ክፍላችን ክስ ለመመስረት በዝግጅት ላይ ነው። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 4.3 መምህራን የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም እንዲከታተሉ ማድረግ | የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (Higher Diploma Program) ለመከታተል 62 መምህራን የተመዘገቡ ሲሆን 44 የሚሆኑት በቅርቡ ጨርሰው እንደሚመረቁ ይጠበቃል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 4.4 በፔዳጎጂ እና ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንዲሰጥ ማድረገ (በተለይ ለአዳዲስ መምህራን) | ስልጠናው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመጡ ባለሞያዎች ተሰጥቷል። (100%) | | |
| | 4.5. የውጭ አገር መምህራንን ቅጥር ማካሄድ (ከህንድ፤ ከፊሊፒንስ እና ከሌሎች አገሮች) | ከህንድ፤ ከፊሊፒንስ እና ከጀርመን የቅጥር ስራ ተከናውኗል። በዚሁም መሰረት በ2006 የትምህርት ዘመን 21 የነበሩት የውጭ ሃገር መምህራን ዘንድሮ 43 ደርሰዋል። ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ የፊሊፒንስ አንዱ ደግሞ የጀርመን መምራን ሲሆኑ የተቀሩት ህንዶች ናቸው። (አፈፃፀም 100%) | | |
| ግብ 5. ብቁ የአካዳሚክ | 5.1 በድህረ ምረቃ ሁለት ፕሮግራሞችን (MBA እና Master of Accounting and Finance) | በድህረ ምረቃ ሁለት ፕሮግራሞች (MBA እና MAcF) ተከፍተዋል። ፕሮግራሞቹ በመደበኛና በማታ የተጀመሩ ሲሆን በድምሩ 108 ተማሪዎች | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፕሮግራሞችና ስርአተ ትምህርቶችን ማረጋገጥና መተግበር | በቅድመ ምረቃ ደግሞ ስድስት ፕሮግራሞችን (Architecture; Pharmacy; Environmental Science; Tigrigna; Theatrical Art; Archeology and Heritage Management) መክፈት | (13 መደበኛ እና 95 የማታ ተከታታይ) አሉን። በቅድመ ምረቃ ስድስት አዳዲስ ፕሮግራሞች (Architecture; Pharmacy; Environmental Science; Tigrigna; Theatrical Art; Archeology and Hetitage Management) ተከፍተው ተማሪዎች ተመድበውላቸዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 5.2 የተከታታይ ምዘና (Continuous Assessment)፤ ቋሚ መስፈርት መሰረት ያደረገው የነጥብ አሰጣጥ (Criterion Referenced)፤ እና ሞዱላራይዝድ ካሪከለም (modularization) ማጠናከርና መተግበር። በአፈፃፀማቸው ዙርያ ግምገማዊ ስልጠናዎችን ማከናወን | የተከታታይ ምዘና፤ ቋሚ መስፈርት ያደረገ የነጥብ አሰጣጥ፤ እና ሞዱላራይዝድ ካሪከለም ቀደም ብለው የተጀመሩ ሲሆን ተጠናክረው እየቀጠሉ ነው። አስፈላጊው ክትትል ይደረግባቸዋል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 5.3. በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ተማሪዎች (በተለይም የሴት ተማሪዎችን መሰረት በማድረግ) የቱቶትያል እና የረሜድያል ድጋፎችን መስጠት | የትምህርት ድክመት የነበረባቸው ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ቀደም ብለው ወደ ዩኒቨርሲቲው እንዲገቡ ተደርገው የማጠናከርያ ድጋፍ (Remedial Support) ተደርጎላቸው እንደገና እንዲፈተኑ ተደርገዋል። የአንደኛ ሰሚስተር ውጤታቸውን መሰረት ያደረገ የማጠናከርያ ድጋፍ ደግሞ በሁለተኛው ሰሚስተር ላይ ተሰጥቷል። በተለይ ሴት ተማሪዎችን መሰረት ያደረጉ ድጋፎች ደግሞ በስርአተ ፆታ እና በኮሌጆች አስተባባሪነት ተሰጥቷል። (95%) | | |
| | 5.4. በቅድመ ምረቃ እና በድህረ ምረቃ የማታ ትምህርት መቀጠል፤ በክረምት ወቅት ደግሞ የቴክኖሎጂ ባችለር ዲግሪ ፕሮግራም ከክልሉ ቴክኒክና ሞያ ጋር በመተባበር፤ የድህረ ምረቃ ዲፕሎማ ፕሮግራም ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፤ እንዲሁም በተለመዱት ፕሮግራሞች እንዲቀጥሉ ማድረግ | የማታ ትምህርት በቅድመ ምረቃ እና በድህረ ምረቃ እየተካሄደ ነው። በቅድመ ምረቃው መርሃ ግብር በሶስት ኮሌጆችና በሰባት ትምህርት ክፍሎች 923 ተማሪዎች ያሉን ሲሆን፤ በድህረ ምረቃው ደግሞ በሁለት ፕሮግራሞች 95 ተማሪዎች አሉን። በድምሩ የማታ ትምህርት ተማሪዎች ብዛት 1018 ነው። በክረምት ተከታታይ በሁሉም ትምህርት ክፍሎች 2320 ተማሪዎች አሉን። (አፈፃፀም 100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5.5. በክረምት የSTEM (Science Technology Engineering and Mathematics) ፕሮግራም መሰረት በክልሉ ምስራቃዊ ዞን እና በአጎራባች የአፋር ክልል ወረዳዎች ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ የተውጣጡ ተማሪዎችን ተቀበሎ ማስተናገድ | በክረምት የSTEM አውትሪች ፕሮግራም 306 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን (ከዘጠነኛ ጀምሮ እስከ 12 ክፍል ያሉትን) ተቀብለን ለአንድ ወር ያህል በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አሰልጥነናቸዋል። ተማሪዎቹ የተውጣጡት ከአፋር ክልል አጎራባች ወረዳዎች (30) ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ከትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ነው። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 5.6. በህክምና ኮሌጃችንና በዓዲግራት ሆስፒታል መካከል የትብብር ግንኙነቶች እንዲኖሩ ማድረግ | የህክምና ኮሌጃችን እና የከተማው ሆስፒታል በትብብር እየሰሩ ነው። ከዩኒቨርሰቲው ጤና ጣብያ ችሎታ በላይ የሆኑ የህክምና ችግሮች ሲያጋጥሙ ደግሞ ዩኒቨርሰቲው ከሆስፒታሉ ባደረገው ውል መሰረት ተማሪዎች ሆስፒታሉ ድረስ እየሄዱ ይታከማሉ። የዩኒቨርሲቲው የህክምና ዶክተሮች ደግሞ በከተማው ሆስፒታል ፕሮግራም ወጥቶላቸው የህክምና ስራ ይሰራሉ (85%) | | |
| | 5.7. የላቦራቶሪ እና የወርክሾፕ አገልግሎቶች በተቻለ መጠን በዩኒቨርሲቲው እንዲሰጡ የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን መስራት። ከብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር (ተገቢው ፈቃድ ከግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር በማግኘት) ላቦራቶሪዎች የሚደራጁ ይሆናል። ለዎርክሾፕ አገልግሎት ተፈላጊ የሆኑ የሌዝ እና CNC ሜሽኖች ደግሞ የሚገዙ ይሆናል። | በእቅዱ መሰረት የላቦራቶሪ እና የዎርክሾፕ አገልግሎቶች በአብዛኛው በዩኒቨርሲቲው እየተሰጡ ነው። በተለይም በባዮሎጂ፤ በኬሚስትሪ እና በፊዚክስ የላቦራቶሪ አገልግሎቶች ሙሉ ለሙሉ በዩኒቨርሲቲው እየተከናወኑ ነው። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያልተሟሉት ብቻ ተለይተው አገልግሎቶቹ በመቐለ ዩኒቨርሲቲ እየተሰሩ ነው። በ2008 የመጀመርያው ሰሚስተር መጨረሻ አከባቢ እንዲደርሱ የሚጠበቁት እና 95 ሚልዮን የሚያወጡ የላቦራቶሪና የላይብረሪ ፈርኒቸሮችን የማሟላት ስራ ደግሞ ከብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ቃሊቲ ፈረኒቸር ድርጅት) ጋር ዩኒቨርሲቲው ውል አስሯል። የሌዝ ሜሽንና የሲኤንሲ ማሽኖች ግዥ ግን አልተከናወነም። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 5.8. የመምህር ተማሪ ጥምርታ (Staff–Student Ratio) በ2006 ከነበረበት 19.42 በእድገትና ትራንስፎርሜሽን በተቀመጠው ታርጌት መሰረት ወደ 1 ለ 20 ማሳደግ። | የመምህር ተማሪ ጥምርታ በስራ ላይ ያሉ መምህራን ብቻ በመውሰድ (የቴክኒክ ረዳቶችን ሳይጨምር) 21.97 የደረሰ ሲሆን የቴክኒክ ረዳቶች ሲጨመሩ ደግሞ 20.37 ነው። በአጠቃላይ በተቀመጠው ግብ አከባቢ መሆናችንን የሚያሳይ ነው። (አፈፃፀም 95%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5.9. የተዘጋጁትን የስፖርት ሜዳዎች እና ጂምናዝየም ጥቅም ላይ ማዋል፤ ለ2007 በዩኒቨርሲቲዎች መካከል ለሚደረገው የስፖርት ውድድር የተሻለ ዝግጅት በማድረግ መሳተፍ | የተዘጋጁት የስፖርት ማዘውተርያ ቦታዎች በተሟላ መልኩ ባይሆንም ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ላይ በተካሄደው የ2007 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የስፖርት ውድድር ደግሞ ከማንም ጊዜ የተሻለ ዝግጅት ተደርጎ ጥሩ ውጤትም ተገኝቶበታል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 5.10. በተመፃህፍት በተፈላጊ መፃህፍት እንዲሟሉ ማድረግ፤ ዲጂታል ላይብረሪ አጠቃቀም እንዲሰፋ ማድረግ፤ አዲሱ ቤተመፃህፍት ዝግጁ ሲሆን ጥቅም ላይ ማዋል | የዲጂታል ላይብረሪ አገልግሎት በዩኒቨርሰቲው እየተሰጠ ነው። በተለይም ደግሞ አሁን በመጠናቀቅ ላይ ባለው የዳታ ሰንተር አመካኝነት ጥቅም የሚሰጡ 500 VDI ኮምፕዩተሮች እየተገጠሙ ስለሆን የተሻለ የዲጂታል ላይብረሪ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል። አዲሱ ማእከላይ ላይብረሪ ደግሞ ተጠናቆ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል (የኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ላይብረሪ እንዲሆን ተደርጓል)። የዩኒቨርሰቲው ቤተመፃህፍቶች የ24 ሰአት አገልግሎት ስለሚሰጡ የማያቋም አገልግሎት (Non-stop service) በመስጠት ላይ ይገኛሉ። (አፈፃፀም 95%) | | |
| ግብ 6. የ70 በ30 ቀመር ላይ የተመሰረተ ሃገራዊ የተሳትፎ መጠንን እውን ማድረግ | 6.1. ቀመሩን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች እንዲመደቡ የሚደረግ ሲሆን በየባንዱ ሊኖር የሚገባው ስብጥርም [ባንድ 1 (40%)፤ ባንድ 2 (20%)፤ ባንድ 3 (5%)፤ ባንድ 4 (5%)፤ ባንድ 5 (20%)፤ ባንድ 6 (10%)] እንዲሆኑ ተገቢው ጥረት ይደረጋል | በ70–30 ቀመር መሰረት ሲታይ በዩኒቨርሲቲው ያለው የተማሪዎች ስርጭት በተፈጥሮ ሳይንስ 71.54 ሲሆን በህብረተሰብ ሳይንስ ደግሞ 28.46 ነው። በየባንዱ ያለው ሁኔታ ሲታይ ደግሞ በባንድ 1 (47.23)፤ በባንድ 2 (11.55)፤ በባንድ 3 (7.37)፤ በባንድ 4 (5.39)፤ በባንድ 5 (18.97)፤ እና በባንድ 6 (9.49) ነው። በተፈጥሮና ቀመር ባንድ ያለው መጠን ያነሰ ቢሆንም በሌሎች ያለው መጠን ግን ከተፈላጊው መጠን ጋር ተቀራራቢ መሆኑ ማየት ይቻላል። የቀመሩ ጉዳይ በዋናነት በሚመደቡት ተማሪዎች የሚወሰን ስለሆነ ዩኒቨርሰቲው የተማሪ ምደባን ሲጠይቅ ነው አስተካክሎ የሚጠይቀው። (አፈፃፀም 100%) | | |
| ግብ 7. የከፍተኛ ትምህርት ፍትሃዊነት ማረጋገጥ፤ | 7.1. የሴት ተማሪዎች፤ አካል ጉዳተኞች እና ከአዳጊ ክልሎች ለሚመጡ ተማሪዎች የትምህርት ክፍል መረጣ ወቅት የተሻለ እድል እንዲያገኙ ማድረግ። በተለይ ለሴት | በእቅዱ መሰረት ሴት ተማሪዎች የ25% ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። (አፈፃፀም 100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የተማሪዎች ተሳትፎ ማረጋገጥ | ተማሪዎች ካሉት ቦታዎች ውስጥ 25% በቅድሚያ እንዲመደቡበት እድል መፍጠር | | | |
| | 7.2. በተለይ ሴት ተማሪዎችን ማእከል ያደረጉ የቱቶርያል እና ረሜድያል ድጋፎችን መስጠት፤ የሴት ተማሪዎች በራሳቸው ፍጥነት እንዲማሩ የሚያስችለውን አካሄድ መከተል | የትምህርት ድክመት ያሳዩ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሰቲው ከሌሎች ተማሪዎች ቀድመው እንዲገቡ ተደርጎ የማጠናከርያ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። የአንደኛ ሰሚስተር ውጤት ከታየ በኋላም የማጠናከርያ ድጋፍ ተሰጥቷል። የቱቶርያል ድጋፎች ደግሞ በየክፍሉ እየተደረገላቸው ነው። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 7.3 ትምህርት የማቋረጥ መጠን በ2006 ከነበረበት 7.16% እንዲቀንስ ለማድረግ ጥረቶችን በማድረግ የማቋረጥ መጠኑ ከ5% ያነሰ እንዲሆን ማድረግ። | የ2007 ትምህርት የማቋረጥ መጠን 5.13% መሆኑን ያሳያል። በዚሁም መሰረት የተያዘው እቅድ በአጠቃላይ የተሳካ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 7.4. የሴት ተማሪዎችን ማእከል በማድረግ የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን በመለየት ድጋፎችን ማድረግ | የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚሹ 185 ወንዶች እና 322 ሴት ተማሪዎች በድምሩ 507 ተማሪዎች ተለይተው የማቴርያልና የፅህፈት መሳርያዎች እና የንፅህና መሳርያዎች) እና የገንዘብ (በሰሚስተር 200 ብር) ድጋፍ እየተደረገላቸው ነው። በመቶኛ ሲቀመጥ የሴት ተማሪዎች ቁጥር 63.5% ነው። እነዚህ በዩኒቨርሲቲው በቀጥታ የሚታገዙ ሲሆን ከሴቶች፤ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ 30 ሴት ተማሪዎች (በየወሩ 200 ብር) እንዲሁም ከፖዝ ፋይንደር በተገኘው ድጋፍ ለ30 ሴት ተማሪዎች የንፅህና ቁሳቁሶች ድጋፍ እየተደረገ ነው። ዝርዝሩ በሪፖርቱ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ሌሎች ተመሳሳይ ድጋፎችም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር እየተደረጉ ነው። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 7.5. የተማሪዎች ካውንስል እንዲጠናከር ድጋፍ ማድረግ፤ የተማሪ ክበቦች እንዲመሰረቱና እንዲጠናከሩ ድጋፍ ማድረግ | የተማሪዎች ካውንስል በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ እያደረገ ነው። ከዩኒቨርሲቲውም ተገቢው ድጋፈ ይደረግለታል። በግቢው ካሉት የተለያዩ ሱቆች፤ እና ላውንጆች እንዲሁም ከትራፊ ምግብ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ለተማሪዎች ካውንስል | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ገቢ እንዲሆን ተወስኖ እየተሰራበት ይገኛል። የተማሪ ክበቦችም በተማሪዎች ካውንስል አስተባባሪነት ድጋፍ ይደረግላቸዋል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 7.6. የካውንስል /የተማሪ ተወካዩች/ በሰኔት፤ በኮሌጅ ካውንስል፤ በትምህርት ክፍል ካውንስል፤ በምግብና እና ሌሎች ስራዎች እንዲሳተፉ ማድረግ | የተማሪ ተወካዮች ከትምህርት ክፍል ጀምሮ እስከ ሰኔት ድረስ በየደረጃው ይሳተፋሉ። የተሳትፎው መጠን ግን ከክፍል ክፍል እንደሚለያይ ለማወቅ ተችሏል። በአጠቃላይ ተሳትፎአቸው በጣም ጥሩ ነው ተብሎ የሚወሰድ ቢሆንም ቀጣይነት ያለው ክትትል ሊደረግለት ይገባል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 7.7. የተማሪ የክፍል ተወካዩች ማስመረጥ ከትምህርት ክፍል ሃላፊ ጋር ተከታታይ ግንኙነቶችን መፍጠር፤ በሶስት ወር አንድ ጊዜ በኮሌጅ እና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ግምገማዎችን ማድረግ | በእቅዱ መሰረት ተወካዮች ተመርጠው እንዲሳተፉ ተደርጓል። በዩኒቨርሰቲ ደረጃ ደግሞ ከክፍል ተወካዮች ጋር ውይይት ተደርጓል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 7.8. ለአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጉ የመማርያ ማቴርያሎች እንዲዘጋጁ ማድረግ (ብሬል፤ ኮምፒዩተር ሶፍትዌር መስማት ለተሳናቸው) | የብሬል እና ልዩ የኮምፒዩተር ሶፍትዌር የሚጠቀሙ ተማሪዎች ስላልተመደቡልን የማቴርያሎቹ አቅርቦት አልተዘጋጀም። | | |
| ግብ 8. ለኢንዱስትሪ ልማት ኣስተዋፅኦ የሚያደርግ ተቋሚዊ ኣቅምን ማረጋገጥ፤ | 8.1 በኣከባቢው እና በክልሉ ከሚገኙ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ትስስር ለመፍጠር ጥረቶችን ማድረግ | በዩኒቨርሰቲው የኢንዱስትሪ ትስስር ዳይሬክቶሬት አመካኝነት ከጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች እንዲሁም ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዲስትሪዎች ጋር ትስስር ለማድረግ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። ለክልሉ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ሰራተኞች የተሰጠው ስልጠናም የሚጠቀስ ነው። ዩኒቨርሲቲያችን ዘንድሮ የኢንጂነሪንግ ተማሪዎችን (አራተኛ አመት) ለመጀመርያ ጊዜ ለተግባራዊ ልምምድ መላክ ስለነበረበት በርካታ ድርጅቶች ተማሪዎቻችንን እንዲቀበሉ ማግባባት ተችሏል ። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 8.2 ጥቃቅንና ኣነስተኛ ድርጅቶችን መደገፍና ማጠናከር (በግንባታ ስራ በስፋት እንዲሳተፉ በማድረግ፤ ለዩኒቨርሲቲው አቅርቦቶችን በማቅረብ፤ ወደውጭ በሚወጡ ስራዎች እንዲወዳደሩ ማድረግ)፤ | በግንባታ ስራ እና ወደውጭ እንዲወጡ በተደረጉት ስራዎች (ፅዳት፤ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ) እየተሳተፉ ነው። (አፈፃፀም 80%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8.3. የህግ ድጋፍ ሰጪ ማእከል (Legal Aid Center) ማቋቋም | በከተማው ለማእከሉ የሚሆን ቢሮ ለመከራየት ሙከራዎች የተደረጉ ሲሆን የመከራየቱ ስራ ስላልተጠናቀቀ በ2008 የሚከናወን ይሆናል።ለዚሁ ማእከል የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግልን ቀደም ብለን ፕሮፖዛል የላክንለት የሰብአዊ መብት መስሪያቤት ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብቶልን የነበረ ቢሆንም ድጋፉን አልላከልንም። (60%) | | |
| | 8.4 የኮሙኒቲ ኤፍ ኤም አገልግሎት ለመስጠት የግዥ እና የተከላ ዝግጅቶችን ማድረግ | ለሬድዮ ጣብያው የሚሆኑ ማቴርያሎች ስፔሲፊኬሽን ተዘጋጅቷል። ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ ስላልቀረበ ሊገዙ አልተቻለም። በድጋፍ መልክ እንድናገኝ ሊደግፉ የሚችሉ አካላት ተለይተው በፕሮፖዛል መልክ እንዲላክላቸው ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም ገና አልተላከላቸውም። (አፈፃፀም 30%) | | |
| | 8.5. በከተማው ሜዴል ፋርማሲ ለማቋቋም ዝግጅቶችን ማድረግ (ፋርማሲው በ2007 ካልተቻለ በ2008 ስራ የሚጀምር እንዲሆን ማድረግ) | ይህ ስራ በ2008 እንዲሰራ ተብሎ እንዲተላለፍ ተደርጓል። | | |
| | 8.6. ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር ያለው ትስስር ማጠናከር፤ የላቦራቶሪ ስልጠናዎች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መስጠት። እንደሁኔታው በአቅራቢያችን የሚገኙት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ላቦራቶሪ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ | ከሁለተኛ ደረጃ የተውጣጡ መምህራን የላቦራቶሪ ስልጠና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በመገኘት እንዲከታተሉ ተደርጓል። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም በክረምት ወራት በላቦራቶሪዎች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 8.7. ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የበለስ ማጣርያ ፋብሪካ በከተማው እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ፤ ለዚሁ ኢንዱስትሪ የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድ። በባለሃብቶች በከተማው አቅራቢያ የሚተከለውን የብርጭቆ ፋብሪካ መሰረት በማድረግ የመደጋገፍ ስራዎችን መስራት | የከተማው አስተዳደር በሰጠው ቀደም ብሎ ተሰርቶ የነበረ ግንባታ ለበለስ ማጣርያ ፋብሪካው በሚሆን መልኩ ተስተካክሎ ተሰርቷል። የጠርሙስና ብርጭቆ ፋብሪካው ስራ ለመጀመር ድርጅቱ በዝግጅት ላይ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። ዩኒቨርሲቲው ከነዚህ ድርጅቶች በትብብር እየሰራ ነው። (አፈፃፀም 70%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8.8. ሌሎች የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን (የከተማው እግር ኳስ ክለብ መደገፍ፤ ሌሎች የስፖርት እንቅስቃሴዎችን መደገፍ፤ የአከባቢው እና የክልሉ ባህላዊ እሴቶች ማዳበር፤ ወዘተ) | የከተማው የእግር ኳስ ቡድን ለማጠናከር የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ ተደርጎለታል፤ ወደ ኮችኔል የተባለው የበለስ በሽታ ለመከላከል ከክልት አውላዕሎ ወረዳ እና ከክልሉ ግብርና ቢሮ ጋር በመተባበር እየሰራን ነው። ቀደም ብለው የተጠቀሱ ሌሎች ስራዎችም ተከናውነዋል (አፈፃፀም 90%) | | |
| ግብ 9. ሃገራዊ ፖሊሲንና ፋይዳን ያማከለ ተቛሚዊ የጥናትና ምርምር አቅምን መገንባት፤ | 9.1. የምርምር የትኩረት መስኮችን (Research Thematic Areas) ለይቶ ማስቀመጥ | የትኩረት መስኮች የመለየት ስራ የተሰራ ሲሆን በሰኔት መፅደቅ ይቀረዋል። የተለዩት የምርምር የትኩረት መስኮች በዚህ ሪፖርት ውስጥ ቀደም ብለው ተቀምጠዋል (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 9.2. የምርምር መመርያ በማዘጋጀት እና እንዲፀድቅ በማድረግ ጥቅም ላይ ማዋል። በዚሁ መመርያ ሌሎች ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው የሶስተኛ ዲግሪ በመማር ላይ ያሉት መምህራን እንዴትና በምን አኳሃን ከምርምር በጀት ሊመደብላቸው እንደሚችል የሚቀመጥ ይሆናል | የሶስተኛ ዲግሪ በመማር ላይ ያሉትን መምህራን በተመለከተ አሰራር ተበጅቶለት እየተሰራበት ይገኛል። አጠቃላይ መመርያውን በተመለከተ ደግሞ ረቂቁ የተዘጋጀ ሲሆን ለሰኔት ቀርቦ የማፅደቁ ስራ ግን ገና አልተሰራም። (አፈፃፀም 65%) | | |
| | 9.3. የሃገሪቱን ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች መሰረት ያደረጉ ችግር ፈቺ ጥናቶች ትኩረት በማድረግ የምርምር ባጀት መመደብ | ከቀረቡት 68 የምርምር ፕሮፖዛሎች 47 የተመረጡ ሲሆን ከሃገሪቱ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያላቸው ትስስር እንደ መምረጫ ክራይቴርያ እንጠቀምበታለን። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 9.4. የምርምር ውጤቶች ቀን (Research Review Day) እና የምርምር ፕሮፖዛሎች የሚቀርቡበት ቀን በመለየት በወቅቱ (ሳይዘገዩ) እንዲከናወኑ ማድረግ። የተመረጡ ምርምሮች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸው ክትትል ማድረግ | ከቀረቡት ፕሮፖዛሎች ውስጥ በየኮሌጁ በተቋቋሙት ኮሚቴዎች አመካኝነት የተሻሉት እንዲመረጡ ተደርገው በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ደግሞ በዲኖች ካውንስል ተቀባይነት ያገኙት ባጀት ተመድቦላቸዋል። የምርምር ውጤቶች ቀን ሰኔ 19 እስከ 20 ተካሂዶ 28 የምርምር ውጤቶች ቀርበዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 9.5. የምርምር ውጤቶችን በProceedings መልክ ማሳተም | የምርምር ውጤቶቹ የቀረቡት ሰኔ ላይ ስለሆነ የማሳተሙ ስራ በቀጣይ የሚከናወን ይሆናል። | | |
| | 9.6. የምርምር ገንዘብ በማፈላለግ በአገር ውስጥም | እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ዩኒቨርሰቲ ኮሌጅ ሎንደን ጋር በመተባበር በአርብቶ አደሮች ዙርያ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በውጭ አገርም ከሚኖሩ ተቋማትና ድርጅቶች የምርምር ስራዎችን በግልም በጋራም ማካሄድ | (አፋር ክልል) የሚያተኩር የምርምር ፕሮፖዛል በኔዘርላንድ አገር ለሚገኘው ድርጅት ቀርቦ ተወዳድሮ አሸናፊ ሆኗል። ጣልያን አገር የሚገኘው የሳሌርኖ ዩኒቨርሲቲም በተለይ ከዓዲግራት ዩኒቨርሰቲ ለተመረቁ ተማሪዎች በሰጠው የትምህርት እድል እንዲወዳደሩ እድል ሰጥቶናል። ሌሎች ሙከራዎችም እየተደረጉ ነው። (አፈፃፀም 70%) | | |
| ግብ 10. የዩኒቨርሲቲውን ገቢ ምንጮች በብዛትና በመጠን ማጠናከር። | 10.1. በዩኒቨርሲቲው ስር የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም፤ ለኢንተርፕራይዙ ቦርድ መሰየም እና የአሰራር ማንዋሎች እንዲዘጋጁ ማድረግ | የቢዝነስ ኢንተርፕራይዙን ለማቋቋም የሚያስችሉ አስፈላጊ ዶኩመንቶችን የሚያዘጋጅ ኮሜቴ ተመስርቶ እንቅስቃሴ ጀምሯል። | | |
| | 10.2. ዩኒቨርሲቲው ባሉት ዎርክሾፖች ለተጠቃሚዎች አገልግሎት በመስጠት የውስጥ ገቢ እንዲገኝ ማድረግ | በሲቪል ኢንጂነሪንግ በኩል ሙከራዎች የተደረጉ ቢሆንም ገና በተደራጀ መልኩ አልተሰራበትም። (አፈፃፀም 35%) | | |
| | 10.3. የማታ ትምህርት (በቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ) እና በክረምት ትምህርት ፕሮግራሞች የውስጥ ገቢን ማዳበር | በእቅዱ መሰረት 1018 የማታ እና 2320 የክረምት ትምህርት ተማሪዎች በመማር ላይ ስለሆኑ የውስጥ ገቢው ጨምሯል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 10.4 የግብርና ግብአቶችን በማቅረብ የውስጥ ገቢን ማበልፀግ | ይህ ስራ በሁለተኛው ግቢ እንዲሰራ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የሁለተኛው ግቢ ግንባታ ዘግይቶ ስለጀመረ ገና አልተሰራበትም። | | |
| | 10.5. ሌሎች የገቢ ምንጮችን መተግበር (ለምሳሌ ስልጠና እና ፈተናዎች በማደራጀት) | የሲስኮ ስልጠና በማካሄድ ተጨማሪ የውስጥ ገቢ እየተገኘ ነው። ከክልሉ የከተማ ልማት እና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር በመተባበር በርካታ የዩኒቨርሲቲው መምህራን የተሳተፉበት የትናንሽ ከተማዎች (ስምንት ከተማዎች) የአምስት አመት እቅድ በመዘጋጀት ላይ ነው። ከክልሉ የፋይናንስና ፕላን ቢሮ ጋር በመተባበርም የምርምር ስራ ተከናውኗል። ከነዚህ እና ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎች የውስጥ ገቢን ለማዳበር እየተሰራበት ነው። (አፈፃፀም 85%) | | |
| ግብ 11. | 11.1. በ2006 በወጣው ጨረታ መሰረት አሸናፊ የሆነው ድርጅት የዳታ ሰንተር | ህዋዌ የተባለው አሸናፊው ድርጅት ተፈላጊ እቃዎችን በማቅረብ የተከላው ስራ በወሳኝ መልኩ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የኢንተርኔትና ኮሙኒኬሽን ስራዎችን ማስፋትና ማጠናከር | በአግባቡ እንዲተከል እና ተያያዥ የኔትወርክ ስራዎች እንዲሰሩ መከታተል | በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል (ገና የሚቀር ስራ ያለ ቢሆንም)። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 11.2. የኔትወርክ ዝርጋታ ባልተከናወነላቸው አዳዲስ ህንፃዎች አገልግሎቱ እንዲዘረጋላቸው እና የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ | ለዝርጋታው አስፈላጊ የሆኑ ሜቴርያሎች አቅርቦት ላይ መዘግየት አጋጥሞ ስለነበር የዝርጋታ ስራው በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ የሚከናወን ይሆናል። (አፈፃፀም 60%) | ተፈላጊ ማቴረያሎች እንዲገዙ ጨረታ የወጣና አሸናፊ የተለየ ቢሆንም አሸናፊው ድርጅቶች በወቅቱ ማቅረብ ያልቻሉበት ሁኔታ አጋጥሟል | |
| | 11.3. በተወሰኑ የተማሪዎች መኖርያ ቤቶች የዋይፋይ አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ | በአንድ የሴቶች ዶርሚተሪ (ብሎክ 27) የዋይፋይ መስመር ተዘርግቶ አገልግሎት እየሰጠ ነው። (አፈፃፀም 70%) | | |
| | 11.4. የአይሲቲ ዳይሬክቶሬት በሰው ሃይል በማጠናከር የተጠናከረ የጥገና እና ተያያዥ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ማድረግ | ተጨማሪ የሰው ሃይል ቅጥር በማካሄድ የአይሲቲ ዳይሬክቶሬት በሰው ሃይል እንዲጠናከር ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 11.5. የሲስኮ አካዳሚ ለመክፈት ዝግጅቶችን ማጠናቀቅ፤ አጫጭር የአይሲቲ ነክ ስልጠናዎችን ማካሄድ | የሲስኮ አካዳሚ ተከፍቶ ሰልጣኞች እየሰለጠኑ ነው። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 11.6. የረጂስትራር ስራዎችን አውቶሜት ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናወን | የረጂስትራር ስራውን አውቶሜት ለማድረግ የሚያስችለን ስራ በራሳችን የሰው ሃይል በአይሲቲ ዳይሬክቶሬት በኩል ለመስራት እቅድ ተይዞ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ውጤቱን በተመለከተ በየጊዜው እየተገመገመ መሄድ ያለበት ነው። (አፈፃፀም 20%) | | |
| | 11.7. የዲጂታል ላይብረሪ አገልግሎት ለሰፊው ተማሪ እንዲደርስ ማድረግ | በሁለቱም ቤተመፃህፍቶች የዲጂታል ላይብረሪ አገልግሎት እየተሰጠ ነው። ከዳታ ሰንተር ተከላ ጋር ተያይዞ 500 VDI ኮምፒዩተሮች እየተተከሉ ነው። (አፈፃፀም 85%) | | |

## 5. ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በ2007 የትምህርት አመት በርከት ያሉ ችግሮች ያጋጠሙ ሲሆን በዋናነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው።

### 5.1. የውሃ ችግር

ዩኒቨርሰቲው የውሃ አገልግሎት እያገኘ የነበረው ለዚሁ አገልግሎት ተብለው በአከባቢው ከተቆፈሩት ሁለት ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ነው። በዚሁም መሰረት ውሃው ከነዚህ ጉድጓዶች በዩኒቨርሲቲው ቅጥረ ግቢ ወደተሰሩት ሁለት የማጠራቀምያ ሪዘርቫየሮች (አንደኛው 200 ሜትር ኩብ፤ ሁለተኛው ደግሞ 500 ሜትር ኩብ) ፓምፕ የሚደረግ ሲሆን ከነዚህ ማጠራቀምያዎች ደግሞ ወደየቦታው በግራቪቲ እንዲሰራጭ ይደረጋል። በዚሁም መሰረት እስከ 2006 ማለቅያ አከባቢ ጥሩ የውሃ አቅርቦት ነበር። ሆኖም በአንድ በኩል ከ2006 መጨረሻ (ማለትም ሚያዝያ 2006) ጀምሮ ከጉድጓዶቹ የሚገኘው የውሃ አቅርቦት እየቀነሰ በመምጣቱ በሌላ በኩል ደግሞ ዩኒቨርሲቲው በ2007 በርካታ አዲስ ተማሪዎችን በመቀበሉ ምክንያት የውሃ አቅርቦት ችግር አጋጥሞናል። ይህ ችግር እንደሚገጥመን ቀደም ብሎ ተገምቶ ስለነበር ተጨማሪ አራት ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ለመቆፈርና ወደ መስመሩ ለማስገባት እቅድ ተይዞ የነበረ ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ ሁለት ተቆፍረው የሚፈለገው መጠን ውሃ ሊገኝባቸው አልተቻለም። ከተቀሩት ሁለቱ ደግሞ አንደኛው ውሃ ላይገኝበት ይችላል ተብሎ የተተወ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቀደም ብሎ ቦታው ለኢንቨስተር የተሰጠ ቦታ ነው ተብሎ ቁፋሮ ማካሄድ አልተቻለም። በዚሁም ምክንያት እስካሁን የተደረጉት ጥረቶች ውጤታማ ሊሆኑ አልቻሉም። እንደጊዚያዊ መፍትሄ ትልቅ አቅም ያላቸው በርካታ ሮቶዎች በግቢው ውስጥ እንዲተከሉ በማድረግ እና ከነባሮቹ ጉድጓዶች ከሚገኘው የመስመር ውሃ ጋር በማቀናጀት በቦቴ ውሃ እየተሞሉ ለተማሪዎች አገልግሎት ይሰጣሉ። ይሄንን በማድረግ የውሃ ችግሩን ለማስተዳደር (manage ለማድረግ) የተቻለ ቢሆንም በዘላቂነት ለመፍታት ግን አልተቻለም። በ2008 ችግሩ በዘላቂነት የሚፈታበት አቅጣጫ ከወዲሁ የተቀመጠ ስለሆነ ውጤት ይገኝበታል ተብሎ ይታሰባል። የውሃ ችግር ግን በ2008 የትምህርት ዘመን ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም።

### 5.2. በሁለተኛው ግቢ የግንባታ ስራ በወቅቱ አለመጀመሩና የፍሳሽ ማጣርያ ግንባታ መጓተቱ

ዩኒቨርሲቲው ሁለት ግቢ ያለው ሲሆን እስካሁን ሁሉም ግንባታዎች የተሰሩትና እና ጠቅላላ ስራውን እያከናወነ ያለው በዋናው ግቢ ብቻ ነው። ሁለተኛ ግቢ ቀደም ብሎ የተፈቀደ 60 ሄክታርና ፤ ቆየት ብሎ ደግሞ ተጨማሪ ቦታ ይሰጠን ብለን ለከተማው አስተዳደር በጠየቅነው መሰረት የተፈቀደልን 55 ሄክታር በድምሩ 115 ሄክታር የሚያካትት ሲሆን በ2007 የስራ ዘመን በዚሁ ግቢ ለጠቅላላው የማስተር ፕላን ስራ በተለይም ቀደም ብሎ በተፈቀደልን ቦታ (ማለትም 60 ሄክታር ደግሞ) የዲዛይን አዳፕቴሽን ስራ በማድረግ 33 ብሎኮች ለመስራት እቅድ ተይዟል። ይሁን እንጂ በአንድ በኩል የማስተር ፕላኑን እና የዲዛይን አዳፕቴሽን ስራውን የሚሰራ አማካሪ ድርጅት መቅጠር ያስፈልግ ስለነበረ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ ያላለቁና የሚያከራክሩ ጉዳዮች ስለነበሩ ግንባታው በታሰበው ጊዜ ሊከናወን አልቻለም። የአማካሪ ድርጅት በጨረታ ለመቅጠር ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪዎች ቀርበው የጨረታ ትንተና ተደርጎ የአሸናፊ መረጣ ተከናውኖ የማስተር ፕላን እና የዲዛይን አዳፕቴሽን ስራ ተሰርቷል። ከካሳ ክፍያ እና ቦታ ማስለቀቅ ተያይዞ ለሚነሱት ጉዳዮች ደግሞ ከዞኑ እና ከወረዳው አስተዳደር ጋር ተደጋጋሚ ውይይት ተደርጎበት ቀደም ብሎ ካሳ ላልተከፈላቸው 16 ነዋሪዎች ዩኒቨርሲቲው ካሳ እንዲከፍላቸው ተደርጓል (በርግጥ አንዳንዶቹ ግምቱ ያንሰናል ብለው ያልወሰዱ አሉ)።

ሌላው ያጋጠመው ችግር በዋናው ግቢ እየተሰራ ያለው የፍሳሽ ማጣርያ (Waster Water Treatment Plant) ግንባታ የተጓተተ መሆኑ ነው። ይህ ግንባታ እየተከናወነ ያለው ለዋናው ግቢ ቀደም ብሎ ከተፈቀደው ቦታ በተጨማሪ ቦታ ተፈቅዶልን እየተሰራ ይገኛል። በቦታው የነበሩ ሰዎች ለህጋዊ ይዞታቸው በአግባቡ ካሳ ተከፍሎዋቸው ቦታውን እንዲለቁ ተደርገዋል። በአግባቡ ካሳ የተከፈላቸው ነዋሪዎች የማስለቀቁ ሂደት ከተገመተው ጊዜ በላይ የወሰደ ሲሆን በዚሁም ምክንያት ግንባታው በሚፈለገው ጊዜ ሊጀመር አልቻለም፤ ከተጀመረ በኋላም በሚፈለገው መልኩ ሊቀጥል

አልቻለም ብቻ ሳይሆን ስራው መሃል ላይ እንዲቆም የተደረገበት ሁኔታም ነበር። ለዚሁ ዋናው ምክንያት ከቦታው መነሳት የነበረባቸው ነዋሪዎች የካሳ ይገባኛል ጥያቄ በማንሳት ሊነሱ አለመቻላቸው ነው። ችግሩ ከዞኑም ከወረዳውም አስተዳድር ጋር ግንኙነት ተደርጎበት መጨረሻ ላይ ቢፈታም ረጅም ጊዜ መውሰዱ ግን አልቀረም።

## 5.3. የኢንተርኔት ብሮድባንድ አገልግሎት በምንከፍለው መጠን የማናገኝ መሆናችን

ለዩኒቨርሲቲው የኢንተርኔት አገልግሎት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ እስከ ዩኒቨርሰቲው ድረስ የፋይበር ዝርጋታ የተደረገ እና የ50 ሜጋቢት መስመር እንዲደርሰን ለኢትዮቴሌኮም ጥያቄ አቅርበን በዚሁ መሰረት እየከፈልን ቢሆንም ወደ ግቢው እየደረሰ ያለው አገልግሎት ግን በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። የምንከፍልበትን መጠን ያህል አገልግሎት የማናገኝ መሆኑ አንድ ነገር ሆኖ በሌላ በኩል ግን አገልግሎቱ በተደጋጋሚ ስለሚቋራረጥ አስተማማኝ አገልግሎት ማግኘት አልተቻለም። ጉዳዩን በተመለከተ በተደጋጋሚ ለኢትዮ ቴሌኮም ያሳወቅን ቢሆንም እስካሁን ሊፈታ ያልቻለ ጉዳይ ነው። እንደምፍትሄ ይሆናል ተብሎ የታሰበው መስመሩን ከኢመሴጅ ጋር ከሚሆን ከኮር ስዊች ጋር እንዲገናኝ ይደረጋል ተብሎ መልስ ተሰጥቶን ለዚሁም ይረዳ ዘንድ ከ50 ሜጋቢት ወደ 100 ሜጋቢት እንድናሳድገው ሃሳብ ተሰጥቶን ጥያቄውን ልከን በዚሁ መሰረት ክፍያውን ከፈፀምን እንደፈፀምን ችግሩ ይቃለላል ወይም ይፈታል የሚል ተስፋ አለን።

## 5.4. የሚቀሩ የላቦራቶሪ እና ዎርክሾች አገልግሎት መኖራቸው

